# ጋብቻ እና ፍቺ

አሁን ለአፍታ ራሶቻችንን ለጸሎት ዝቅ እናድርግ። እጅግ ርህሩህ አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ቀኑ ያዘለው ነገር ፊት ለመጋፈጥ በዚህ አዳራሽ ውስጥ ስለተገኘን፡ እድሉንም ስላገኘን እናመሰግንሃለን። ቀኑ ያዘለው ነገር ምን እንደሆነ ባናውቅም፡ ቀኑን የያዘው ግን እናውቀዋለን። ስለዚህ ዛሬ እሱን ለማገልገል፡ እንዴት መኖር እንዳለብን ለማወቅ፡ በፊቱ በሰሙ ተሰብሰበናልና ዛሬን እና ነገን እንዲሁም ዘለአለምን በእጁ የያዘውን፡ እርሱ እንዲባርከን እንጸልያለን። አባት ሆይ፡ አሳባችን በሙሉ ይህ ነው። ልባችን የሚያውቃት፡ አምላክ፡ ይህ እውነት እንደሆነ ያውቃልና። በአገልግሎትህ—ቀሪ የቀኑ ክፍለ ጊዜ ጋር፡ እራሳችንን፡ ለአንተ እናቀርባለን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ኣሜን።

2 ተቀመጡ። (አመሰግናለው። እዚህ ጋርም ሌላ አለ።)

3 ዛሬ እዚህ የምትታዩኝ እና በመላ አገሪቱ ሆናችሁ በስልክ መስመር የምትከታተሉ ታዳሚዎች በሙሉ፡ እንደምን አደራችሁ። ይህ ወደዚህ እንድመጣ እና ዛሬ ጠዋት በዚህ ወሳኝ ርዕስ ጉዳይ ላይ ለመናገር ትልቅ እድል ሰጥቶኛል። እዚህ ለሚታዩኝ ታዳሚዎች፡ ከፊት ለፊቴ መጋረጃ ተዘርግቷልና፡ በርግጥ በትንሹ ግራ የሚያጋባ ነው፡ በዚህም ምክንያት ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ መናገር ይጠበቅብኛል። እና ለማይታዩኝ ታዳሚዎች፡ በቀኜ በኩል አዳራሹ ሲሆን፡ በግራዬ ደርግሞ ጂምናዚየሙ ይገኛል፡ እኔም ወለሉ ላይ ነኝ፡ መጋረጃዎቹም፡ በቀኜ እና በግራዬ ተከፍተዋል። እናም ዛሬ ጠዋት፡ አዳራሹ፡ እንዲሁም ጂምናዚየሙ፡ ሞልቶ ተትረፍርፏል፡ በኤይት ኤንድ ፔን ጎዳና የሚገኘው ቸርችም፡ ቸርቹም እንዲሁ ሞልቷል። በተትረፈረፈባቸው ቦታዎችም፡ የቴሌፎን መስመሩ ወደ ሌሎች ቦታዎች እያሰራጨ ይገኛል።

4 ከጌታ ጋር ታላቅ ጊዜ አሳልፈናል፡ ስለ ዛሬ ማለዳ አገልግሎትም በታላቅ ጉጉት እየተጠባበቅን እንገኛለን። አሁንም ላለፉት አራት ቀናት የቆየው ካምፔን ፍጻሜ ዛሬ ማታ በመሆኑ፡ ይኸው፡ መገኘት የሚችሉ ሁሉ፡ የቻልነውን ያህል፡ ጋብዘናል። ጌታ ዛሬ ምሽት እጅግ በጣም ባልተለመደ መልኩ አንዳች ነገር በማድረግ ታላቅ ፍጻሜ እንደያደርግልን እናምናለን፡ አብዛኛው ጊዜ እንደሚያደርገው የታመሙትን እንደሚፈውስ እና ታላላቅ ነገሮች እንደሚያደርግ እናምነዋለን። እና ምሽቱን በጉጉት እየተጠባበቅን እንገኛለን። ሕዝቡ ሁሉ፡ ከየሐይማኖት ተቋም እና ከየቸርቹ፡ በአክብሮት ተጋብዘዋል። እዚህ ለመምጣት ክርስቲያኖች መሆን አይጠበቅባችሁም፥ ኃጢአተኞች በመካከላችን እንዲመጡ፡ እንዲቀመጡ በርግጥ እንፈልጋለን። እኛም በሕይወት እንድንኖር የጌታ መንገድ ምን እንደ ሆነ ለማስተማር፡ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።

5 አሁን ታዳሚዎች እንደማይጨነቁ ተስፋ አደርጋለሁ። እኔም እንዳልጨናነቅ በጌታ እታመናለሁ፡ ከባድ ማታ አሳልፌአለሁ፡ እጅግ ብዙ ውጥረት ነበረብኝ። ዛሬ በማለዳ የምናገረው ነገር በፍርድ ቀን በእኔ ላይ እንደሚሆን አውቃለሁና፡ ስለዚህ ሳ—ሳልተኛ ነው ያደርኩት፡ ካልተናገርኩትም በፍርድ ቀን በእኔ

ላይ እንደሚቆጠርብኝ አውቃለሁና። ስለዚህ ከባድ ያደርገዋል፡ መግለጽ አትችሉም።

6 እና አሁን ዛሬ ጠዋት ስለ **ጋብቻ እና ፍቺ** የምንወያይበት ታላቅ ርዕስ ጉዳይ ነው። በሰንበት ትምህርት ያደረግሁበት ምክንያትም፡ በላዩ ላይ ሌላ ሰብከት ከመሰበክ ይልቅ፡ ስለ ጉዳዩ እንድንነጋገርና በቂ ጊዜ እንዲኖረን በማሰብ ነው። ከቃሉ የተገኘ ትምህርት ነው።

7 እና እኔ—እኔ ማለት የምፈልገው፡ ይህ ቅጂ በየትኛውም ሰፍራ ለሚገኝ፡ አገልጋይ፡ ወይም በአገልጋዮች እጅ ከገባ፡ ይህን ካሴት ከለቀቅነው... ቤተክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደምታደርግ አላውቅም። ወንድም ፍሬድ ይህን ካሴት ከመልቀቁ በፊት የቤተክርስቲያኑን ቦርድ እንዲያወያይ እጠይቃለሁ። እና በመላው አገሪቱ ለምትገኙ ሰዎች፡ የቴፕ መቅጃዎቻችሁ አዘጋጅታችሁ ላላችሁ ሰዎች እላለሁ፡ እባካችሁ ስለ ጉዳዩ ከወንድም ሶትማን ካልሰማችሁ በቀር ቴፑን አታሰራጩ።

8 አሁን፡ ከተለቀቀ ግን፡ አገልጋይ የሆናችሁ፡ ወይም በየትኛውም ሰፍራ የምትገኙ፡ እኔ በምናገረው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የማትሰማሙ ክርስቲያን ወንድሜቹ፡ እንደማትነቅፉት ተስፋ አ—አደርጋለሁ። እኔ ባስተማርኩት መንገድ፡ ካልተረዳችሁት፡ እንደ አገልጋይ፡ እንደ እረኛ፡ ለዚያም መብት አላችሁ። የምታምኑትን ሁሉ አከብራለሁ።

9 እናም በዚህ ርዕስ ላይ ሁለት ጽንፎች አሉ። እና ሁለት ጥያቄዎች ሲኖሩም፡ ከመካከላቸው አንዱ ትክክል መሆን አለበት፡ ወይም ሁለቱም ትክክል አይደሉም። ስለዚህ ይህንን ለማስተካከል፡ ዛሬ ጠዋት፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለመፈተሽ እንሞክራለን። ለእኔ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ ከሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ መልሱን ይዟል።

10 አሁንም እነዚህ ነገሮች፡ ማለቴ፡ ርዕስ ጉዳዩ ከመዳሰሳችን በፊት፡ በቃሉ ላይ ከመጸለዬ በፊት፡ ሁላችሁንም እንዲህ ልል እፈልጋለሁ፡ በተለይ... ክርስቲያኖች የሆናችሁ፡ ዛሬ ማለዳ... እንድትጸልዩልኝ እ—እፈልጋችኋለሁ። እናንተ በማይታዩ ታዳሚዎች ዘንድ ያላችሁም እንዲሁ፡ ጸልዩልኝ፡ ምክንያቱም ቅን እና እውነተኛ መሆን እፈልጋለሁ።

11 አሁን እነዚህን አሳቦች ስናስቀምጥ፡ የሆነ አካል፡ አንድ ሰው ብቻ ቢሆንም እንኳ፡ ይህ ነገር ወይ ሞት ወይ ህይወት በማለት፡ እንደሚይዘው እንገነዘባለን። አምናችሁ የምትወጡ ብዝዎች እዚህ አላችሁ። በርግጥ፡ ምናልባትም፡ ብዙዎች፡ አታምኑትም። ነገር ግን፡ በእኔ አገልግሎት፡ እኔን ለመሰማት፡ እኔ የምናገራቸውን ለመሰማት የሚመጡ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ፥ እነዚህም፡ ዛሬ፡ በዚህ ማለዳ እዚህ ተቀምጠዋል፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም፡ ብዙዎች ከዩናይትድ ስቴትስ፡ ከካናዳ፡ እና ከባሕር ማዶ ሁሉ። እናም የዚያ ሰው ዘላለማዊ መዳረሻ በእጃችሁ ላይ እንዳለ ሰታውቁት፡ የሚፈጥርባችሁ ጫና መገመት ትችላላችሁ፡ ምክንያቱም የምትናገሩትን ነገር ከልብ ይቀበለዋል። ስለዚህ እግዚአብሔርም ይጠይቀኛል፡ በዚህም ምክንያት በቻልኩት መጠን ቅን መሆን እፈልጋለሁ።

12 አሁን እ—እህቶቻችንን እጠይቃለሁ። እና በፊታቸው እናገር ዘንድ አንዳንድ ቃሎቼን ቀይሬአለሁ። ቢሊ ዛሬ ጠዋት፡ በ—በድብልቅ ህዝብ ፊት የማይነገሩ ነገሮች፡ በኪሱ ውስጥ ይዞ፡ በዚያ አለ። እና ምናልባት አንዳንዶቹን

ልላቸው ስለምችል፡ መረዳት አለባችሁ። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ፡ ከገዛ ወንድማችሁ እንደሰማችሁ አርጋችሁ—ተቀበሉት። በዶክተር በቢሮው ፊት ስትቀርቡም ትሰሙታላችሁና፡ እያንዳንዷን ነገር ልቅም አርጎ ይናገራችኋል። እና አንዳንዶቻችሁ ወጣት ሴቶች እና ወጣት ወንዶች፡ የተሳሳተ ግንዛቤ እንድትይዙ አልፈልግም። እንድታምኑ እና፡ ኣንድትረጋጉ እፈልጋለሁ። ልብ በሉ፡ እውነትን እውነት መባል አለበት።

13 አሁንም፡ ብዙዎቻችሁ፡ በሚባለው ነገር እንደማትስማሙ ምንም ጥርጥር የለውም፡ እኔ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። እንደው ትሑታን ከሆናችሁ እና ከሰማችሁ፡ እስከ ዛሬ ድረስ፡ ሰጎሰመው የነበረውን ነገር በተሻለ መልኩ የመረዳት እና ጭብጥ የመያዝ፡ አጋጣሚ እንደሚሆንላችሁ አምናለሁ። ይህ እንደሚያብራራው አምናለሁ፡ እንደሚሆንም እተማመናለሁ።

14 አሁን በዚህ ላይ፡ ትንሽ ጊዜ ልንወስድ እንችላለን፡ አንድ ሰዓት ተኩል፡ ምናልባትም ከዚያ በላይ። ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ አላውቅም።

15 አሁንም እንደገና፡ ማለት የምፈልገው ነገር፡ በዚህ ጊዜ፡ ሰዎች፡ በቃላችሁ የምትገኙ መሆናችሁ በማወቅ፡ አዎን ለፓስተሮቻቸው፡ እንደዚያ ናቸው። እኔም፡ እርግጥ ነው፡ ፓስተር ነበርኩና።

16 እና የፓስተራቸውን ቃል፡ ልክ በሞት እና በሕይወት መካከል እንዳለ ነገር አርገው ያከብሩታል። የቄሳቸው ቃል፡ በሞት እና በሕይወት መካከል እንዳለ ነገር አርገው ያከብሩታል። እርግጥ ነው፡ ፓስተሩም፡ በሚችለው አቅም ሁሉ፡ በሴሚናር ውስጥ እንደተማረው ህዝቡን ያስተምራቸዋል፥ በሌሎች ሐይማኖቶችም፡ ቄሱ፡ ያለ ጥርጥር እንዲህ እንደሚያደርግ የተረጋገጠ ነው። እርግጥ፡ ፓስተሩ ራሱ ቄስ ነው፡ የሚማልድ ነው። ስለዚህ፡ ቄሱ፡ በሴሚናር ሁሉ እና በገዳማት፡ የተማራቸው ነገሮች፡ ይህ ሰው በቅንነት ሁሉ እንደተማረው መንገድ ይናገራል።

17 እንግዲህ፡ እኔ ምንም ዓይነት የሴሚናሪ ልምምድ፡ ወይም የገዳም ልምምድ የለኝም፡ ይህ ሁሉ አልተቃወምኩም፡ ግን በጣም የተለየ ሕይወት አለኝ።

18 የተጠራሁት ገና ትንሽ ልጅ ሳለሁ ነበር። እናም በሰባት ዓመቴ ሳለሁ፡ በጫካ ውስጥ ከሚመላለስ የእሳት አምድ ውስጥ፡ በግልጽ የሚታይ—የሚሰማም፡ ምልክት ተሰጠኝ፡ እዚህ በዩቲካ ፓይክ ላይ ነበር። አባቴ በቅርብ ጊዜ ከሞተው ከአቶ ኦ. ኤች. ዋተን ጋር ይሰራ ነበር። መጽሐፉን ስላነበባችሁት፡ ታሪኩን ታውቁታላችሁ። እና በዚያ ወቅት... በወንዙ ላይ በወረደ ጊዜ በህዝብ ፊት በግልጽ ታይቷል። አሁንም በዚ ጊዜ፡ ምስሉ በተደጋጋሚ ተነስቷል፡ እና በዋሽንግተን፡ ዲሲ፡ የቅጂ መብት ተደርጎለት፡ በሃይማኖታዊ ጥበብ አዳራሽ ውስጥ ተሰቅሎ ይገኛል፡ በሳይንሳዊ ፎቶግራፍ መነሳቱ የተረጋገጠ ብቸኛው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሰዕል እንደሆነ ታምኖበታል፥ እስራኤልን ከግብፅ ያወጣው፡ በሁሉም መንገድ በተመሳሳይ ሁኔታ፡ የእስራኤል ልጆችን ከግብጽ ያወጣቸው እርሱ ነው። በእግዚአብሔር ልጅነት ሰራው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ መልኩ እንደሆነ አምናለሁ።

19 ያኔ መጀመሪያ በመጣ ጊዜ "የሰው ልጅ" ተባለ፡ አሁን ደግሞ "የእግዚአብሔር ልጅ" ይባላል፡ በሚሊኒየም ውስጥ "የዳዊት ልጅ" ይሆናል። ስለ እርሱ እንደ ተባለ፡ የሰው ልጅ፡ ነቢይ ሆኖ መጣ፥ አሁን ከተፈጥሮ

በላይ በሆነ፡ በእግዚአብሔር ልጅነት፥ በሚመጣው ታላቁ ሺህ ዓመት፡ የዳዊት ልጅ ይሆናል፡ በዳዊት ዙፋን ላይ ይቀመጣል። የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች እንደሚያውቁት ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ ለዳዊት የተገባለት መለኮታዊ ቃል ኪዳን ነው፡ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጥ ልጅ እንደሚያስነሣለት ተናግሯልና።

20 አሁንም እኔ በተለየ መንገድ፡ በልዩ አገልግሎቴ ላይ፡ እርሱ "እግዚአብሔር" ነው ከመባል ጀምሮ እስከ "ዲያብሎስ" ነው መባል ደርሻለሁ። ይህም፡ ሁሌ እንደዚያው ነው።

21 ያን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በሌሊት ስብሰባ በነበረን ጊዜ፡ በዚያው ምሽት የነገሩኝ ያ ነበር፡ እንዲህ አሉኝ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ በነብይ ኢሳያስ አስቀድሞ እንደተነገረለት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ራሱን በግልፅ ታውቋል።" እንዲህ አለ፡ "የአንተ አገልግሎትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በግልጽ የታወቀ ነው።" እንዲህ አለ፡ "ሉተራኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ።" "ሉተራውያን ሉተርን ያውቁት ነበር። ዌስሊአውያን ዌስሊን ያውቁት ነበር። እነዚህ ጴንጤቆስጤዎቹስ? " አለ፡ "እየተንከራተቱ ነው። የት መሄድ እንዳለባቸው አያውቁም፡" አለ።

እኔም "ጌታዬ፡ በጣም አመሰግናለሁ፡" አልኩት።

22 መንፈሱ በሴቲቱ ላይ የወረደው ያን ጊዜ ነበር፡ ሚስቱ ናት፡ አይታኝ አታውቅም ነበር... እሷም አንድ አይነት ነገር አሳወቀች።

23 አሁን፡ እውነቱን ለመናገር፡ ዛሬ ጠዋት ከምናገረው ከዚህ መልእክት በፊት፡ እኔ አላውቅም። እኔም እንዲህ ነገርኩት፡ አልኩትም፡ "ጌታዬ፡ እኔ እንዲህ ነው ማለት አልችልም። እንዲህ ብሎ ለመናገር ይከብዳል። እንዲሁ ይመስላል።"

24 አንድ የማውቀው ነገር፡ በእርግጠኛነት፡ የተፈጸመ ነገር እንዳለ ብቻ ነው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ ልክ፡ በሳይንስ የተረጋገጡ፡ እና በአለም እና በአለም ዙሪያ ተረጋግጧል፡ ተረት ብቻ ሊሆን አይችልም። እውነታ ነው። ምን ይሆን? ዛሬ ጠዋት፡ ይህን ለእናንተ ከማናገሬ በፊት፡ ልናዘዝ፡ እኔ አላውቅም። እናም ከዚህ በፊት ካናገረኝ ከእርሱ እስክስማ ድረስ እና ስለ እነዚህ ነገሮች እስኪነግረኝ ድረስ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ለማድረግ አልደፍርም።

25 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ራሱ ፈጽሞ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ እንደማያውቅ፡ አስታውሱ። እርሱ ያለው፡ "አንተ አልክ፥ ለዚህም ተወለድኩ፡" ወዘተረፈ፡ እንጂ ስለ ራሱ እኔ ይህ ነኝ ፈጽሞ አላለም።

26 እንግዲህ፡ አሁን፡ የእስራኤልን ልጆች የመራው ያን የእሳት ዓምድ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ መልክ ነበር፡ (ይህን ታምናላችሁ? )፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወጣ ሎጎስ እርሱ ነው።

27 ከዚያም በምድር ላይ ሳለ፡ እንዲህ አለ፡ "ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁ፡ ወደ እግዚአብሔርም እሄዳለሁ።" ይህን ሁላችንም እናውቃለን።

28 ከሞተ፡ ከተቀበረና፡ ከትንሣኤው በኋላ፥ ሳውል የተባለ የጠርሰስ ሰው ክርስቲያኖችን—ለማሳደድ፡ በደማስቆ መንገድ ይሄድ ነበር፡ ምክንያቱም እነሱ የተማሩትን የሚጻረር ነገር ያስተምሩ ነበርና። በዚያም በትምህርት ቤታቸው፡ በገዳማቸው ውስጥ፡ በዚያ ዘመን ከነበሩ ታላላቅ አስተማሪዎች፡ ገማልያል

በተባለ ሰው፡ እግሩ ስር የነበረ ታላቅ ሰው፡ ታላቅ ተዋጊ፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ኦፊሰር ነበር። በዚያም ነበር በጠራራ ቀን ላይ፡ ታላቅ የሆነ ብርሃን፡ የእሳቱ ዓምድ፡ ያንጸባረቀበት። ድምፅም እንዲህ አለው፡ "ሳውል፡ ሳውል ሆይ፡ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? "

29 አሁን ልብ ብላችሁ ከሆነ ጳውሎስ፡ ማለት ሳውል፡ ተነሣና፡ እንዲህ አለ፡ "ጌታ ሆይ፡ አንተ ማን ነህ? " አሁን፡ ይህ ሰው፡ አይሁዳዊ ሆኖ፡ እግዚአብሔርን የሚያመላክት ነገር ካልሆነ በቀር፡ ማንንም እንዲህ ብሎ አይጠራም ነበር፡ ማንንም "ጌታ" ብሎ አይጠራም ነበር። ስለዚህ፡ ያው የእሳት ዓምድ ነበረ።

30 ኢየሱስ ተናግሮ ነበር፦ "ወደ እግዚአብሔር እሄዳለሁ። ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁ፡ ወደ እግዚአብሔርም እመለሳለሁ" ብሏል።

31 አሁንም ይኸው፡ እንደገና በእሳት ዓምድ መልክ፥ እንዲህ ብሎ መለሰለት፡ "አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፥ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል።"

32 እና ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ቁልፍ የተሰጠው ሐዋርያው ጴጥሮስ፡ በእስር ቤት ውስጥ በገባ ጊዜ፡ እና ይህ የእሳት አምድ፡ በመወርወሪያዎቹ ውስጥ አልፎ፡ የእስር ቤቱን በሮች ከፍቶ፡ ዘበኞቹን ሳይረብሽ፡ በምስጢር፡ ጴጥሮስን እንደወሰደው ተገንዝበናል። ይህ ለእኔ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው መሆኑ ነው።

33 በተጨማሪም የትኛውም ነገር በተፈጥሮው ይታወቃል። ማንኛውም ነገር በተፈጥሮ፡ ማለት በሚያፈራው ፍሬ ይታወቃል። እኔም የሚያፈራውን የፍሬ ዓይነት እንድትመለከቱ እጠይቃችኋለሁ፡ ይህም ብርሃን ማለት እግዚአብሄር ነው፡ ምክንያቱም ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይሄዳል፡ እና የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክራል፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብካል፡ እግዚአብሔርም ያንን ቃል በተግባር በፊታችሁ ያረጋግጣል። ከበስተጀርባው የሆነ ነገር ሳይኖር አይቀርም።

34 ሰዎች ነብይ ብለው ይጠሩኛል። እኔ ራሴን ነብይ ብዬ አልጠራም፡ ምክንያቱም ይህን ለማለት አልደፍርም፡ ነገር ግን... ይህን እላለሁ... ይህን እናገራለሁ፡ ጌታ ነገሮች ማየት እንድችል አድርጎኛል፡ የተፈጸሙ ነገሮች፡ ወደፊት ሊፈጸሙ ያላቸው ነገሮች፡ እና እየተፈጸሙ ያሉ ነገሮች እንድናገር አድርጎኛል፡ እና በሺህዎች በሚቆጠሩ ጊዜያት፡ አንድ ጊዜ እንኳ መሬት ላይ አልወደቀም። ይሆናል ብሎ የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ፡ ሆነዋል። ሁላችንም እናውቃለን። ዛሬ ጠዋት በዚህ በሚታዩ ታዳሚዎች፡ ወይም በማንኛውም ቦታ፡ ይህ አልተፈጸመም የሚል ሰው ካለ፡ ተነስታችሁ ለመናገር ነጻነት አላችሁ። ነገር ግን በሺዎች በሚቆጠሩ ጊዜያት ውስጥ፡ በትክክል እንደተፈጸሙ፡ የምታውቁ ከሆናችሁ፡ "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው "አሜን!" አለ፡—አርታዒ።] አያችሁ? ስለዚህ ያ በዓለም ዙሪያ ተመሳሳይ ነገር ይሆናል።

35 የሆነ ነገር ሊሆን እየተቃረበ ይገኛል። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ከበስተጀርባ የሆነ ዓላማ ሳይኖረው ፈጽሞ አይልካቸውም።

36 እዚህ ጋር እያሰብኩት ነበር። በማስታወሻዬ ውስጥ፡ እዚህ ጋር ጽፌዋለሁ። እኔ ዛሬ ማለዳ እነዚህን; የተደረደሩ የልብስ ቁልፎች እንደለበስኩ... እና ብዙዎቻችሁ የፊልም ተዋናይቷ፡ ጄን ሩሰልን ታውቋታላችሁ፡ እናቷም ጴንጤ ናት፥ እና ዳኒ ሄንሪም የአክስቷ ልጅ ነው፡ ዋና የአክስቷ ልጅ፡ የእናቷ እህት

ልጅ ነው። እርሱም ባፕቲስት ነበር። ከሁለት አመት በፊት በሎስ አንጀለስ፡ ካሊፎርኒያ፡ በተደረገው የቢዝነስ ሜን ስብሰባ፡ በስብሰባ ላይ ቆሞ ነበር።

37 እና ታላቅ፡ ኃይለኛ፡ እና ግፊት ያለው አሳብ ተናግሬ ገና መጨረሴ ነበርና፡ ዋናው የበላይ ኃላፊው፡ የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ የበላይ ኃላፊ፡ ተቀምጦበት ከነበረው ከባልኮኒው ወርዶ ወደ መድረኩ መጣና፡ እንዲህ አለ "ወንድም ብራንሃም ይህን ለማለት ፈልጎ ነው ብዬ አላምንም፡" አለ።

38 እኔም "እንደዚያው ማለቴ ነው፡ ጌታዬ። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው።" እናም፡ ነገሩም፡ በዚህ ዘመን ስላለችው ቤተ ክርስቲያን፡ በተመለከተ ነበር።

39 እና በዚያን ሰዓት አካባቢ፡ ነጋዴ የሆነው ይህ ወጣት... ወንድሙም እዛው ጋር... ያን ቀን ማለዳ ስለ ቴሌቪዥን ስርጭት ቀረጻ እያደረገ ነበረ፡ ሌላኛው ወንድሙም የ—የካሊፎርኒያ መንገዶች ተቆጣጣሪ ነው። እና ስብሰባው ካለቀ በኋላ ዳኒ ሄንሪ ወደፊት፡ ሰዎቹ ሁሉ ወደተቀመጡበት፡ ወደ መድረኩ፡ **እንዲህ** መጣና፡ እጆቹን በእኔ ላይ ጣል ለማድረግ ወረደ። እነዚህንም ቃላት ተናገረኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ይህ መመናፈስ እንዳይመስልብኝ ተሰፋ አደርጋለሁ፡ ይሁን እንጂ፡" "ይህ የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 23 መባል ይቻላል፡" አለኝ። በራእይ ዮሐንስ ውስጥ ሃያ-ሁለት ምዕራፎች ብቻ፡ ናቸውና። "መመናፈስ እንዳይመስልብኝ ተሰፋ አደርጋለሁ፡" አለኝ። ገና ተናግሮ ሳይጨርስ... እንግዲህ፡ ልጁ ባፕቲስት ነው፡ ስለ መለኮታዊ ነገር አንዳች አያውቅም። ክንዶቹ ትከሻዬ ላይ እንዳደረገ፡ በልሳን መናገር ጀመረ።

40 በልሳን መናገሩን ከጨረሰ በኋላ፡ ከፊት ለፊቴ፡ አንዲት ጥቁር—ወፍራም ሴት ተቀምጣ ነበር፡ ተነስታ እንዲህ አለች፡ "ይህ'ማ ትርጉም አያስፈልገውም፡" ብላ ተናገረች። "እኔ ራሴ ከሽሬቬፖርት፡ ሉዊዚያና፡ ወይም፡ ከባቶን ሩዥ፡ ሉዊዚያና ነኝና፡" አለች። "ይህ በግልጽ ፈረንሳይኛ ነው፡" ብላ ተናገረች።

41 ፈረንሳዊ የነበረው፡ ቪክቶር ሌ ዱክስ፡ እዚያም ተቀምጦ ከነበረበት ሆኖ፡ እንዲህ አለ፦ "በእርግጠኝነት፡ እኔ ፈረንሳዊ ነኝ፡ ይህም ፍፁም ፈረንሳይኛ ነው አለ።"

42 እኔም አልኳቸው፡ "ይኸውላችሁ። ምንም ከማለታችሁ በፊት፡ እስኪ **አንተ** የተናገረውን ጻፍ፡ **አንተም** እሱ የተናገረውን ጻፍ። የምትሉትን ጻፉና፡ ማስታወሻዎቹን እንያቸው። እናም አንዱ ጻፈ፡ ሌላኛውም ጻፈ፡ ሥርዓተ ነጥቡ ሳይቀር ተመሳሳይ ነበር።

43 እና የጻፉትን ማስታወሻ፡ ለማምጣት በተዘጋጁ ጊዜ፡ እነሆ መልከ-መልካም፡ ባለ ወርቃማ-ጸጉር ወጣት ከኋላ ተነስቶ መጣ። እርሱም፡ የሚቀመጥበት ሰፍራ ስላልነበረው፡ ከኋላ ቆሞ ነበር። ተራምዶ መጣና፡ እንዲህ አለ፡ "ይኸውላችሁ፡ እኔም፡ መጻፍ እፈልጋለሁ አለ።" "እኔ ለተባበሩት መንግስታት UN፡ የፈረንሳይኛ አስተርጓሚ ነኝ፡" አለ። "እኔም ማስታወሻዬ ላይ ጽፌ ማምጣት እፈልጋለሁ፡" አለ።

44 እነሆም፡ ሶሥቱም፡ ማስታወሻዎች፡ በፈረንሳይኛ ተመሳሳይ ነበሩ። እንዲህም ይነበባል። ይህ የማስታወሻው ዋናው ነው፡ ከዚያ የተወሰደ ነው። ይህ የዳኒ፡ የራሱ ማስታወሻ ነው፡ ኪሱ ላይ ይዞት ነበርና። እርግጥም፡ ነገሩ ወደ ክርስቲያን ቢዝነስ ሜን፡ እና ወደ ሌሎች ሁሉ ተሰራጭቷል።

**ጠባቡን መንገድ፡ ከባዱ መንገድ መርጠሃልና፡ በገዛ ምርጫህም ተጉዞሃልና፡ እነሆ አንተ ትክክለኛውን እና ቅን ውሳኔ መረጥህ፡ ይህም መንገዴ ነው።**

**በዚህ ቆራጥ ውሳኔህ ምክንያት፡ በሰማይ ላይ ትልቅ ዕጣ ፈንታ ይጠብቅሃል። እንዴት ያለ የከበረ ውሳኔ ወሰንህ!**

**ይህ፡ በራሱ፡ በፍቅር መለኮታዊ ውስጥ ያለውን፡ ታላቁን ድል የሚሰጥ፡ እና እውን የሚያደርግ ነው።**

45 አሁን፡ ሰውዬው ሰሙን ፈርሞበታል፡ “ከላይ የተነገረው ነገር... በዳኒ ሄንሪ ስለ ወንድም ብራንሃም የተሰጠ ትንቢት ሲሆን በእከሌ የተተረጎመ፡ በሎስ አንጀለስ፡ ካሊፎርኒያ በሚገኘው ካፊቴሪያ በሶስት ምስክር የጸደቀ ነው ይላል።”

46 አሁን፡ ይህ ምን እየተናገረ እንደነበረ ሳያውቅ፡ ትንቢቱን የተናገረው ወጣት ራሱ፡ የዛሬ ወር አካባቢ በኢየሩሳሌም ነበረ። ወደዚያ የመሄድ አጋጣሚ አግኝቶ—ኢየሱስ ከሞተ በኋላ የተቀበረበትን መቃብር ላይ የመተኛት ዕድል አገኘ። በዚያም ተኝቶ ሳለ፡ እኔ በኃይል ወደ ልቡ መጣሁበት እና ማልቀስ ጀመረ። “አለምንና እነዚህን ነገሮች አብያተ ክርስቲያናትንም ጭምር መቃወም ለወንድም ብራንሃም እንዴት ከባድ ይሆን፡” አለ!

47 እንዱ ነው—አንዴ፡ ስለ ቢሊ ግራሃም፡ እንደተናገረው አይነት ነው፡ “ቢሊ ግራሃምን ማየት እንችላለን፡ ምክንያቱም አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት ይደግፉታልና። ኦራል ሮበርትስም እንዲሁ፡ በጴንጤቆስጤዎች። ሰዎች ከዚህ በፊት ከተማሩት በተለየ መልኩ ሲሆንብን ግን፡ እንዴት እንቀበለዋለን? ” እግዚአብሔር ነው።

48 እና፡ ዳኒ፡ በትርፍ ጊዜው ማሳለፊያ፡ ትናንሽ ድንጋዮችን ያሰጌጣል። እና መስቀሉ ወደ ነበረበት፡ ተተክሎበት ነበረ ወደሚሉት ድንጋዩ ወዳለበት ቦታ ወጣ። በአካባቢው ማንም አልነበረምና፡ ትንሽ ድንጋይ ሰበረና ለመታሰቢያ የሚሆን ኪሱ ውስጥ አደረገና፡ ወደ ቤት መጥቶ ሁለት ጥንድ የልብስ ቁልፎች ሰራልኝ። እና በሚገርም ሁኔታ፡ ሲፈጥራቸው፡ በደም የተነከሩ ድንጋዮች ይመስላሉ። እና በትክክል በሁለቱም ላይ፡ ቀጥ ብሎ፡ ወደ ታች የሚወርድ፡ ጠባብ መስመር በሁለቱም ላይ ይታያል። ምናልባት ዝም ብሎ ሊመስል ይችላል... እያችሁ፡ ሌላ ሰው ላያስተውለው ይችላል፡ ለእኔ ግን እኔ ከማምናቸው ነገሮች ጋር የሚስማማ ነው። እያንዳንዱ ነገር ከሱ ጋር ትርጉም እንዳለው አምናለሁ።

49 አሁንም፡ በዚህ ጊዜ ላይ፡ ጌታ ራሱ... ስለ ሚልኪያስ 4 እና ሉቃስ 17፡ እና በዚህ በመጨረሻው ዘመን ላይ ሊፈጸሙ የሚገባቸው፡ ሌሎች የተናገራቸው የመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢቱ ቃላት ናቸው፡ በመዝጊያው ላይ ይህን ልበል፡ ሰውዬው በሚመጣበት ጊዜ የተጣሉ የመሰረት ድንጋዮች ናቸው። ስለዚህ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ፡ እንደዚያ ከሆነ፡ ትንሽ ነገር ላደርግ ስለፈቀደልኝ በጣም አመሰግናለሁ፡ ባልተማረው ሁኔታዬ፡ ለእኔ ያለውን ፍቅር፡ ለእርሱ ያለኝን ፍቅር፡ እና ለሰዎች ያለንን ፍቅር አድናቆት ለማሳየት ነው።

50 ስለዚህ፡ በትሕትና፡ ይህ **ጋብቻ እና ፍቺ** የሚለውን ርዕስ ጉዳይ እዳስሳለሁ። እግዚአብሔር ለሁላችንም ምህረቱን ይስጥልን።

51 እና አሁን በጥሞና አዳምጡኝ። እህቶችም፡ ተነስታችሁ፡ እንዳትወጡ፥ ለአፍታ ያህል በትዕግስት ተቀመጡ። ወንድሞችም፡ እንዲሁ አድርጉ። እናንተም በዚህ የስልክ መስመር ላይ የሚተላለፍላችሁ ሰዎች ሆይ፡ አታጥፉት። እንደዚያ እንዳታደርጉ። እስኪያልቅ ድረስ ለጥቂት ደቂቃዎች በትዕግስት ተቀመጡ። በደንብ ተከታተሉኝ። በምጠቅሳቸውን ቃላት ካልተሰማችሁ፡ ከመወሰናችሁ በፊት፡ ጽፋችሁ ሂዱና በጸሎት መንፈስ ሆናችሁ አጥኗቸው።

አምላክ ሆይ፡ ወደዚህ ርዕስ ጉዳይ ስንቃረብ ሳለን እርዳን።

52 አሁን፡ ትንሽ ረዘም ያለ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በምንም እንድትቸኩሉ አልፈልግም። እና እንዴት እንደምናጠናው እንደምናውቀው፡ ሁላችንም፡ ጊዜ ወስደን፡ በእውነት እና በጥልቀት፡ የእግዚአብሔርን ቃል እናጥና።

53 በቅዱስ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ 19 እንጀምር። እና መጀመሪያው፡ ይመስለኛል፡ 19ኛው ምዕራፍ ከቁጥር 8 ላይ፡ መጀመር እፈልጋለሁ። በ1ኛው ጀምሬ፡ እስከ 19ኛው ምዕራፍ ቁጥር 8 ድረስ ማንበብም እችላለሁ።

54 አሁን፡ እነዚህ የምናገረው ነገሮች ከእግዚአብሔር ቃል የመጡ መሆን እንዳለባቸው፡ አስታውሱ። ከራሴ አስተያየት ሊሆን አይችልም፡ ምክንያቱም የእኔ አስተያየት እንደማንኛውም ሰው አስተያየት ነው። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ዘንድ ቀጣይነት ያለው መሆን አለበት። አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያለማቋረጥ ያስቀጥላልና። ፈጽሞ አይለዋወጥም። ትናንትናም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ነውና። ታምናላችሁ? እሱ ያው ነው።

55 አሁን ከ19ኛው ምዕራፍ አነባለሁ።

**እንዲህም ሆነ፡ ኢየሱስም ይህን ነገር ከፈጸመ በኋላ፡ ከገሊላ ሄደ፡ ወደ ይሁዳ አውራጃ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ መጣ፥**

**ብዙ ሕዝብም ተከተሉት፥ በዚያም ፈወሳቸው...**

**ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና፡ ሲፈትኑት፡...**

56 እሱን የሚፈትነው ማን እንደነበረ ጠቅለል ያለ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ እዚህ ላይ ቆም አደርገዋለሁ።

**... ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ፡ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን አሉት?**

**እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፡ እንዲህ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን፡ ፈጣሪ** በ**መጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥**

**አለም፡ ስለዚህ ሰው አባቱንና... እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?**

ስለዚህ **አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን፡ እንግዲህ ሰው አይለየው።**

**እነርሱም፡ እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው፡ እንዲፈቱአት... ስለ ምን አዘዘ አሉት?**

እርሱም፡ **ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፥ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።**

አሁን፡ እግዚአብሔር፡ ይርዳን።

57 ይህ የመጽሀፍ ቅዱስ ቃል፡ ይህ ጥያቄ፡ ኢየሱስን በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ የገጠመው ነው። በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ሙሴን ገጥሞታል። በአማኞች ልብ ውስጥ ቀዳሚ ጥያቄ ነው። ኃጢአተኛው ግን ደንታ የለውም። ለአማኞች ግን ነው፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት በትክክል ለመኖር የሚያውቀውን ሁሉ ለማድረግ የሚጣጣረው አማኝ ነው። ስለዚህ፡ በሐይማኖት ውስጥ በሚነሳ ጥያቄ ሁሉ፡ **የጋብቻ እና ፍቺ** ጉዳይ ይዳሰሳል። ለምን? ምክንያቱማ የመጀምሪያው ሐጢአት ጠንቅ እሱ ስለሆነ ነው። ኃጢአት የጀመረው እዚያ ነው። በየጊዜው የሚነሳበት ምክንያትም ለዚህ ነው፡ ምክንያቱም እሱ የኃጢአት መጀመሪያ ነውና።

58 አሁን እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለማብራራት ጊዜ አይኖረኝም፡ ይሁን እንጂ ደብዳቤዎቻችሁ እና ሌሎች ነገሮች ለመመልሰ ግን እጅግ ደስ ይለኛል። ወይም፡ ይሄን በተመከተ የጻፍነው መጽሀፍ አለ፡ ባለ ብዙ ጥያቄ ነው፡ የነገሩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጋዜጣዎችንና፡ ሌሎች ነገሮች ሳይቀር ቆራርጠናል፡ ሔዋን እንደሆነች ተረድተናል (በላችው የተባለው አፕል እንኳ፡ መጽሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡ አሁን ደግሞ አፕሪኮት ነው እያሉ ነው፥ ይሄም አይደለም።)፡ ዝሙት አደረገች፡ በዚያም የበኩር ልጅ፡ ቃየንን ወለደች፡ እርሱም የሰይጣን የራሱ ልጅ ነው፡ በእርሱ ዘንድ ክፋት ነበረበትና። በአቤል በኩል አልመጣም። የሰይጣን ልጅ ቃየን ነው።

59 አሁን ጥያቄአችሁን አውቄዋለሁ፡ "ሔዋን እንዲህ አለች፡ 'ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰው አገኘው።'" አዎን ይህ ትክክል ነው።

60 በከተማው ውስጥ እጅግ በጣም ቆንጆ የሆነውን ሴት፡ እና እጅግ ክፉ የተባለውን ሰው ውሰዱና፥ ሕፃን ቢወልዱ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መሆኑ ግድ ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የተደነገገ ሕግ አለውና። እና እነዚህ ሕጎች፡ ለምሳሌ ጸሀይ ስትወጣ፥ ከኩልበር በጥሩ ማሳ ላይ ብትዘሩት፡ ያድጋል። ማደጉ የማይቀር ነው፡ የእግዚአብሔር ሕግ ስለሆነ። ዘር ሲዘራ፡ ማደጉ የማይቀር ነው። ከእግዚአብሄር በቀርም ሕይወትን ማሳደግ የሚችል የለም፡ ምክንያቱ በደነገገው ስርዓት ስለሚከናወን ነው። ስለዚህ ክፉው ዘር በ—በሔዋን ማኅፀን ውስጥ በተዘራ ጊዜ፡ መብቀል ነበረበት፡ ምክንያቱ የእግዚአብሄር የማባዛት ሕግ ነውና። እና ከማብቀል በቀር ሌላ ማድረግ አይችልምና፡ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣት ነበረበት።

61 ለዚህም ነው ሰዎች፡ "ስለ ትናንሽ ሕፃናት፡" አንዳንድ ጊዜ፡ "ከክርስቲያን ወላጆች ያልተወለዱ ህጻናት አይድኑም፡" ይላሉ።

62 የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለልጁ ያስተሰርያል፡ በምን መንገድ እና ምን ያህል ክፉ ሆኖ ተወለደ አይገደኝም። እርሱ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው። ህጻን ንስሓ መግባት አያስፈልገውም፡ ንስሓ የሚገባበት ምክንያት የለውም፡ ይህም በክርስቶስ ደም የተወገደው የዓለም ኃጢአት ነው። ሕፃናት ወደ ገነት ይሄዳሉ።

63 የመጀመሪያው ኃጢአት ነው፡ ጥያቄ የሚነሳባትም—ለዚህ ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ታላላቅ ክስተቶች ሲነሡ፡ ከሁሉ በፊት፥ "ስለ ጋብቻ እና ፍቺስ?" አሁንም፡ እንደወትሮው፡ አሁንም በህዝቡ ዘንድ ጥያቄ ነው።

በኢየሱስ ዘመን እንደነበረው፡ በሙሴ ጊዜ እንደነበረው፡ ሁልጊዜም እንደነበረ፡ እስከ ዛሬ ድረስም፡ በሰዎች ዘንድ ጥያቄ ነው፡ ምክንያቱ ሰዎች እውነቱን ማወቅ ይፈልጋሉና።

64 ነገር ግን ጥያቄ ባለበት ቦታ፡ መልስም ሊኖር ይገባል። አሁንም መልስ በመገኘቱ፡ አስቀድሜ፡ በዚህ ሳምንት እንደተናገርኩት፡ ትክክለኛ መልስ መኖር አለበት። እና ለማንኛውም ነገር መልስ ከተሰጠን፡ መልሱም—ትክክል ካልሆነ፡ ስሕተት እንደነበረ እንረዳለን። ነገር ግን እንዲህ ነው፡ እውነትን ማወቅ ስትወድ፡ ጥያቄው እስኪመለስልህ ድረስ መጠየቅ መቀጠልህ የማይቀር ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ በመሆኑ፡ መልሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን ይገባል።

65 አስቀድሜ እንዳልኩትም፡ ዛሬ ጠዋት ወደ ምስራቅ አቅጣጫ መጓዝ ብፈልግ፡ በማውቀው በተሻለ መንገድ ሁሉ፡ በመስኩ ላይ አንዳች ነገር ለማግኘት መጣር አለብኝ፡ እና ቀጥታ ምስራቅ ሲሆን፡ ወደ ምስራቅ እጓዛለሁ። አንድ ሰው “ወንድም ብራንሃም፡ ምስራቅ **በዚህ** ነው፡” ሊለኝ ይችላል። ስለ እውነት፡ ምስራቅ ነው፡ ይሁን እንጂ ሰሜናዊ ምስራቅ ነው። ስፈልገው የነበረውን ንብረት እስተዋለሁ፥ ስሕተት እንደነበረ ስረዳ፡ እንደገና እመለሳለሁ። ከዚያም ሌላኛው ደግሞ “ወንድም ብራንሃም፡ **በዚህ** በኩል፡ በስተቀኝህ ሂድ፡” ይለኛል። አሁንም፡ ይህም ደግሞ፡ ስለ እውነት ምስራቅ ነው፡ ይሁን እንጂ ደቡባዊ ምስራቅ ነው። ስለዚህ ስፈልገው የነበረውን ንብረት አጣዋለሁ፡ ምክንያቱ ትክክለኛው እና ቀጥተኛው ድንበር አልፌ ሄጃለሁና።

66 አሁን፡ ነገሩ እንዲህ ከሆነ፡ በዚህ **በጋብቻ እና በፍቺ** ዙርያ ላይ ሁለት እሳቤዎች አሉ። ይህም ደግሞ፡ አንደኛው፡ እንዲህ ይላል፡ “አንድ ሰው ሚስቱ ካልሞተችበት በቀር፡ አንዴ ብቻ ማግባት አለበት ይላል።” እና ከጥያቄዎቹ ውስጥ አንዱ ይህ ነው፡ ነገር ግን፡ ያንን ተከትላችሁ ትሄዳላችሁ፡ ጥራዝ ነጠቅ አካሄድ ትወጣላችሁ። ከዚያም ሁለተኛው ደግሞ እንዲህ ይላል፡ “ኦህ፡ ሚስት ወይም ባል፡ አንዳቸው፡ ካመነዘሩ፡ ከሁለቱ አንዱ ተፋቶ እንደገና ማግባት ይችላል ይላሉ።” በዚህም ደግሞ ጥራዝ ነጠቅ አካሄድ ትወጣላችሁ።

67 ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ የፈለግነው ደቡባዊ ምስራቅ ወይም ሰሜናዊ ምስራቅ ሳይሆን፡ በቀጥታ ምስራቅን ነው። **በዚህ** መንገድ ስትሄድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውጪ ትወጣላችሁ፡ **በዚያ** መንገድ ብትሄዱም ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውጪ ትወጣላችሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የሚገናኙበት ስፍራ ማወቅ አለብን፡ በተጨማሪም እውነቱን መረዳት ያስፈልገናል። ሁለቱም በየመንገዳቸው ሄዱ፡ ትክክለኛውን መልስ ማምጣት ተሳናቸው፡ ይሁን እንጂ መልስ መኖሩ የማይቀር ነው።

68 ልክ፡ እንደ ዛሬ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሁለት ታላላቅ የዶክትሪን እሳቤዎች እንዳሉ፥ አንደኛው ካልቪኒዝም ሲሆን፡ ሌላኛው ደግሞ አርሜኒ-... አርመኒያኒዝም ነው። አንዳቸው ወግ አጥባቂነት ሲሆን፡ ሁለተኛው ጸጋ ነው። እንደተረዳነውም በጸጋ የሚያምኑ ሰዎች፡ ማለት ካልቪኒስቶች፡ እንግዲህ ይላሉ፡ “እግዚአብሔር ይባርክ፡ ማጨስ አይጎዳኝም። መጠጣት አይጎዳኝም። የዘላለም ደህንነት አግኝቻለሁና፡ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እችላለሁ።” ሌላኛው ወገን ላይ ደግሞ፡ ወግ አጥባቂው፡ ወገን ደግሞ፡ “ኦህ፡ ባንከባልለው

ደስ ባለኛ ነበር፡ ሌላኛው አእምሮዬን ባሳየው እመኛ ነበረ፡ ምን ዋጋ አለው፡ ክርስቲያን ነኝ፡ ዝም ማለት አለብኝ።" እያችሁ፡ እራሳችሁን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ታገኛላችሁ፡ እና እንዳቸውም ልክ አይደሉም። አሁን፡ ያንን ለማለት አስቸጋሪ ነው፡ እውነታው ግን ይህ ነው።

69 እራሳችንን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ላይ እናገኛለን፡ አንደኛው፡ በአንዱ መንገድ፡ አንደኛውም፡ በሌላ መንገድ። ስለዚህ አሁን እውነት ምን እንደሆነ እንይ።

70 አሁን አዳምጡኝ፡ እና ትርጉም የሚሰጥ ከሆነ ተመልከቱ። ለምሳሌ፡ ወደ ከአገር ለመውጣት ከተዘጋጀሁ፡ እና ቤተሰቤን እወስዳቸዋለሁ፡ ባለቤቴን ወደ እኔ እጠራትና፡ እንግዲህ "እንግዲህ እኛ-... የኔ ቆንጆ፡ እነሆ እወጣለሁ፡" እላታለሁ። አሁን ወግ አጥባቂው ወገን ይህ ነው፡ "ይኸውልሽ፡ ሚስቴ፡ አሁን ሕግ እደነግግብሻለሁ! እኔ በሄድኩ ጊዜ ከማንም ሰው ጋር ከተሽኮረመምሽ፡ በተመልሰሁ ጊዜ የተፈታሽ ሴት ነሽ። እና ዓይኖችሽ እንድታስለመልሚ አልፍገልግም፡ እንድትሽኮረመሚ አልፈልግም! ገብቶሻል? እኔ ባልሽ ነኝ! እንዲህ ካደረግሽ፡ እኔ ሰመለሰ አባርርሻለሁ።"

71 ከዚያ እሷም በተራዋ ወደ እኔ ቀርባ ከረባታዬን ትይዝና፡ እንዲህ ትለኛለች፡ "የኔ መልካም ሰው፡ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ፡ ተመልከት፡ ይኸውልህ፡ በማንኛዋም ሴት ላይ ዓይንህን ብትጥል፡ ወይም ማንንም ሴት ብታወጣ፡ ወይም ማንኛውም ሴት ብታሽኮረምም፡ ተመልሰህ ስትመጣ ፍት ትሆናለህ።" አሁን፡ ያ ደስተኛ ቤት አይሆንምን? ወግ አጥባቂ ማለት ይህ ነው። በጣም ጥሩ።

72 አሁን፡ ሌላኛው ወገን ደግሞ፡ ከቤት ርቄ ከሄድኩ በኋላ ከተሳሳትኩ... ሄጄም እንዲህ እላለሁ፡ "አሁን፡ ይኸውልህ፡ **ይህች** ሴት እወጣለሁ። ኦህ፡ ሚስቴ ምንም ችግር የለባትም፡ ምንም ግድ የላትም።" ሚስቴም፡ "**ከዚህ** ወንድ ጋር እወጣለሁ። ቢሊ ምንም ችግር የለበትም፡ ግድ የለውም።" ግድ የለኝም ከሆነ፡ በእኔ ላይ የሆነ ችግር አለ፥ ያቺን ሴት በትክክል አልወዳትም ማለት ነዋ። እሷም ግድ የሌላት ከሆነች፡ ችግር አለባት። እሷም የእኔ ሚስት ናት፥ ሌላ ሰው ከእሷ ጋር እንዲቃለድ አልፈልግም። ሚስቴ **የእኔ** ናት።

73 አሁን፡ ትክክለኛው መንገድ፡ ሁለቱም እውነት አላቸው፡ ነገር ግን ትክክለኛው እውነት አይደለም።

74 እና ነገሩን ለማረም ያክል፡ እኔ ከቤት ስርቅ፡ ትንሿ ቤተሰባችን አንድ ላይ እንሰበሰባለን፡ እና እርስ በርሳችን እንጸልያለን። ለእግዚአብሔር አደራ እሰጣቸዋለሁ፡ እነርሱም ለእግዚአብሔር አደራ ይሰጡኛል። እንዲህ ካደረግን በኋላ፡ እንወጣለን... ርቀን እንሄዳለን። እንግዲህ፡ እንደምትወደኝ አውቃለሁ፥ በሷ ላይ የራስ መተማመን አለኝ። እ-... እሷንም እወዳታለሁ፥ በእኔ ላይ በራስ መተማመን አላት። እንደዛ እስከወደድኳት ድረስ፡ ሌላ ሴት ስለማውጣቴ ምንም አትጨነቅም። እሷ በትክክል ብቻ ትውደደኝ እንጂ፡ ለምን፡ ሌላ ወንድ ከሷ ጋር ይሄዳል ብዬ መጨነቅ አያስፈልገኝም፡ ምክንያቱም ሚስቴ ናት እኔም አምናታለሁ።

75 ምናልባት ስሕተት ላይ ከወደቅኩ፡ ወጥቼ ከሌላ ሴት ጋር ከተሳሳትኩ፡ ተመልሼ፡ መጥቼ እንደምነግራት በፊቷም እንደምናዘዝ፡ አምናለሁ። "ሚዳ፡

አሰቤው አላደረግኩትም። አጋጣሚ ወጥመድ ውስጥ ገባሁ፥ አንዲት ሴት እንዲህ ተከታተለችኝ እ—እና እጄን ያዘችኝ፡ ከዚያ በኋላ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ተጀመረ፡" ትረዳኛለች ብዬ እገምታለሁ። ይቅር እንደምትለኝ እምናለሁ። ነገር ግን ስለምወዳት፡ እንዲሁ በከንቱ፡ አላደርገውም። ይቅር ብትለኝም፡ እኔ አላደርገውም። እንዲሁ በከንቱ፡ አልጎዳትም። ይቅር እንደምትለኝ ባውቅም እንኳ፡ እሷን መጉዳት ግን አልፈልግም።

76 በእግዚአብሔርም ዘንድ እንደዛ ነው። እንግዲህ ይህ... **ፊልዮ** የተባለው ፍቅር፡ ሰዋዊ የሆነው ፍቅር፡ ሕብረታዊ ፍቅር፡ አንድን ሰው ስለሚሰቱ እንዲህ ሊሰማው ካደረገ፥ **አጋፔ** የተባለው ፍቅርስ እንዴት ይሆን፡ ቃሉ በግሪክኛ "የእግዚአብሔር ፍቅር" ማለት ነው፡ ይህስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ያደርገኝ ይሆን? እኔ፡ አንድን ነገር ላደርግ ከተሰማኝ፡ ያን ለማድረግ በልቤ ውስጥ ነው! እንዲህም... ብል፡ ያን ለማድረግ በልቤ እስካለ ድረስ፡ ሄጄ አደርገዋለሁ። ወግ አጥባቂነት ግን ይህን እንዳደርግ አያደርገኝም፡ ምክንያቱም ስለ ድርጊቴ ቅጣት እንደሚያስከትልብኝ አውቃለሁ። ትክክለኛ እውነታው ግን፡ ያንን ነገር ለማድረግ **እስክትመኘው** ድረስ የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ልብህ ሲመጣ ነው። እውነታው ይህ ነው። ሁለቱ እሳቤዎችም እነዚህ ናቸው። ወግ አጥባቂነት ወይም ሌላ፡ ወይም ካልቪኒዝም ብቻ ሳይሆን፡ ሁለቱም።

77 አሁን ደግሞ፡ እንደምናውቀው ዛሬ ዛሬ፡ እጅግ የተለያዩ የእምነት ተቋማት አሉ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አለ፡ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አለ። እያንዳንዳቸው መንገድ ነን ይላሉ፡ አያችሁ፡ "መንገድ ከእኛ ጋር አለች፡ እውነት እኛ ነን ይላሉ።" ሜቶዲስቶች፡ "እውነት ከእኛ ጋር አለች፡" ይላሉ። ባፕቲስቶችም "እውነት ከእኛ ጋር አለች፡" ይላሉ።

78 እንግዲህ፡ እንደ'ኔ፡ እንደዚያ ቢሰማቸውም፡ እንደዚያ አይደሉም፡ ምክንያቱም ኢየሱስ "እውነት እኔ ነኝ፡" ብሏልና። አያችሁ?

79 ስለዚህ፡ የትላንትናው ምሽት ስብከቴ እንደ ነበር፡ እርሱ ብቻውን፡ እግዚአብሔር ስሙን ያስቀመጠበት የአምልኮ ስፍራ እርሱ ነው። ፕሮቴስታንት ስለሆንክ ክርስቲያን አይደለህም። ካቶሊክ ስለሆንክ ክርስቲያን አይደለህም። ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ወይም ጴንጤ ስለሆንክ ክርስቲያን አይደለህም። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ፡ በውኃ ሳይሆን፡ በመንፈስ ቅዱስ ስለተጠመቃችሁ ክርስቲያን ናችሁ። "አንድ እምነት፥ አንድ ጌታ፥ አንዲት ጥምቀት አለ፡" ያም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። የውኃ ጥምቀት ወደ ሕብረት ብቻ ያደርሳችኋል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደ ክርስቶስ ያደርሳችኋል። እውነት ይኸው ነው።

80 ስለ **ጋብቻ እና ፍቺ** ሁለት እሳቤዎች አሉ። እንግዲህ፡ ጌታችን በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ የቃሉ የሰባት-ማኅተም ምስጢር፡ ከፍቶልናል። አሁን፡ ለብዙዎቻችሁ፡ ይህ ለእናንተ ግሪክኛ ሊሆንባችሁ ይችላል፣ ቤተክርስቲያኔ ግን ትረዳዋለች። በምን? ስለ ራእዮቹ እና ስለተከናወኑት ነገሮች ስምታችኋል። እናም ጥያቄው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ ነው፡ እዚህ ጋር ዓለም ሳይፈጠር በፊት ተሰውረው ወደነበሩት ምስጢራት እንድናምን ተጋብዘናልና ስለዚህ ትክክለኛ መልስ መኖሩ ግድ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችም በዚህ በመጨረሻው ዘመን ምስጢራቶቹ እንደሚታወቁ አስቀድመው ተናግረዋል።

ራእይ 10፡ "የሎዶቅያ መልእክተኛ፡ ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር ይታወቃል።" የመጨረሻው ዘመንም ይህን ነው፡ ሎዶቅያ ይባላል።

81 ተመልከቱ ይህ ሁሉ ሪቫይቫል ላለፉት አስራ አምስት ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ሲንቀሳቀስ ኖሯል፡ እስከ አሁን ድረስ አንዳች የሐይማኖት ተቋም ከዚያ አልወጣም። ሉተር ሪቫይቫል ነበረው፡ ወደ ሐይማኖት ተቋምነት ገባ፥ ዌስሊ፡ የሐይማኖት ተቋም ሆነ፥ አሌክሳንደር ካምቤል፡ የሐይማኖት ተቋም ሆነ፥ እነዚህ ሁሉ ሌሎች ታላላቅ... እነ ጆን ሰሚዝ እና ሌሎችም፡ የሐይማኖት ተቋሞች፡ እነ ሙዲ፡ ሁሉም። ይኸኛው ግን... ብዙውን ጊዜ ሪቫይቫል የሚቆየው ለሦስት ዓመታት ያህል ብቻ ነው። ይሄኛው ግን ላለፉት አስራ አምስት አመታት እየቀጠለ ይገኛል፡ ከውስጡ አንድ የሐይማኖት ተቋም አልወጣም፡ ይህ የዘሩ ጊዜ ነውና። ከእንግዲህ ቅርፊት የለም፥ ቅርፊቱ ከተራገፈ በኋላ፡ ቀጥሎ ያለው ዘር ነውና።

82 እግዚአብሔር ተዘጋጅቷል፡ በዚህ ጊዜ ካላደረገው፡ በቃሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ፍጽምና ለማምጣት የሚጠራት ቤተ ክርስቲያን ያሰነሣል። ልብ በሉ፡ በሆነ ቦታ ላይ መልስ መኖሩ የማይቀር ነው፡ እና ይህ የእግዚአብሔር የሰባት ማሕተማት ምስጢር ስለሆነ፡ ሰባቱ ማሕተሞች...

83 ሰንቶቻችሁ ይሄን ትረዱታላችሁ፡ እጆቻችሁን ከፍ አድርጉ። እሰኪ እንየው። እንደሚመስለኝ በዙርያ ሁሉ ያሉ የጉባኤያችን አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም፡ ሰሙኝ። ካልተረዳችሁት፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ፡ መጻሕፍቶቹ በቅርብ ይወጣሉ። አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ፡ የተወሰኑ መጽሕፍቶች አሉን።

84 ኢየሱስ፡ በጽሑፋችን ላይ፡ ወደ እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ፡ ወደ መጀመሪያው እንድንመለስ ጋብዞናል።

85 አሁን፡ በዚህ ጥያቄ በተጋፈጡት ጊዜ፡ ሁለት የሚታዩ ነገሮች ነበሩ። ካህናቱም፡ "ሰው በሆነ ምክንያት፡ ሚስቱን ሊፈታ፡ ይችላልን?"

ኢየሱስም "ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም፡" አላቸው።

ከዚያም እንዲህ አሉ፡ "ሙሴ የፍች ጽሕፈት ፈቀደልን፡ በፈለግነው ነገር ሁሉ እንድንተዋት ፈቀደልን።"

86 አለም፡ "ሙሴ ይህን ያደረገበት ምክንያት፡" ይህችን ለተወሰነ ጊዜ አቆያታለሁ፡ "ምክንያቱ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ፥ እንጂ፡ በመጀመርያ እንደዚያ አልነበረም።" ጥያቄው!

87 የዛሬው ጥያቄ፡ የዓለም ሰላም በማን ይመጣል፡ "በፖለቲካ፡ በተባበሩት፡ በተባበሩት መንግስታት ነውን?" እኔ እላችኋለሁ፡ አይደለም። ከዚህ በፊት አልተሳካም፡ ወደፊትም አይሳካም። ለጥያቄው ግን ትክክለኛ መልስ አለ፡ "በምድር ላይ ሰላም ይሆናልን?" አዎን፡ ኃጢአት ከምድር ላይ ሲወገድ፡ ሰላም ይሆናል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን፡ ሰላም አይኖርም፡ "ሕዝብ በሕዝብ ላይ፡ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል።" እግዚአብሔር የኃጢአት መድኃኒት ሰጠ። አሁን በደንብ አዳምጡ። ኃጢአትን ከምድር ላይ ለማሰወገድ እግዚአብሔር መድኃኒቱን ሰጥቷል፡ የምድር ሰው ግን የእግዚአብሔርን መድኃኒት አልተቀበለውም።

88 እግዚአብሔር አምላክ ሚስቶቻችንን እግብተን ከእነርሱ ጋር የምንኖርበትን መንገድ እና መድኃኒትን ሰጠን፡ ሰው ግን የእግዚአብሔርን መድኃኒት አልተቀበለም፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ቃሉን አይቀበልም። ኢየሱስ ይህን ተናገረ። ይህም ከቃሉ እንደተናገረ—ያስታውሰናል፡ የተናገረው እናውቃለንና፦ “ሰማያትና ምድር ያልፋሉ፡ ያልፋሉ፡ የእኔ ግን አያልፍም።”

89 ጥያቄው፡ ኢየሱስ እንድንመለስ የሚፈልገን ወደ እውነተኛው መልስ፡ ወደ መጀመሪያው በመመለስ ነው። ያም ደግሞ፡ ወደ ዘፍጥረት ነው፡ ምክንያቱም **ዘፍጥረት** የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ ጥያቄ የዘር ምዕራፍ ነው። እና በእርሻው ውስጥ ምን ዓይነት ዘር እንዳለ ለማየት ሰብላችሁ ምን አይነት እንደሆነ ለማወቅ፡ ሁልጊዜ ወደ ዘሩ መመለስ አለባችሁ። አሁን፡ ምን አይነት ዘር ተዘራ? ዘፍጥረት፡ የዘር ምዕራፍ በመሆኑ፡ ወደ ዘፍጥረት እንመለስ። ኢየሱስ “በመጀመሪያ፡” በማለት ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስተዋወቀን። አሁን፡ ልብ በሉ፡ በመሰረቱም የጊዜ መጀመሪያ ያኔ ነው። ከዚያ በፊት፡ ዘላለማዊነት ነበር። አሁን፡ ጥያቄአችን ላይ፡ ልብ በሉ፡ ወደ መጀመሪያ ከተመለስን።

90 ይህ እንዳያልፋችሁ! ቀስ ብዬ መናገር የምፈልገውም ለዚህ ነው፡ በስልክ መስመር ውስጥ ስላሉ ሰዎች፡ ቅጂውም በትክክል እንዲናገረው ስለፈለግኩት ነው።

91 ኢየሱስ “ወደ መጀመሪያው ተመለሱ፡” ብሎ ከተናገረን፡ በምድር ላይ የነበረው ጥንድ ጥንድ አንድ አንድ ብቻ ነው። አንድ አዳም፡ አንድ ሔዋን ነበሩ፡ እግዚአብሔር ብቻ ከእነርሱ ጋር ነበረ። አንዲት ሴት ፈረስ፡ አንድ ወንድ፥ አንዲት ሴት በቀቀን፡ አንድ ወንድ። “በመጀመሪያ፡” ወደ ኋላ እንድንመለስ እንደነገረን፡ ሁሉም ነገር አንድ አንድ ጥንድ ብቻ ነበር። ልክ ነው? ስለዚህ፡ “በመጀመሪያው” እያንዳንዱ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ በፍጹም ሥርዓት እና በመስማማት ይሄድ ነበር፡ ከተሰመረው ውጪ የሆነ አንድም አልነበረም።

92 በሰማይ ያለው ሁሉ አሁንም በሥርዓት ነው፡ ከዋክብት፡ ጋላክሲዎች፡ የፀሐይ ስርዓት፡ ሁሉም ነገር በሥርዓት ነው። ከመካከላቸው አንዱ ቢዛነፍ፡ ሙሉውን ፕሮግራም ያደናቅፋል።

93 አሁን አዳምጡ። ይታያችኋል? አንዲት መዛነፍ ሙሉውን ፕሮግራም ያበላሻል! እንግዲህ፡ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር፡ ከአንድ ወንድና ከአንዲት ሴት በማይቋረጥ ኪዳን ሲኖር ሳለ፡ ይህች ሴት ኃጢአት ሠርታ ሁሉንም ምድራዊ ፕሮግራም በእግዚአብሔር ዘንድ ኪዳኑ እንዲቆራረጥ አደረገች። ስለዚህም፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ አንዳች ቃል መጨመር፡ ወይም አንዳች ቃል መቀነስ ክርስቲያንን ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን እንዳይኖረው ይዳርጋል፡ ቤተ ክርስቲያንን ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን እንዳይኖራት ይዳርጋል፡ ቤተሰብን ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን እንዳይኖራቸው ይዳርጋል። የእግዚአብሔርን ቃል ባለመቀበል፡ እያንዳንዱ አማኝ ወደ ውጭ ሊጣል ይችላል።

94 ስለዚህ፡ ያን ውድ ቤተሰብ እንዲለያዩ ያደረገችው ሴትዮዋ ነች። ምድርን የረበሸው ኪሩቤል አልነበረም። ቤቱን የጣለው አዳም አልነበረም። ቤቱን የጣለው እና ኪዳኑ እንዲሰበር የዳረገው፡ ሌላ ነገር ሳይሆን፡ ሴትዋ፡ ሄዋን ናት። ስለዚህ “መጀመርያው፡” በማለት ኢየሱስ የተናገረው፡ የተሰበረው እዚህ

ጋር ነበር። ኢየሱስም “በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ ዓይነት፡ አንድ ወንድ፡ አንዲት ሴት አደረገ፡” አለ። እና አሁን ይህች ሴት... የፈረሰ ሴት ሳይሆን፡ የአሳማ ሴት ሳትሆን፡ ሴቲቱ፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ በኪዳን የሚሰራውን ነገር ሰብራ፡ ሁሉንም ነገር ወደ ሞት ጣለችው። ወንዱ ሳይሆን፡ ሴቲቱ፡ ቃል ኪዳኑን አፈረሰች። ቃል ኪዳኑን አፈረሰች፡ ምክንያቱም (ለምን? ) የእግዚአብሔርን ቃል ድንበር አልፋ ረግጣለች። ይህ ማለት፡ ከባልዋ ጋር የገባችውን ቃል ኪዳን ካፈረሰች፡ ከእግዚአብሔር ጋር የገባችውን ቃል ኪዳን አፍርሳለች፥ ሰለዚህ፡ ከእግዚአብሔር ጋር የገባችውን ቃል ኪዳን ሰላፈረሰች፡ ከባልዋ ጋርም አፈረሰች።

95 ለእግዚአብሔር የገባችሁት ቃል የገባችሁት ቃል ኪዳን ስታፈርሱ፡ ብዙ ሕገወጥ የቤተ ክርስቲያን አባላትን የሚያሰከትለው ይህ ነው፡ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ተሰብሰበው “እንግዲህ፡ **ያንን** ለማለት ፈልጎ አይደለም፡” ይላሉና፡ ይህም መላውን ድርጅት ከቃሉ ኪዳን ያሰወግደዋል። “እኛ ያንን አናምንም። ዶክተር ጆንስ አይደለም ብሏልና።” ግን እግዚአብሔር እንዲህ ነው እሰካለ ድረሰ፡ እንዲህ አለ፡ “የሰው ቃል ሁሉ ውሸት ይሁን፡ የኔም እውነት ይሁን!” በዚህ ምክንያት የማይለወጥ ኪዳኑን ያፈርሳል።

96 አሁን እያየን ነው፡ ኪዳኑ ፈርሷል፡ ያኔ የህይወት መሰመር ተቋርጧል፡ እንዲሁም የጊዜ መሰመር ተሰብሯል፡ ቃል ኪዳኑ ፈርሷል፡ ሁሉም ነገር ፈራርሷል! ምክንያቱ ማን ነው? ሴት። ቃል ኪዳኑን ያፈረሰው ይህ ነው። አሁን፡ ያንን ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ ከዘፍጥረት 3 ላይ፡ ማንበብ ትችላላችሁ።

97 እንግዲህ፡ ያን ጊዜ ሰው በእግዚአብሔር ቃል፡ በሴቲቱ ላይ እንዲገዛ ተደረገ። ከእንግዲህ ከሱ ጋር መተካከል-አልቻለችም። እንደምታውቁት፡ ከተፈጥሮ ጋር የምትተካከል-ነበረች፥ የእግዚአብሔርን ቃል በተላለፈች ጊዜ፡ ግን፡ እግዚአብሔር ሰውዬውን በእሷ ላይ ገዥ አደረገው። ማሰታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ ዘፍጥረት 3፡16። ከእንግዲህ ውዲያ ከወንዱ ጋር የተተካከለች አልሆነችም። የእግዚአብሔርን ቃል ተላላፊ ነበረች።

98 አይታያችሁም ወይ፡ “እሷ፡” እሷ፡ ቤተክርስቲያኒቱ? የእግዚአብሔር ቃል ተላላፊዋ፡ ከኪዳኑ ውጪ እንድትሆን አደረጋት። ቤተክርስቲያኒቱ የፈጸመችው ነገር ይህ ነው፡ በሁሉም ነገር ላይ መንፈሳዊ ሞት ጣለችበት። አሁን በዚህ መልኩ በእነዚህ ነገሮች ላይ ለምን እንደምቀጠቅጥ አሁን ይገባችኋል። እውነት ነው! የመጽሐፍ ቅዱሰ እውነታዎች ናቸው።

99 አሰተውሉ፡ ለምን እንዲህ ያለ ነገር አደረገች? ያቺ ቆንጆ፡ ውብ፡ ፍጹም ሴት እንዴት ሊሆን ይችላል... ?

100 አንድ ጊዜ ሠዓሊ የሣለው፡ የሔዋንን ሥዕል አየሁ፡ በግሪክ ይመሰለኛል። ከዚህ ቀደም ካያችሁት አሰፈሪ ነገር ሁሉ እጅግ የሚያሰፈራ-መልክ ነበራት። ይህ የሚያሳየው ሥጋዊ አእምሮ ምን እንደሚመለከት ነው። እሷ ግን፡ አሰፈሪ አልነበረችም፥ ቆንጆ ነበረች፡ ምክንያቱ ፍጹም ሴት፡ ሙሉ ሴት ነበረች።

101 ልብ በሉ፡ በዚህ መልክ ሰትኖር ሳለች፡ ለምን እንዲህ ያለ ነገር አደረገች? እሷ ከሰው ጋር ትክክል ነበረች፡ ከውንዱ ጋር የተተካከለች—ነበረች። ነገር ግን ኃጢአትን በሠራች ጊዜ፡ ከወንዱ ጋር መተካከል-እንዳጣች ሁላችንም

እናውቃለን፡ እግዚአብሄርም አለ፦ “ከእንግዲህ ወዲህ ወንዱ ገዢህ ይሆናል።” አሁን፡ ይህ መንጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከፈለጋችሁ፡ ልናነበው እንችላለን።

102 የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እየሰጠኋችሁ ነው፡ በሰልክ መሰመር ውስጥ ከመላ አገሪቱ እየተከታተሉ ላሉ ሁሉ ጊዜ ለመቆጠብ፡ በራሳችሁ ጊዜ እንድታነቡ በማሰብ ነው።

103 ይህን ያደረገችበትን ምክንያት ልብ በሉ። ሰይጣን እንዴት ወደ እሷ ቀረበ?

104 በሆነ ወቅት ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር የሚተካከል-እንደነበረ ታውቃላችሁ? ፈጣሪ ከመሆን በቀር፡ በሁሉ በትክክል ነበረ፡ በሰማያት፡ በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቆም፡ ሁሉ ነገር ነበረ፡ ታላቁ መሪ ኪሩቤል ነበረ።

105 ልብ በሉ ይህንን ያደረገችበትን ምክንያት፡ በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ ስላልነበረች ነው። በእግዚአብሔር የመጀመሪያ ፍጥረት ውስጥ አልነበረችም፡ ተረፈ-አካል ነበረች። ስለዚህ፡ “በመጀመሪያ፡” ኢየሱስ እንደገለጸው፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ከተፈጠሩት የመጀመሪያ አይደለችም። ኢየሱስ “በመጀመሪያ” ባለው መሰረት፡ ከሰው የተገኘች ተረፈ-አካል ናት።

106 አስታውሱ፡ በመጀመሪያ ፍጥረት ላይ፡ አዳም ሴት እና ወንድ ሆኖ፡ አንድ ነበረ፡ በኋላ ግን በጎድን አጥንት ተለየ።

107 አስተውሉ፡ እና፡ ከእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ብቸኛዋ፡ ተለይታ በተረፈ-አካል ናት፡ እና ሌላው እንስሳ እና ሌላው በሙሉ፡ ተመልከቱ፡ በዚህ መንገድ የተነደፈችው ብቸኛዋ እሷ ነበረች። ሌሎች ሴቶች ሁሉም በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ ነበሩ። ሌሎች ሴቶች በሙሉ በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ ነበሩ፡ ሔዋን ግን በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ አልነበረችም። አያችሁ፡ ያን እንደዚያ መሆን ነበረበት። ከአፍታ በኋላ እንገባበታለን። በዚህ ፍጥረት ውስጥ፡ እሷ በዋነኛነት ሳይሆን፡ በተረፈ-አካል ውስጥ እንደነበረች፡ ልብ በሉ። በዚህ ፍጥረት ውስጥም፡ ይህ ነገር…

108 አሁን ስሜታችሁን መጉዳት አልፈልግም፡ እውነቱን ግን መናገር እፈልጋለሁ። እና ዝም ብላችሁ ተቀመጡ፥ መልካም አድርጋችኋል።

109 እንደ ሴት አታላይ ሆኖ የተነደፈ ንድፍ ሌላ የለም፡ ሴት አማላይ ናትና። ሌላ ምንም ነገር ሊኖር አይችልም፥ እንደዚያ እንዲሆን የተደረገ ነገር የለም።

110 በተጨማሪም፡ እንደ ሴት በቀላሉ ሊታለል የሚችል ምንም ነገር የለም። አሁን፡ ውድቀቱ ራሱ፡ የመጀመሪያው ውድቀት ራሱ ይህ አባባል እውነት መሆኑን ያረጋግጣል።

111 በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ አልነበረችም። በመጀመሪያ፡ በአዳም ውስጥ ነበረች፡ ራሷን ችላ፡ በሴት ጾታ ግን አይደለችም። የተሰራች ተረፈ-አካል ነበረች።

112 አሁን፡ እንደ ሴት በቀላሉ የሚታለል፡ እንዲሁም እንዲያታልል ተደርጎ የተነደፈ፡ አንዳች ነገር የለም። እንደ ሴት ዝቅ ብሎ መውረድ እስኪችል ድረስ ተደርጎ የተነደፈ ሌላ ነገር የለም። አሁን አስቡት። በፍጥረት ሁሉ ውስጥ፡ አንዲት ሴት ዝቅ የምትለውን ያህል፡ መውረድ የሚችል ምንም ነገር የለም። በዓለም ላይ ካሉት ከማንኛውም ነገሮች ይልቅ የወንዱን ልብ በቀላሉ ልትሰብረው የምትችለው፡ ሚስቱ ናት። ያቺ ቆንጆ ሚስት ከሌላ ወንድ ጋር ትሂድ

በሉና፡ ከዚያ በኋላ ልጆቹን ይዞ በዚያ ቁጭ ያለውን ሰውዬ፡ እንባው ከዓይኖቹ የሚፈስውን ተመልከቱ። የተነደፈችው በዚያ መንገድ ነው። ይህንን ለማድረግ የተነደፈች ነች። እንደ እሷ ሆኖ፡ ወይም እንደሷ መርከስ የሚችል ተደርጎ የተነደፈ ውሻ፡ ወይም አሳማ፡ ወይም ሌላ እንስሳ የለም። አሁን፡ ይህ እውነት ነው።

እህቶቼን በተመለከተ፡ እንድትነቁ እፈልጋችኋለሁ።

113 የትኛውም እንስሳ ስነ ምግባር ሊጎድለው አይችልም። ውሻዋን፡ ሴትዋን ውሻ "ከሁሉም ጋር የምትተኛ" ትሏታላችሁ፡ ወንዱንም... ሴትዋ አሳማ "ባለጌ" ትሏታላችሁ፡ ስነ ምግባሯ ግን ከብዙዎቹ የሆሊውድ ኮከቦች በላይ ሚሊዮን ማይልስ የራቀ ነው። ይሄን ያህል ዝቅ እንድትል ተደርጋ የተነደፈች ናት። አትችልም... ይህን አሁን አስቡት። በዓለም ውስጥ፡ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ ከተሰሩት፡ ሥነ ምግባር የጎደለው፡ ያን ያህል ዝቅ ብሎ የሚወርድ ምንም ነገር የለም።

114 እናንተም "ቆይ እንዴ ቆይ፡ 'ወንድ'!" ትላላችሁ፡ ወደዚያ እየገባን ነው። "እሺ" ማለት የምትችለው ሴቲቱ ናትና።

115 አስተውሉ፡ እንደ ሴት ዝቅ እንዲል፡ ወይም እንዲቆሽሽ ተደርጎ፡ የተነደፈ ሌላ ማንም የለም። ውሻ እንዲህ አትሆንም፡ አሳማ እንዲህ አትሆንም፡ ወፍ እንዲህ አትሆንም። ሥነ ምግባር የጎደለው እንስሳ የለም፡ ሊሆንም አይችልም፡ እንደዚያ እንዲሆን አልተነደፈምና። ሴት አሳማ ሥነ ምግባር የጎደላት ልትሆን አትችልም፡ ሴት ውሻ ሥነ ምግባር የጎደላት ልትሆን አትችልም፡ ሴት ወፍ ሥነ ምግባር የጎደላት ልትሆን አትችልም። እንዲህ ልትሆን የምትችለው ሴቲቱ ብቻ ናት።

116 አሁን ሰይጣን ወደማን እንደ ሄደ አይታችኋል? አያችሁ? ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ይህ አላት፡ "እሺ" ወይም "እምቢ" የማለት ስልጣን አላት። አያችሁ፡ እራሷ መሆን በምትፈልገው መንገድ ይሆናል። አያችሁ? አሁን እዚህ ላይ የእባቡን ዘር፡ የት እንደገባ በግልጽ ማየት እንችላለን። የሚሄድበት አንድ ቦታ ብቻ አለው። ይህ ነገር በደንብ ካላብራራው፡ የታወረ ሰው አለ ማለት ነው። አያችሁ? አያችሁ፡ ወደሷ መሄድ ነበረበት።

117 ልብ በሉ፡ እንስሶች፡ ሴት እንስሶች ያን ማድረግ የማይችሉበት ምክንያት፡ በመጀመሪያው ፍጥረት ስለነበሩ ነው። ሴቲቱ ግን በዚያ በመጀመሪያ ፍጥረት ውስጥ አልነበረችም። አሁን ይህንን ለመቆፈር ወደ ኋላ እንመለሳለን፡ ከዚያም ወደ ዘመናዊው ዘመን፡ ወደ ኪዳኑ እናመጣዋለን።

118 የረከሰ እና የቆሸሸ አኗኗር እንድትችል የተነደፈች፡ ብቸኛዋ፡ እሷ ናት። ውሻ እንደዚያ አትኖርም፡ ሌሎች እንስቶችም አይኖሩም። ይህን የምትችለው ሴቲቱ ብቻ ናት። ውሻ ወይም ሌሎች እንስሶች፡ በዓመት አንድ ጊዜ፡ ብቻ ይፈጽማሉ፡ ያውም ለጾታዊ ደስታ ሳይሆን፡ ልጆች ለመውለድ ነው። ምስኪኗ አሳማ፡ ምስኪኗ ውሻ፡ በዓመት አንዴ፡ አንዴ ብቻ፡ ያውም ስለ ልጆቿ ነው። ሴት ግን በማንኛውም ጊዜ ባማራት ቁጥር እንዲሁ እንድትሆን የተነደፈች ናት። አሁን አንዳንድ ያለፍኳቸው ነገሮችም ይዣለሁ፥ የቀረውን መገመት ትችላላችሁ። ውሻ አትችልም፥ ሴቲቱ ትችላለች። ሌሎች ያለፍኳቸው ነገሮች መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንዲገልጥላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

119 ከወንድ ይልቅ ውብ እንድትሆን ተደርጋ የተሰራችው፡ ብቸኛ ዝርያ፡ ብቸኛዋ የእንስት ዝርያ እሷ ናት። በማናቸውም ዝርያዎች ሌላ እንደሷ የለም። በሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ ቆንጆው ወንዱ ነው፡ ለምሳሌ በእንስሳት፡ በአእዋፋት፡ እና በመሳሰሉት፡ ወንዱ ሁልጊዜ ቆንጆ ነው።

120 ወንዱን አጋዘን፡ ታላላቅ ግሩም ቀንዶች፡ ታላቅ ዝርያ፥ እና ምስኪኗ፡ ትንሿ ሴት አጋዘን ተመልከቷቸው። አውራ ዶሮውን ከነ ውብ ላባዎቹ፥ እና ምስኪኗ፡ ቡናማ ዶሮ ተመልከቷቸው። ወፎቹን፡ አውራ ዶሮንና ዶሮን ተመልከቷቸው። ለምን? ከሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረታት፡ ለምን እንዲህ ሆነች? በሁሉም ፍጥረታት ዘንድ፡ ቀንጆው ወንዱ ነው። በበጎች መካከል፡ በ—አሳማዎች መካከል፡ በፈረሶች መካከል፡ በሌሎች በማንኛውም መካከል፡ በወፎችም ዘንድ ጭምር፡ ትልቁ ወንዱ ቆንጆ ነው።

121 በሰው ልጅ ዝርያ ውስጥ ግን፡ ቁንጅና፡ በወንዱ ሳይሆን በሴቷ ነው። እሱ ከሆነ ግን፡ ችግር አለ፡ በሆነ መንገድ ላይ የዘር—መዳቀል አለ። ከመጀምሪያው ግን እንደዚያ ነው። ለምን? ለምን ሆነ? ለማታለያ። ንድፍ አውጪዋ፡ ሰይጣን፡ በዚህ በመጨረሻ ዘመን፡ ሳይቀር፡ እየሰራባት ይገኛል።

122 እዚህ ላይ ለአፍታ ብቻ ቆም ላርገው። "ቁንጅና!" በመጀመሪያ፡ በአለምአቀፍ ደረጃ፡ በነበረው፡ የዓለም፡ ወይም ዓለም አቀፋዊ ውድመት፡ ምክንያቱ በቆንጆ ሴቶች ምክንያት እንደነበረ ታውቃላችሁ? "የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች መልከ መልካም ሆነው ባዩ ጊዜ፡ ሴቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።" ልክ ነው?

123 በዚህ ዘመንስ የሴቶች ውበት መጨመሩን አስተውላችኋል? በአገር ደረጃ በጣም ቆንጆ ሴት የተባለችውን የፐርል ኦብራይን ምስል፡ በአንድ ወቅት፡ አይቼው አውቃለሁ። ቁንጅና ከተባለ ግን፡ በዚህ ሰዓት በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ እሷን በቁንጅና-የማትበልጣት ወጣት-ሴት የለችም።

124 የሴቶች ውበት መጨመር የማታለል ጊዜን መሆኑን ያሳያል። መቼ ነው ቤተ ክርስቲያን ከዛሬ በፊት የበለጠ ቆንጆ የመሰለችው? ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ተሰርቷል፡ ጥሩ ጥሩ ሕንፃዎች፡ እና **በዚህ** ሚሊዮኖች **በዚያም** ሚልዮኖች ሆነዋል። አይታያችሁም ወይ፡ "እሷ፡" ማታለያዋ!

125 አሁን፡ እንደሷ ወርዶ የሚረክስ የለም፡ እናም ደግሞ አታላይ እንድትሆን እንዲሁ የተነደፈች ነች። ሰይጣንም ዛሬ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ በእሷ ላይ እየሠራባት ይገኛል፡ ምክንያቱም ንድፍ አውጪዋ እሱ ነው። ያንን አሁን ማረጋገጥ እችላለሁ። ወደ መጀመርያው ተመልሰን፡ በእሷ ላይ መሥራት የጀመረው፡ አዳም ነው ወይስ ሰይጣን፡ እግዚአብሔር ነው ወይስ ሰይጣን? አያችሁ፡ ንድፍ አውጪዋ እሱ ነው። ሰውን ወደ ቆሻሻዋ ለመጣል ዋናው መሳሪያዋ ነው፡ ቆንጆ ሴት በመሆኗ፡ ወንድን በፈለገችበት መንገድ ማወዛወዝ ትችላለች። ወንድሜ፡ ሰውን የሚያጠምዱት የመሸታ ቤት ሴቶች አይደሉም፥ ግማሽ ልብስ ለብሳ፡ በጎዳናው ላይ እየተውረገረገች የምትራመደው፡ ቆንጆዋ ሴት ናት። ነገሩ ያለው በዚያ ነው... አታላዩ ያለው በዚያ ነው። እና ይህን ይዛ እጅግ መርዛማ፡ ፍጹም መርዛማ ናት። እንግዲህ ሰይጣን ንድፍ አውጪዋ ስለመሆኑ እናንተ ልትጠይቁኝ ትችላላችሁ፡ እውነታው ግን ያ ነው። የነደፋት ሰይጣን ነው። አሁን እየቀጠለ ይገኛል።

126 ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነገር ላሳያችሁ። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ልመልሳችሁ፡ እናንተም ዛሬ እንዲያችሁት አሳብ ስጡበት።

127 እንደዚህ አይነት ውበት ያለው ሰይጣን ራሱ ነው። ካስተዋልን፡ በመንግሥተ ሰማያት ካሉት መላእክት ሁሉ እጅግ ያማረ እሱ ነበር። ልክ ነው? እርሱም መንግሥተ ሰማያትንም ከሚካኤል መንግሥት ይልቅ የተሻለች ውብ ቦታ ሊያደርጋት ፈለገ። ልክ ነው? በተጨማሪም፡ ቃየን ልጁ መሆኑን ለማሳየት፡ የበለጠ የሚያምር መስዋዕት አቀረበ፡ መሠዊያዎቹን በፍራፍሬና በአበቦች ያጌጣቸው፡ ወዘተ። ልክ ነው? ውብ! ዛሬ ውበት የምንለው ኃጢአት፡ ውብ ነው። ኃጢአት ደግሞ፡ በውበት እያታለለ ይገኛል። በመንገድ ላይ የምትሄድ ሴት አይተህ በልቧ ውሰጥ ያለውን መናገር አትችሉም። አያችሁ? እነዚህን ነገሮች ለማለት የፈለግኩት ግን ሰይጣን ንድፍ አውጪዋ የሆነው ለምን እንደሆነ እንድታዩት ነው። ይህ በትክክል እውነት ነው፡ የገዛ ልጁ፡ ቃየን አረጋግጦታል። አሁን፡ ውብ የሆነችው ማታለል እንድትችል ነው።

128 ዓለም ቆንጆ የሆነችው ለማታለል ነው። ማለቴ **ኮሰሞስ፡** የዓለም ሰርዓት ማለቴ ነው። ምርጥ የቅንጦት ትላልቅ ቦታዎች፡ ለማታለል እንዲችሉ ውብ ናቸው።

129 ነቢዩ አሞጽ መጥቶ፡ ወደ ከተማይቱ በተመለከተ ጊዜ፡ አሰታውሱት፡ እና እንደ ዘመናዊ ሆሊዉድ አያት፡ ትናንሽ አይኖቹ በፊቱ ከተንጠለጠለው ሽበታም ጽጉሩ ሰር፡ አጠበባቸው። መልእክትን ይዞ ወደዚያ ወረደ፡ በዚያ ሰፍራም ዘረገፈው። አላቸውም፡ “እናገለግለዋለን የምትሉት አምላክ፡ ያጠፋችኋል!” በትክክል።

130 ኃጢአት፡ ውብ ነው። ይሁዳን በምናባቸው ሲሰሉት ሰክሮ በጎዳና ላይ የሚንገዳገድ፡ አፉ ላይ ዝንቦች የወረሩት፡ እና ይሁዳ፡ እንዲሁ አይነት ይመስላቸዋል። ይሁዳ ቆንጆ፡ ጠንካራ፡ እና አታላይ ነበረ። ከአንተ ለመለመን የሚመጣ ሰው አይደለም፡ ሚሰትህን ለማየት (እንደ ሽመገለ ገበሬ) ቱታ ለብሶ የሚመጣ፡ ዓይነት ሰው አይደለም፥ ሙልጭልጭ ያለ፡ ሸፍታ ነው።

131 ኃጢአት በዓለም ዓይን ውብ ነው፡ ሰለ እግዚአብሔር ውበት ግን በዚህ መንገድ ተተንትኖ አያውቅም። ይህን ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር የሚታወቀው በባህርይ፡ በውብ ባህርይ ነው።

132 ቃሉን መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ኢሳይያሰ 53 አለ። ጎን ለጎን የተጻፉ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ይዟል። ትንቢተ ኢሳያሰ 53፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ሰለ ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡ “እንፈልገው ዘንድ ደም ግባት አልነበረውም። ፊታችንም ሰወርንበት።” ልክ ነው? ደም ግባት ሰላልነበረው፡ አልፈለግነውም። ምናልባት አንድ ምሰኪን ሰው የነበረ ሊሆን ይችላል፡ ከትከሻው ጎበጥ-ያለ፡ መልከ-ጥፉ፡ መሪ እንዲሆናችሁ የማትመኙት ዓይነት ነበር። መሪ አይመሰልም ነበር። ማንም ሰው እንደሚያደርገው፡ እንደ ሰው፡ ጎዳና-ላይ ከተራ ሰዎች ጋር የሚነጋገር፡ ዓይነት ነበረ፡ ሰለዚህም ታላቅ ምሁር፡ የተማረ፡ ኩሩ፡ የተጎናጸፈ፡ እና ሁሉም ነገር የሆነ አይመሰልም። ተራ ሰው ነበር። “እንፈልገው ዘንድ፡ ደም ግባት አልነበረውም።” በሰዎች መካከል ይገባል፡ ይወጣል፡ እሱ ማን እንደሆነ እንኳ አያውቁም ነበር። እኛ አምላክ ነው

ብለን እንደምናስበው፡ ሲገባ ሲወጣ አምላክ አይመስልም ነበር። ነገር ግን፡ እሱ ራሱ፡ እንዲሁ ነበር!

133 ጌታ እግዚአብሄር ሳሙኤልን—በተናገረው ጊዜ ልብ ብላችኋል፡ "ወደ እሴይ ቤት ውጣና፡ በሳኦል ምትክ፡ ከልጆቹ አንዱን ንጉሥ አድርገህ ቅባው"?

134 አሁን፡ ሳሙኤል በትክክል ተው ብሏቸው ሳለ፡ ህዝቡ ሳኦልን እንዲሁ መረጡ። "እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ነውና፡ ንጉሥ እንድታነግሱ አይፈልግም፡" አላቸው። እንዲህም አላቸው፡ "በጌታ ስም ነግሬአችሁ፡ ሳይፈጸም የቀረ፡ አንዳች አለን? ለኑሮዬ ገንዘብ ወይም **ሌላ ነገር**፡ ለምኜአችሁ አውቃለሁ? "

135 አሉትም፡ "አይ፡ ገንዘብ ለምነህ አታውቅም። በጌታ ስም፡ የተናገርከን ሁሉ፡ ሳይፈጸም የቀረም የለም። እኛ ግን ምንም ይሁን፡ ንጉሥ እንፈልጋለን፡" ሳኦልንም መረጡት። ዓለም የመረጠውን ተመልከቱ! እስራኤል የመረጠውን ተመልከቱ! በእግዚአብሔር የቀባው፡ እስራኤል፡ በአገሪቱ ካሉ ሰዎች ይልቅ ራስና ትከሻው ከፍ ያለውን ሰው መረጡ፥ ታላቅ፡ ግዙፍ፡ ኩሩ፡ ውብ-የሆነ ወጣት መረጡ፡ እሱ ግን ሁልጊዜ በዘይት ውስጥ እንደገባ ዝንብ ነበር።

136 እግዚአብሔር ግን "እንደ ራሴ አመራረጥ ንጉሥ እመርጥላችኋለው፡" አላቸው። ስለዚህም "ሳሙኤል ሆይ፡ ማን እንደሆነ አልነግርህም፡ አንተ ግን ወደዚያ ውጣ። ከእሴይ ልጆች መካከል አንዱ ነውና፡" አለው።

137 እሴይ፡ እና ሚስቱም፡ ሌሎቹም ሁሉ አይተው፡ እንዲህ አሉ፡ "አዎን፡ ትልቁ ልጃችን፡ እሱ ታላቅ፡ ረዥም፡ ቆንጆ ሰው ነው፡ ለንጉሥ ዘውድ በትክክል ይመጥናል። ብልህ ነው። የተማረ ነው። ኩሩ ሰው ነው። ትክክለኛ ሰው እንደሆነ አውቃለሁ። ሲናገር በትክክል ይናገራል።"

138 ባመጡትም ጊዜ፡ ሳሙኤል የዘይቱን ማሰሮ ይዞ ወደ እርሱ ሄደ። "አይደለም፡ ጌታ አልመረጠውም፡" አለ። ስለዚህ እንደዚያ እያደረገ፡ ሰድስት ልጆች ድረስ ወረደ፡ ጌታ ግን ሁሉንም አልመረጣቸውም። እርሱም "ሌላ የለምን፡" በማለት ጠየቀ?

139 "ኦህ፡" አለው፡ "አዎን፡ አንድ አለ፡ በጎቹን እየጠበቀ ነው። ይሄኔ ተቀምጦ መዝሙር እየተጫወተ፡ እና እየዘመረ፡ እና እየጮኸ፡ እና ሌላም እያደረገ ይሆናል። እሱ ግን፡ ትንሽና ከትከሻው-ጎበጥ ያለ፡ ባለ ተራ-መልክ፡ ለመንግሰት ፈጽሞ የማይመች ነው።"

140 አለውም "ሂድና እሱን አምጣው፡" አለው። ዳዊትም በነቢዩ ፊት በመጣ ጊዜ፡ ነብዩም ፈጥኖ ዘይቱን በራሱ ላይ አፈሰሰውና፡ "ይህ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነው፡" አላቸው። ውበት ሳይሆን፡ ባህርይ። እግዚአብሔር የሚያየው ባህርይ ነው።

141 ሰው የተፈጥሮ ውበትን ይመለከታል። እሱም ያታልላል። ለሴት ያንን ውበት የተሰጣትም፡ ለማታለል፡ ለማታለያ ነው። ቆንጆ ሴት፡ በትክክለኛው መንገድ ካልተጠቀመችበት፡ ለእሷ እርግማን ነው፥ እኔ ከማውቀው ከማንኛውም ነገር በበለጠ ፍጥነት ወደ ገሃነም ይሸኛታል። እንግዲህ... ውብ ከሆነች፡ እና፡ ትክክለኛውን ነገር እያደረገች ከባልዋ ጋር ከጸናች፡ እንግዲህ ይህ—መልካም እና ያማረ ነው። ነገር ግን ያንኑ ነገር ተጠቅማ፡ አቤት፡ በሱም ማታለል ትችላለች፡ ይህን ለማድረግ ተሰጥቷታልና።

142 ልብ በሉ፡ አሁን፡ እግዚአብሔር ግን የሚታወቀው በባህርይ ነው። "ኢየሱስ እሱን የምንፈልግበት ደም ግባት አልነበረውም፡" በምድር ላይ ግን፡ እንደ እርሱ ያለ ባህርይ ያለው ሌላ አልነበረም።

143 አሁን፡ ዛሬ፡ የ—የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ፡ የሰይጣንና የቡድኑ አይተነዋል፡ ትልልቅ፡ የሚያማምሩ አብያተ ክርስቲያናትን፡ የሚያማምሩ ነገሮችን ይከተላሉ። ዛሬ አለም የሚመለከተው ያንን ነው። "ኦህ፡ ጊዜው የፓስተር እንትና፡ ታላቁ **እከሌ-እና-እከሌ** ጊዜ ነው፡ **እከሌ-እና-እከሊት፡** ትክክለኛ እና፡ እግዚአብሄር መሳይ ቄስ ነው፡ ታላላቅ መጎናጸፊያዎች፡ እና የመሳሰሉ ነገሮች ይደርባል።" ውበት የሚሉት ያንን ነው።

144 እውነተኛዎቹ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ግን የተረጋገጠውን የቃሉን ባሕርይ ይፈልጋሉ።

145 በዚያ ዘመን ቅዱሳን ኢየሱስን ባዩ ጊዜ፡ ያደረጉት ይህንኑ ነው። እሱ የሚታይ ነገር አልነበረውም፡ እግዚአብሔር በእሱ ውስጥ እንዳለ ግን አዩ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ አይተዋል።

146 እነዚያም እንደነ፡ ኢዮአብ እና ከዳዊት ጋር የነበሩ ባሕርያት፡ አንድ ምስኪን ወጣት ቢሆንም፡ እነርሱ ግን—ሰውዬው በእርሱ ውስጥ አዩ። እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ እንዳለ አይተው፡ አንድ ቀን ወደ ሥልጣን እንደሚመጣ አወቁ። ሌሎቹን... የጎልያድ አምስት ወንድሞች፡ አንዱ ብቻውን በአንድ-እጁ ገደላቸው። አንዱ ብቻ ሦስት መቶ ሰዎች ገደለ፡ አንዳንድ ሴቶች ለእራት ጥቂት ባቄላ ሲለቅሙ፡ ሠራዊቱ ሄዶ ነበርና፡ ጦርም ወሰዶ፡ ከፍልስጥኤማውያን ሦስት መቶ ሰዎች ገደለ። ባህርይ! ለምን? ከዳዊት ጋር ሆኑ። ቅባቱ በእርሱ ላይ እንዳለ ተረድተው፡ ወደ ስልጣን እንደሚመጣ አውቀዋል።

147 ይህም በቃሉ ጎን የምትቆመው የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ንጹህ ምስል ነው! አንድ ቀን እንደሚሾም እናውቃለንና። አንድ ቀን ወደ ስልጣን እንደሚመጣ እናውቃለን። ሳኦል ዘንድ... በሌሎች ህዝቦች ፊት የሸሸ ቢሆንም፡ ወደ ስልጣን እየወጣ እንደነበረ አውቀውታል። እኛም፡ እሱ ወደ ስልጣን እየመጣ እንዳለ አውቀናል፡ ስለዚህ ምንም አይነት ዋጋ ቢያስከፍለንም፡ ቃሉን ተቀበለን ከጎኑ እንጸናለን። ፍልስጤማውያንን መጉመድ ቢጠበቅብንም፡ ወይም አንዱ እንዳደረገ፡ ጉድጓድ ውስጥ ገብተን አንበሳ መግደል ቢጠበቅብንም፡ ምንም ቢሆን እንሄዳለን፡ ምክንያቱም... እግዚአብሔር ያዘጋጀው በዚህ መንገድ ነው። ባህርይ እንፈልጋለን።

148 አሁን እናንተ "ለምን እንዲህ ሆና እንድትነደፍ ፈቀደ፡" ትሉኝ ይሆናል? ብዙ ጊዜ ማጥፋት አልፈልግም፡ እዚህ ጋር ማለት የምፈልገው ብዙ ነገር አለኝ። "ለምን፡" የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡ "እግዚአብሔር ይህችን ሴት ለምን እንዲህ አደረጋት? ለምን እንዲህ እንድትሆን ፈቀደ? " ስለበጎ ፈቃዱ ነው። በትክክል።

149 አሁን ለአንድ ደቂቃ ብቻ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ከከፈታችሁ፡ እስኪ ለአፍታ ያህል፡ ወደ ሮሜ 9 እንክፈት፡ ማንበብ—ከፈለጋችሁ፡ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደሚያደርግ፡ የሆነ ነገር አሳያችኋለሁ። እና እግዚአብሔር ለራሱ በጎ ፈቃድ የሚያደርገውን ነገር እዚህ ማየት እንችላለን። ሮሜ 9፡14።

እንግዲህ **ምን እንላለን?**

**በእግዚአብሔር** ዘንድ **ዓመጻ አለን?...**

150 ዔሳውን ሲመርጥ፡ ወይም ያዕቆብን መርጦ ኤሳውን በናቀው ጊዜ፡ ልጆቹ እንዳቸውም መምረጥ ከመቻላቸው በፊት፡ ከእነርሱ ከሁለቱ ሳይሆን፡ ከራሱ፥ ገና ሳይወለዱ፡ በእናት ማኅፀን እያሉ፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ "ኤሳውን ጠላሁ፡ ያዕቆብንም ወደድሁ።" አያችሁ? ለምን?

> ለሙሴ፡ **የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ፡ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና።**
>
> **እንግዲህ ምሕረት... ለወደደ፡ ወይም... ለሮጠ አይደለም፡** ከሚምር **ከእግዚአብሔር ነው እንጂ።**
>
> **መጽሐፍ ፈርዖንን፡ ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ፡ ሰሜም በምድር ሁሉ** ይነገር **ዘንድ፡ ለዚህ አስነሣሁህ ይላልና።**
>
> **እንግዲህ... የ** (እዚህ ጋር ተከታተሉ።)... **-የሚ... የሚወደውን ይምረዋል; የሚወደውንም እልከኛ ያደርገዋል።**
>
> **እንግዲህ...** ስለ **ምን፡ እስከ አሁን ድረስ...** ይነቅፋል? **ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው** ትለኝ **ይሆናል?**
>
> **ነገር ግን፡ አንተ ሰው ሆይ፡ ለእግዚአብሔር** የምትመልስ **ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን፡ ስለ ምን** እንዲህ **አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?**
>
> **ወይም ሸክላ** ሠሪ **ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር፡** አንዱንም **ለውርደት ሊሠራ፡ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?**
>
> **ነገር ግን እግዚአብሔር፡ ቍጣውን** ሊያሳይ፡ **ኃይሉንም ሊገልጥ ወዶ፡ ... አስቀድሞ ለክብር** ባዘጋጃቸው **በምሕረት** ዕቃዎች ላይ **የክብሩን ባለ ጠግነት ይገልጥ ዘንድ፥**
>
> **... ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ** ዕቃዎች **በብዙ ትዕግሥት ከቻለ፡ እንዴት ነው፡**

151 አሁን ከዚህ ጋር ትንሽ ተከራከሩ። እግዚአብሔር አደረገው! በዚህ መልኩ ማድረግ ነበረበት። ይህ መሆን ነበረበት። አሁን አዳምጡ። አሁን ለአምስት ደቂቃዎች ያህል፡ ትኩረታችሁን ወደ አንድ ነገር ማምጣት እፈልጋለሁ።

152 እግዚአብሔር ምንድን ነው? እግዚአብሔር ታላቅና ዘላለማዊ ነው። በመጀመሪያ፡ ከመጀመሪያ በፊት፡ እሱ አምላክ አልነበረም። ይህን ታውቃላችሁ? **አምላክ** ማለት "የሚመለክ ነገር" ነው፡ ያኔም እሱን የሚያመልክ አንዳች ነገር አልነበረም። ብቻውን ይኖር ነበር።

153 በእርሱም ውስጥ መገለጫዎች ነበሩት። መገለጫ ምንድነው? አሳብ። አሁን ለዛሬ ምሽት ትምህርቱን የሚገድብ ነገር ታገኛላችሁ። ልብ በሉ፡ እሱ ራሱ በሱ ውስጥ የሚኖር የራሱ መገለጫ ነበረ። ስለዚህ፡ አባት መሆን በሱ ውስጥ ነበረ፡ አምላክ መሆን በሱ ውስጥ ነበረ፡ ልጅ መሆን በውስጡ ነበረ፡ አዳኝ መሆን በውስጡ ነበረ፡ ፈዋሽ መሆን በውስጡ ነበረ። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የእሱን ባህሪያት ብቻ የሚያስረዱ ናቸው። ከሰርዓት የወጣ አንዳች ነገር የለም። እግዚአብሔር መጨረሻውን ከመጀመሪያው ያላየው ይመስላችኋልን?

በእርግጠኝነት፡ አይቶታል። መገለጫዎቹን እያሳየ ብቻ ነው እንጂ፡ ከስርዓት የወጣ አንዳች ነገር የለም።

154 አሁን፡ ሰውን እንዲወድቅ አድርጎ **ጻዲቅ** ሊሆን አይችልም። የራሱን ምርጫ እንዲመርጥ፡ ግን እንደሚወድቅ እያወቀ፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ ነጻ የመምረጥ መብት ያለው ሊያደርገው ይገባ ነበር።

155 አሁን፡ የሆነ ነገር ካልጠፋ በስተቀር አዳኝ ሊሆን አይችልም። አንድ ነገር ካልታመመ በስተቀር ፈዋሽ ሊሆን አይችልም። እነዚህ ነገሮች እንደዚያ መሆን ነበረባቸው። እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ የሠራቸው ታላላቅ መገለጫዎቹ እንዲገለጡ ነው። ያ ባይሆን ኖሮ፡ ፈጽሞ አዳኝ መሆን አይቻለውም ነበር። ይሁን እንጂ አዳኝ እንደነበረ እናውቃለን፡ ጊዜ ከመምጣቱ በፊት ሳይቀር፡ እርሱ አዳኝ ነበረ። እርሱ አዳኝ ስለነበረ፡ ስለዚህ የሚጠፋ ነገር መኖር ነበረበት። እንዴት ይሆናል?

156 እሱ ራሱ አድናለሁ በማለት፡ ይሄን ወስዶ ካጠፋው፡ እንግዲያውስ በፍርዱ ጻዲቅ አይሆንም። ሰውን ወደ ሲኦል ወርውሮ፡ ጻዲቅ ሊሆን አይችልም። እሱ ደግ፡ ገር፡ እውነተኛ፡ ታማኝ ነውና፡ ድንቅ ዳኛም ነውና። አያችሁ፡ እንዲያ ከሆነ እራሱን የሚቃወም ስራ ስራ ማለት ነው።

157 ስለዚህ ሰውን በዚህ ሁኔታ ውስጥ፡ እራሱ መውደቁን እያወቀ፡ እንዲወድቅ፡ ማድረግ ነበረበት፡ ነጻ የመምረጥ መብት ያለው አድርጎ ሊሰራው ይገባ ነበር፥ በራሱ አምሳል የተሰራው፡ ይህ ወንድ፡ እንዴት ሊወድቅ ይችላል? አሁን የቀን ብርሃን ይታያችኋልን? ስለዚህ፡ ከዋናው ፍጥረት ላይ፡ ሌላ-ምርት ማድረግ ነበረበት። አሁን ተመልከቱት። አያችሁ? ይኸውላችሁ። አያችሁ? እንግዲያውስ፡ የወደቀው ያ ነው። እንደምትወድቅ እያወቀ፡ ሰራት። ለውርደት ዕቃም፡ በሰይጣን እጅ ተላለፈች። ዛሬ ክብር የሚሰጠው የት ነው? አሰቡት። በደንብ ተከታተሉኝ።

158 እንደገና ደግሞ፡ ሌሎች እንስቶች እንዲህ ሳይሆኑ እንዴት እሷ ብቻዋን በዚህ ንድፍ ተሰራች፡ ሌሎች እንስቶች እንዲህ ሳይሆኑ እንዴት እሷ ብቻዋን በዚህ ንድፍ ተሰራች? ሌሎች እንስቶች ሁሉ በዚያ ንድፍ አልተሰሩም። ዛሬም፡ አይደሉም። ሊሆኑ አይችሉም። በዚያ መንገድ ካልተሰራች፡ እንደዚያ አትሆንም። ለምን ይህችን ሴት፡ ማለት ሴቲቱን፡ እንደሌሎቹ ሁሉ መሆን እንድትችል፡ ልጆቿን ለማሳደግ ብቻ፡ እንደ ሌሎቹ እንስቶች አርጎ ለምን አልሰራትም? ያን ጊዜ ባል ይኖራታል፡ ትኖራለች፥ ልጅ በሚያስፈልጋት ጊዜ፡ ልጇን ትወልድ ነበር። ለምን—ለምን እንዲህ አደረጋት?

159 እነዚህን ቃላት መናገር አልችልም። እናንተ ራሳችሁ ስለምናገረው ነገር ይገባችኋል፡ አይደል? ከገባችሁ፡ "አሜን" በሉ። [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አዎን። አያችሁ? እዚህ ጋር ወጣት ልጃገረዶች፡ እና ወጣት ወንዶች ተቀምጠዋልና፡ አያችሁ። ይሁን እንጂ እንደምታውቁት፡ እንሰሳ በዓመት በአንድ የተለየች ወቅት ይመጣና፡ ይገናኛታል፡ ከዚያ በኋላ አበቃ። ሴት ላይ፡ ግን፡ ዘወትር ነው። እና ለምን እንደዚህ አደረጋት?

160 አሁን በዚሁ እየቀጠልን ሳለ፡ ታላቅ አሳቡ ምን እንደነበረ፡ ፍጹም መሆን በሚችለው ፍጽምና ሁሉ ሲከፈት ተመልከቱት። ይህንን እስከ በቀደም ለታ ድረስ አላውቀውም ነበር።

161 ለምን በመጀመሪያ እንደ ሌሎቹ እንሥቶች፡ እንደነሱ ለምን አላደረጋትም? በፊቱ የማያምር ስለሚሆንበት። እርሱ የንጽሕና ሁሉ ምንጭ ነው። ባታለላት ጊዜ፡ ሰይጣን እንዲይዛት የፈቀደው በዚህ ምክንያት ነው። ከመጀመሪያ ለዚህ የተነደፈ፡ እንዲህ ያለው ፍጥረት፡ ለእርሱ አይሆንም።

162 በዋናው የነደፋቸው፡ ሥራዎቹ ሁሉ፡ የሚቀጥሉ ናቸው። ሁሉም የመጀመሪያ ስራዎቹ ቀጣይነት ነበራቸው። ሴት ውሻ፡ ተባዕት ውሻ፥ አያችሁ፡ ሴት ላም፡ ተባዕት ላም፥ ሁሉም ነገር ቀጣይነት ያለው ነው። ሁሉም ተፈጥሮ ቀጣይነት ያለው ነው። ዘር ይሞታል፡ ልክ እንደ ሞት፡ ቀብር፡ ትንሣኤ፥ መሬት ውስጥ ይወርዳል። ከዛፉ ውስጥ ፈሳሹ ይፈሳል፡ ቅጠሎቹን ያረግፋል፡ በሚቀጥለው አመት በአዲስ ቅጠል በትንሳኤ ይመጣል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? ሁሉም ነገር፡ ተፈጥሮ ሳይቀር፡ የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ፡ በአንድነት፡ ቀጣይነት አለው፥ ከዚህ ሁሉ አንድ ግን በእግዚአብሄር ቀጣይነት ኪዳን ያልተነደፈ ይታያል። ተፈጥሮ ኃጢአት እንዳይሠራ በጣም በንድፍ የተሰራ ነው። አሰቡት! የመጀመሪያው፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት፡ ኃጢአትን ማድረግ አይችልም።

163 ኦህ፡ አሁንስ አይታያችሁም ወይ፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ መታለል፡ በዚህ እይታ አይታያችሁምን? መጀመሪያው የእግዚአብሔር ቃል ራሱ ነው! በእግዚአብሔር ዘንድ ሐጢአት የለም። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አይታችኋል? በውድቀት ምክንያት ወደ ሕልውና የመጣው ፈጣሪ ይህ ነው። እግዚአብሔር የራሱ ቤተክርስቲያን ትኖረዋለች፡ ይሁን እንጂ እዚህ ያሉት ሁሉ ውድቀቶቻቸውን ተመልከቱ።

164 እግዚአብሔር ወንድም ሴትም ነበሩት። ይህች ሴት፡ ግን፡ ተመልከቱ፡ ምልክቶቿ ራሱ በእግዚአብሄር ዘንድ የነበረው አሳብ ምን እንደነበረ ያሳያል። አንድ፡ ወይም ሁለት ሰአት ወሰደን፡ ከፋፍለን ማየት እንችላለን። እ... ያን ፍጥረት ለዚያ ነገር ሠራውና፡ ያን ፍጡር ሰርቶ ሰይጣን እንዲያስታት አመጣት፡ እርሱም አሳታት። እስከ አሁን ድረስ እንደያዛት አለ። እሷም፡ እንደ ወንዱ፡ ወደ መስቀሉ ብትሸሽ ይሻላታል።

165 ልብ በሉ፡ ተፈጥሮ ሁሉ ያለመቆራረጥ ይሰራልና። ሴቲቱንም በተመሳሳይ መንገድ በመጀመሪያ ፍጥረት ቢሰራት ኖሮ፡ ኃጢአት ባልኖረም ነበር። ምክንያቱ እንዲህ አታደርግም ነበር፡ አታደርግም ነበርና። እሷ የዋናው ፍጥረት መዛባት ናት።

166 ስለዚህ ኃጢአትም የዋናው እውነት መዛባት ነው! ውሸት ምንድን ነው? እውነት ሲዛባ ነው። ምንዝርና ምንድነው? ትክክለኛው ድርጊት ሲዛባ ነው። ስለዚህ የተዛባ ፍጥረት አለ፡ ሁሉም ነገር የተዛባ ነገር አለው። እና ይህ ሁሉ ነገር ኃ-ጢ-አ-ት በመባል፡ ይታወቃል። ጥያቄው ታላቅ የሚሆነው ለዚህ ነው።

167 ይህች እሱን ለማታለል፡ ከሰው የተገኘች፡ አንዲት፡ ቅንጣት፥ እዚህ ጋር እንዳረጋገጥነው፡ ሠሪዋ እግዚአብሔር ነው። የተሰራችው ለዚህ ነው።

168 በምድር ላይ ሊታሰብ ከሚችለው ነገር በላይ የወረደች ዝቅተኛ ማለት፡ ሥነ ምግባር የጎደላት ሴት ናት። ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ወጣት ሴቶች። የሰው ቆሻሻ መጣያ፡ የስጋ ግንኙነት ዕርቃን ናት። ሥነ ምግባር የጎደላት ሴት ማለት፡ የሰው ልጆች የስጋ ግንኙነት ቆሻሻ መጣያ፡ ብክለት፡ ብሰባሽ፡ ቆሻሻ፡ ክፋት፡

የዝቅተኛና-ወራዳነት በሷ ላይ የሚወገድባት መጣያ፡ ብቻ ናት። በዚህ መንገድ የተሰራችው ለምንድነው? ለማታለል። በምድር ላይ የነበረው ኃጢአት ሁሉ በሴት ምክንያት የመጣ ነው።

169 ከቺካጎ የመጣች አንዲት ተንታኝ፡ አ—አንዲት ሴት እንዲህ ብላ ጽፋለች፡ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ፡ በሜትሮፖሊታን ዩናይትድ ስቴትስ፡ የፖሊስ ኃይል፡ በሚከታተሏቸው ነገሮች እንዲህ ብላለች፡ በ፡ "በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በማንኛውም መልኩ ከተፈጸሙት ወንጀሎች፡ ዘጠና-ስምንት በመቶው፡ ወይ ሴት የፈጸመችው ነው ወይም ከበስተጀርባው ሴት አለችበት ይላል።"

170 አሁን ይህን ሁሉ ያልኩት፡ መጨረሻ ላይ ወደ አንድ ነገር ለመድረስ፡ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ማየት እንድትችሉ ነው።

171 እሷም በመጀመሪያ አዳምን ፍሬው ደስ የሚል እንደሆነ፡ እና ሌላ ሌላ ነገር ተናግራ፡ እንዳታለለችው፡ አታላይ ለመሆን የተፈጠረች፡ ከቃሉ እንዲርቅ እና እንዲታለል አደረገችው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የምትሠራው በዚህ መንገድ ነው፡ ተመሳሳይ ነገር ናት።

በኋላ፡ ግን፡ እሷን የሚገዛ፡ ገዢዋ ሆነ።

172 አሁን ግን በዚህ የጽንሰ ዘመን፡ እንዴት ያለ ልዩነት ተፈጠረ። እሱ ገዢዋ እንደመሆን፡ ጭራሽ አማልክት ሆናበታለች። አዎን፡ እሷ ገዛችው። አሁን ምን እየመታሁ እንደቆየሁ በትክክል ትረዱኛላችሁ። በውበቷ እና በፆታዊ የመቆጣጠር አቅሟ፡ ሰይጣን በሰጣት ቅርፅ፡ ሰይጣን በሰራው ተረፈ-አካል፡ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድታታልል ተልካለች። እና ሰይጣን ካለው መሳሪያዎች ሁሉ በበለጠ ወደ ሲኦል ልታሰገባቸው ትችላለች። በትክክል ትክክል ነው።

173 እህቶች ሆይ አሁን የምናገረው ስለ እናንተ አይደለም፡ ሥነ ምግባር ስለ ጎደለባቸው ነው። እዚህ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ስፍራችሁን፡ እናሳያችኋለንና። ከመጀመሪያው—ጀምሮ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ነበር።

174 አሁን ዛሬ ይህን ለማድረግ፡ የዩናይትድ እስቴትስ አምላክ ምንድናት? ከብዙ ዓመታት በፊት በተበርናክል ውስጥ ሰብኬዋለሁ፡ ታስታውሳላችሁ? የዚህ የዘመናዊው ዘመን አምላክ፡ ሜክ-አፕ ተቀባብታ እና ከጉልበቷ በላይ ለብሳ፡ እና እንዲህ የመሳሰሉ ነገሮች ለብሳ፡ የተቀመጠች ነውረኛ ናት። "እነኋት አምላካችሁ፡" ብያችሁ ነበር! እውነትም ነው፡ ግማሽ አካሏ ዕርቃን ሆና፡ በየማስታወቂያው ትታያለች። በየጎዳናውም፡ ያው ናት።

175 ኢየሱስ ብሏል፡ "ከመጀመሪያው፡" የሰይጣን መሳሪያ ናት። አያችሁ? አሁን እንደዚያ እንደሆነ፡ እና "ከመጀመሪያ ጀምሮ፡" ሲል ስለ ምን እየተናገረ እንዳለ አይተናል።

176 አሁን፡ አሕዛብ እንደ አምላክ፡ (ይህን ታውቃላችሁ? ) እንደ አማልክታቸው ያደርጓት ነበር። አዎን በትክክል። አማልክታቸው አደረጓት፡ ምክንያቱ በአምልኮአቸው ላይ የጾታዊ ግንኙነት ተግባር ይፈጽማሉና። "ፈጣሪ ነበረች። በማኅፀንዋ ውስጥ ዘሩን ተሸክማ ፈጠረች፡" በማለት ይገልጿታል። ይህ ውሸት ነው። ፈጣሪ አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። የጳውሎስን

ታስታውሳላችሁ? “ከሰማይ የወረደች፡ አማልክት፡” የሚሏት፡ ከድንጋይ የተቀረጸች፡ “የኤፌሶኗ፡ ዲያና።” የአሕዛብ አምልኮ እንዴት እንደሆነ አታዩምን?

177 እኛም፡ ሳናውቅ፡ በቀጥታ ወደ አሕዛብ አምልኮ፡ ወደ ሴቶች ተመልሰናል፡ በምድር ካሉ ፍጥረታት ዝቅተኛ ወደ ሆነችው፡ ወደ ሴት-አምልኮ! ሰውን ወደ ፈለገችው መጠምዘዝ ትችላለች። ውበቷ ሁሉ ከውጭ ነው፡ ከውስጥ ግን ገሃነም መሆኗን፡ አያውቅም። ሰሎሞን እንዲህ አለ፡ “ደጆቿ፡ የገሃነም ደጆች ናቸው።”

178 አሁን እዚህ ላይ ኢየሱስ በራእይ፡ በምዕራፍ 2 እና በ15ኛው ቁጥር ስለ ኒቆላውያን ትምህርት፡ የተናገረው በግልጽ ይታየናል፡ ይህም እራሷን ከቃሉ እየጎተተች የምታሰወጣዋ ቤተክርስቲያን መምጣት ነው።

179 እንዲሁም እዚህ፡ በግልጽ፡ እነዚህ በየቴሌቪዥኑ የምናያቸው፡ ጸያፍ፡ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌላቸው የቆሸሹ የሆሊውድ የወሲብ ንግሰቶች፡ ፕሮግራሞችን መታዘብ እንችላለን። እነዚህ ልጆች፡ ምስኪን ወጣት ሴቶች በየጎዳናው ላይ-እና-ታች ሲሉ፡ የከተማዋን እርኩሰት መታዘብ እንችላለን፡ ቅዝቃዜው ሊገድላቸው በሚችል አቅም ብርድ ሆኖ ሳለ፡ ትንንሽ ሚጢጢ፡ ታይት ለብሰው፡ ይዞራሉ። ያንን የሚያደርገው ዲያብሎስ መሆኑን አያውቁም። እርኩስ መንፈስ ገብቶባቸዋል፡ አያውቁትምም! ሴት ውሻ እንዲህ ስታደርግ አታዩአትም አይደል፡ ታዩአታላችሁ እንዴ? ሌላ እንስት ያን ስታደርግ አታዩም፡ ወንዱም፡ ወደሷ ሲሄድ አታዩትም።

180 አያችሁ፡ አሁንስ ምስሉን አገኛታችሁታል? ጌታ ቢፈቅድ አንድ እፍታ፡ አንድ ነገር እንተዋወቃለን።

አሁን ኒቆላውያንን ተመልከቱ፡ አስተምህሮአቸውን አይታችኋል።

181 እነዚያ በጉርምስና-ዕድሜ ላይ የሚገኙትን ንግሰቶች፡ በጎዳና ላይ የራቁት ዳንሰኞች የሚሏቸውን፡ ተመልከቷቸው። እነዚህን የራቁት ዳንሰኞች ለማየት፡ በየጥጉ ያሉትን ጸያፍ ትርዒቶች ለማየት ይገቡ ነበር። አሁን ጎዳናውን ተመልከቱት፡ ከእናንተ የሚጠበቀው፡ ዓይናችሁን መግለጥ ብቻ ነው። ነገር ዓለሙ ራቁት ደናሽ ሆኗል። አዎን። ይህን የሚያደርጉት ለምንድነው? ይህን የምታደርገው ለማማለል፡ ለመፈተን፡ ብቻ ነው። እርኩስ ስለሆነች ይህን ታደርጋለች። እንዲሁ እንድትሆን ስለተሰራች ታደርገዋለች። በሰይጣን እጅ ውስጥ ያለች መሳሪያው እንደሆነች አታውቀውም፡ ደግሞም ናት።

182 ዛሬ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ሳይቀር፡ ስለ ወሲብ ድርጊቶችን እያስተማሩ ነው። ዓለማችን የበሰበሰች የሴት-አምልኮ ናት! እውቃለሁ ይሄን ማመን አይፈልጉም። ቀን ላይ፡ ዝማሬ ለመዘመር እና ሌላ ለመሆን፡ ይወጣና ይቆማል፥ ከዚያ በኋላ ሴት ይዞ ይወጣና፡ ሌሊቱን በሙሉ፡ ሲንቀዠቀዥ ያድራል። አያችሁ? በጣም ጥሩ። ይህም፡ በእግዚአብሔር፡ በቃሉ ፊት፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ከፈጠራቸው እንስሳት ሁሉ ዝቅተኛ ናት። ይኸውላችሁ።

183 እግዚአብሔር ቃሉን እንዳታስተምር የከለከላት ለዚህ ነው። እውነት ነው። አንደኛ ጢሞቴዎስ 2፡9-15 ላይ፡ “ሴት እንድታስተምር፡ ወይም ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም።” አያችሁ? ደግሞም 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡34 ላይ፡ “ሴቶቻችሁ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዝም ይበሉ፡ ሕግ ደግሞ እንደሚል፡

ዝም እንዲሉ ታዝዘዋልና፡ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም።” ዛሬ፡ ግን፡ ቤተ ክርስቲያን ምን አደረገች? መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ እየከለከለ ሳለ፡ ፓስተር፡ እና ወንጌላዊት ያደርጉዋታል። መጽሐፍ ቅዱስም “ሕግ ደግሞ እንደሚል፡” ብሏልና፡ መላ ነገሩ፡ ቀጣይነት እንዲኖረው አደረገው።”

184 ልክ እንደ ትናንት ማታ፡ ብቸኛው የአምልኮ ሰፍራ፡ በፈሰሰው በበጉ ደም ስር፡ በበጉ ዘንድ እንደሆነ ሁሉ። ዛሬ ሰፍራው፡ በክርስቶስ ብቻ ነው። የምታደርጉበት ብቸኛው መንገድ ወደ እርሱ በመምጣት ነው። ብቸኛው ማምለኪያ እሱ ነው። ድሮም እንደዛ ነበር። የአምልኮ ሰፍራው በፈሰሰው ደም ስር ብቻ ነው።

185 ስለዚህ አሁን ሙሉ ምስሉ ለእኛ ሲገለጥ እያየነው ነው። ያቻትና። ለዚያም ነው እግዚአብሔር እንድታስተምር የማይፈቅድላት፡ ፊቷን ሸፍና ከመቀመጥ በቀር በቤተክርስቲያን ውስጥ ምንም ነገር እንድታደርግ አይፈቅድላትም።

186 አሁንስ ወንድምና እህቶቼ ሆይ ይህን ሁሉ በልቤ አውቄ የተናገርኩት ነገር ሁሉ፡ ለምን እንደተናገርኩ፡ ያደረግሁትን ለምን እንዳደረግሁ፡ አሁንስ አያችሁን? እህቶች ሆይ፡ አውቃለሁ፡ እ... ሰፍራ አላችሁ (አንዴ ቆዩ)፡ ይህም እግዚአብሔር በውስጣችሁ የሚቀርጸው ድንቅ የሆነ ባህርይ አላችሁ። እኔ ለመናገር የሞከርኩት ሰለ ሌላኛው ጽንፍ ነው፡ ይህም “በመጀመሪያ፡” ከምን እንደሆናችሁ ለማሳየት ነው። ኢየሱስም ይህን መረዳት እንድንችል “ወደ መጀመሪያው ተመለሱ፡” ብሎናል። እያደረግን ያለነው ይህ ነው።

187 አሁን በእነዚህ ሁሉ ዘንድ ከፍ ከፍ ያሉትን ነጥቦች መዳሰስ ነበረብኝ፡ እናንተም እንደተረዳችሁት ተሰፋ አደርጋለሁ። እናተም ይህን ቅጂ የምትሰሙ ሰዎች፡ እንደምትረዱት ተሰፋ አደርጋለሁ። ብቻ መለስ እንበል። ይህም ኢየሱስ “ወደ መጀመሪያው፡ መለስ ብላችሁ፡ ተመልከቱ፡” ያለውን ለማሳየት ብቻ ነው። ሰለ ሁሉም ነገር፡ ወደ መጀመሪያው ተመለሱ። ያኔ ዛሬን፡ ማየት ትችላላችሁ።

188 ሰዎች፡ ሰለ’ኔ፡ የሴት-ጠላት ነው ይሉኛል። ይህ ከእውነት የራቀ ነው። እኔ አልጠላም። “የሴት-ጠላት፡” አሉ። ጳውሎስንም፡ የሴት-ጠላት ብለው እንደጠሩት አስታውሱ። በቅርብ ጊዜ፡ አንዲት ሴት አገልጋይ፡ እንዲህ አለችኝ፡ “ኦህ፡ አንተ እንደ ጳውሎስ ነህ፡ ነገረ ሰራው ሁሉ እኛን ሴቶችን ማቃለል ነበር።”

189 መጽሐፍ ቅዱስን፡ አዲስ ኪዳንን፡ ቃሉን እንዲጽፍ የተፈቀደለት፡ የእግዚአብሔር ቅዱስን ሰው ትከራከራላችሁን? እርሱ እንዲህ አለ፡ “እኔ ካስተማርኩት ወንጌል የተለየ የሚያስተምር፡ የሰማይ መልአክ ቢሆንም የተረገመ ይሁን ብሏል፡” ሴት ሰባኪ ይቅርና።

190 ስለ ኤልያስም የሴት-ጠላት ነበር ብለውታል። የሴት-ጥላቻ አልበረበትም፡ ትክክለኛ ከሆነች። እሱ የማይወዳቸው ኤልዛቤሎችን ነው።

191 ይህ ከሆነ ደግሞ፡ እግዚአብሔር ሁሌም ያው መሆን አለበት፡ ምክንያቱም ወደ ነብያት የሚመጣው ቃል እርሱ ነውና። ስለዚህ እግዚአብሔር መሆን አለበት፡ በተመሳሳይ መንገድ፡ ሰለዚህም፡ ተመልከቱት፡ የመጀመሪያውን ፍጥረት፡ “ከመጀመሪያው” ያውቀዋል፡ “ከመጀመሪያው፡” አለ። ቃሉ የመጣላቸው ለነቢያት ነበረ።

192 እሷ ስለ ወንዱ ሰራት እንጂ፡ ወንዱ ስለ እሷ አልተሰራም። ይሄን ታውቃላችሁ፡ ማለት፡ “ሴት ለወንድ ተሰራች እንጂ፡ ወንድ ለሴት እንዳለተሰራ ታውቃላችሁ”? ሰንቶች ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ ያን ያስተምራል። እሺ እንግዲህ። ከውድቀት በፊት፡ በሰው ዘንድ፡ በፍጥረት ሁሉ ላይ እኩል ሰፍራ ተሰጥቷታል። ከውድቀት “በኋላ” ግን፡ አሁን ወደ ዋናው እንግባ። ከውድቀት “በኋላ” ግን፡ መሪዋ ሆነ፡ በሌሎች ነገር ሁሉ ዝም ማለት አለባት፡ ይህ ግን ከዋናው መጀመሪያ በኋላ ነው።

193 ኢየሱስም “ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም፡” ብሏል። ጊዜ የጀመረው ያን ጊዜ ነው፡ እግዚአብሔር በኦሪጂናል ፍጥረቱ ላይ መጀመሪያ ባደረገ ጊዜ ነው። ይህን የገባችሁ ሁሉ፡ እንደገና “አሜን” በሉ። [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—እርታዒ።] በመጀመሪያ እግዚአብሔር አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ ፈጠረ። ሴትየዋ ግን፡ ማማለል እንድትችል ተደርጋ፡ ከሌሎቹ እንሰሳት ሁሉ በልዩ ሁኔታ ተሰራች። አሁን ተከታተሉ አሁን፡ “ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም።” ተሰራች፡ በኦሪጂናል ሁኔታዋ ብትቆይ ኖሮ፡ ውድቀት አይሆንባትም ነበር። እሷ ግን የእግዚአብሔርን አጠቃላይ የቀጣይነቱ ውድቀት እና መቋረጥ ምክንያት ሆነች፡ በዚህም ሞትን፡ ሀዘንን፡ እና ሁሉንም ነገር፡ በምድር ላይ አወረደች። እሷም በዚህ መንገድ ተሰራች።

194 አሁን ልብ በሉ። አሁን፡ ከመጀመሪያው **በኋላ**፡ ከመጀመሪያው **በኋላ**፡ ጊዜ ከጀመረ **በኋላ**፥ ዘለአለማዊነት፡ ያን ጊዜ፡ አበቃለት። ልብ በሉ፡ በሔዋን ከተፈጸመው ውድቀት በኋላ፡ ከውድቀቱ በኋላ፡ ሌላ ቃል ኪዳን እንዲደረግ አሰፈለገ። አሁን ይህ ያሰናክላችኋል፡ ነገር ግን ይህ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እሰጣችኋለሁ። አሁን አሰተውሉ ከውድቀት በኋላ፡ ኢየሱስ አለ... እግዚአብሄር፡ በመጀመሪያ፡ ከየወገኑ አንድ አንድ አደረገ፥ አሁን ግን፡ ከውድቀት በኋላ ግን፡ አሁን ከዚያ አልፈን እንሄዳለን። ድሮ ቃል ኪዳኑ በ-እኩልነት ነበረ፥ አሁን ግን፡ ከውድቀት በኋላ፡ ሌላ የተገባ ቃል ኪዳን አለ። ከእንግዲህ ወዲያ ከእርሱ ጋር ገዢ አልሆነችም፡ እያንዳንዱ የተለየ ቃል ኪዳን ሊኖረው ተገባ።

195 አሁን ያ ትክክል መሆኑን እንመልከት። ዘፍጥረት 3ን እንይ እና፡ ትክክል መሆኑን እንወቅ፡ አሁን በዚህ ሰንቀጥል ሳለ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ቅኖች መሆን አለብን፡ በትክክለኛው መንገድ ወጥተው በትክክል ተምረናቸዋልና። ሰለዚህ ምናልባት ያለን ጊዜ ውሱን ሊሆን ይችላል፡ ይህም ርዕሱን ለማጠቃለል ያለን ጊዜ፡ ፍች በተመለከተ፡ **ለምን** እና **ምን** እንደሆነ አሳይተን ለመጨረስ፡ በጣም የራቅን ሰላልሆንን ነው። አሁን በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ፡ አሁን በ3ኛው፡ በ16ኛው ቁጥር እንጀምራለን። በ14ኛው ቁጥር እንጀምር።

> **እግዚአብሔር አምላክም... እባቡን አለው፡** (ይረግመዋል)፡ **ይህን ሰላደረግህ—ከእንሰሳት፡** ከ**ምድር አራዊትም ሁሉ፡... ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፥ በሆድህ**ም ትሄዳለህ፡ **አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ** ትበላለህ፥
>
> **በአንተና በሴቲቱ መካከል፡ በዘርህና** በዘርዋም **መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፥** እርሱ **ራስህን ይቀጠቅጣል፡** አንተም

**ስኰናውን ትቀጠቅጣለህ።** (ተሰፋ ሰጪው፡ ይቤዠን ዘንድ፡ “በሴት በኩል የሚመጣው፡” መሲሑ ነው።)

**ለሴቲቱም አለ፡...**

196 አሁን ተመልከቱ፡ ከእባቡ ጋር የተደረገው ኪዳን ያ ነው። ያም ደግሞ፡ በፊት ማለት በመጀምሪያው፡ ወይም ከመጀመሪያው በፊት፡ ሁሉም ሰላም ነበሩ።

**ለሴቲቱም አለ፡ በፀነሰሽ ጊዜ** ጭንቅሽን **እጅግ አበዛለሁ፥ ልጆችን**ም **በጭንቅ ትወልጃ**ለሽ፥ **ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፡ እርሱም ገዥሽ ይሆናል፡** (ከእንግዲህም ወዲህ በፍጹም በ-እኩልነት መሆን አልቻሉም።)

197 አሁን ደግሞ ዞራ፡ ገዢ ሆናለች።

**አዳምንም አለው፡ የሚሰትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከ... እርሱ እንዳትበላ፡ ካዘዝሁህ፡ ዛፍም፡ በልተሃልና፥** ከ**አንተ የተነሣ** (አዳም፡ አልተረገመም) **ምድር** ከ**አንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፥ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ** በድካም **ከእርሰዋ ትበላለህ፥**

**እሾህንና... አሜከላን ታበቅልብሃለች፥ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ፥**

ወደ **ወጣህበት መሬት** እስክትመለስ **ድረስ፡ በፊትህ ወዝ እንጀራን** ትበላለህ፥ **ወደ ተገኘህባት—ወደ ተገኘህባት፥ አፈር ነህና፡ ወደ አፈርም ትመለሳለህ።**

198 ሁለት ቃል ኪዳኖች። አሁን ኢየሱስ “በመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም፡” ያለውን “መጀመርያው፡” በዚህ ይቋጫል። አሁን ሌላ ቃል ኪዳን ይህ ነው። አስተውሉ፡ ሌላ ቃል ኪዳን ነው። ለአካሉ፡ እና ለተረፈ-አካሉ የተደረገ ቃል ኪዳን ይህ ነው። አስተውሉ፡ ውድቀቱ፡ በተፈጥሮ ላይ ለውጥ በማድረግ፡ በፍጥረት ሁሉ ላይ፡ ሞት እና ችግር አስከትሏል። አሁን ኢየሱስ “ከመጀመሪያው እንደዚያ አልነበረም፡” በማለት የተናገረለትን እንመልከተው። እንደዚያ አልነበረም “ከ፡” አሁን ነው ከመጀመሪያው “በኋላ” አሁን እንደዚያ ሆኗል። አሁን ድርብ ቃል ኪዳን አለ።

199 በመጀመሪያ ቃል ኪዳን ብቻ ነበር፡ አዳምና ሔዋን በ-እኩልነት ነበሩ፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት። አሁን ሴቲቱ ኃጢአት ሠራች፡ እና (ምን አደረገች? ) ሁሉንም ለሞት ሸጠቻችው፡ እግዚአብሔርም፡ በዚያ ምክንያት ሌላ ቃል ኪዳን አደረገ። እዚህ በዘፍጥረት 3:16 ላይ፡ ሌላ ቃል ኪዳን አደረገ።

200 አሁን ዓለም እንደገና በህዝብ መሞላት ነበረባት፡ በመጀመሪያው፡ በዋናው በእግዚአብሔር ፍጥረት ግን አይደለም፡ በመጀመሪያው አፈጣጠር አይደለም፡ ነገር ግን በጾታዊ ምኞት ነው። አሁን ያ “ስለ መጀመሪያው” መልስ ይሰጣል፡ አይደል’ዴ? በመጀመሪያ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ ነበሩ፡ አንድ ተባዕት እና አንድ እንስት፥ ነገር ግን ያንን መስመር ማለፏ ይህን ኃጢአት ባመጣች ጊዜ ግን፡ አሁን ዓለም እንደገና፡ በወሲብ፡ በህዝብ መሞላት ነበረባት፡ ስለዚህ በመፍጠር ሳይሆን፥ በወሲብ ሆነ። ሴትየዋ አሁን የት እንዳለች አያችሁ? አሁን ግን፡ ዓለም በህዝብ የምትሞላው በዚህ መንገድ ነው፡ በሴቶች በኩል።

201 ለዚህም ነው ኢየሱስ በሴቲቱ በኩል የመጣው፡ ያለ ስጋዊ ፍላጎት፡ እንደገና ወደ ዋናው ወደ መጀመሪያው ለመመለስ መጣ። በድንግልና የተወለደ ነው። ነገር ግን፡ ሃሌሉያ፡ እነሆ በስጋዊ ፍላጎት የማይሆንበት ዘመን ይመጣል፡ ያን ጊዜ ግን እግዚአብሔር፡ ልጆቹን በሴት በኩል ሳይሆን፡ ከምድር አፈር እና ከኮስሚክ ላይት፡ እና ከፔትሮሊየም ጭቃ አበጅቶ በመጀመሪያው እንደነበረ፡ ከምድር አፈር ይጠራቸዋል፡ በመጀመሪያ እንዳደረገው እንደ አዳም እንደገና ይፈጥራል። እግዚአብሔር ራሱን ሰው አድርጎ፡ በሴቲቱ በኩል ወደ ዓለም ማምጣት፡ ይህ ኢየሱስ እንዲቻል አደረገው። አሁን በኃጢአት፡ የፈተና ጊዜ ነው።

202 እንግዲያውስ ተመልከቱ፡ ከመጀመሪያው “በኋላ፡” እነሆ ሌላ ነገር ተዋወቀ። አሁን ይህ ያስደነግጣችኋል። ደክማችኋል´ዴ? [ጉባኤው “አልደከመንም፡” አለ።—አርታዒ።] ትንሽ ጊዜ በትዕግስት ጠብቁኝ።

203 በስጋዊ ፍላጎት የሆነው፡ ሁለተኛው ኪዳን በተደረገ ጊዜ፡ ፈጽሞ ሌላ ኪዳን (ኦሪጂናሉ ኪዳን ሳይሆን፡ ሌላ ኪዳን)፡ ምን ተዋወቀ? ብዙ ሚስት ማግባት ፖሊጋሚ፡ ተዋወቀ። ስለዚህ፡ ከመጀምሪያው በኋላ፡ በሰዎች እና በእንሰሶች ዘንድ ፖሊጋሚ ተዋወቀ፥ ይህም ከመጀምሪያው፡ ከውድቀት በኋላ ነው። እግዚአብሔር አሁን፡ በሁለተኛ ደረጃ፡ እንደገና በስጋዊ ፍላጎት የሚሆን፡ አዲስ ተፈጥሮ አበጀ። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የፈጠረው ያለ ስጋዊ ፍላጎት ነው። ይህን ታምናላችሁ? ይህ ግን ከተፈጥሮ ጋር የተደረገ፡ በወሲብ የሆነ፡ ሌላ የኪዳን ሰርዓት ነው። ሁለተኛ ኪዳን፥ አንድ ወንድ፡ ከብዙ ሴቶች፥ አንድ ወንድ አጋዘን፡ ከሙሉ የሴት አጋዘኖች መንጋ ጋር። ልክ ነው? አንድ ወይፈን፡ ከሙሉ የከብት መንጋ ጋር፡ ላሞች ጋር፥ አንድ አውራ ዶሮ፡ ሜዳ ሙሉ ሴት ዶሮዎች ጋር። ልክ ነው? እንደ ልቤ የተባለው፡ አንዱ ዳዊት፡ ከአምስት መቶ ሚስቶች ጋር፥ በአንድ ዓመት፡ ከተለያዩ ሚስቶች፡ አንድ መቶ ልጆች ይወለዱለታል፡ ኧሃ-ምም፡ እንደ ልቤ የተባለው ሰው። አንዱ ሰለሞን፡ ከአንድ ሺ ሚስቶች ጋር። ይሁን እንጂ ይህ አስተውሉ፡ በመጀመሪያው እንደዚያ አልነበረም፡ ይህ ግን ከመጀምሪያው “በኋላ” ነው። ሴትየዋ ይህን አደረገች፡ ከዚያ በኋላ አሁን የሆነችበትን ነገር ሆነች። አያችሁ?

204 የክርስቶስ ተምሳሌት የነበረው፡ ንጉሥ ዳዊት! ይህን በአእምሮአችሁ ያዙ። ዳዊት የክርስቶስን ተምሳሌት ነበረ። ይህን ታምናላችሁ? ክርስቶስ ወደፊት... በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል። እንደ እግዚአብሔርም ልብ የነበረ፡ ይህ ዳዊት፡ አምስት መቶ ሚስቶች ነበሩት። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? ዳዊት ከአምስት መቶ ሚስቶቹ ጋር፡ ሰሎሞንም ከሺህ ጋር። ሰሎሞን፡ በስጋ የዳዊት ልጅ ነው፥ በመንፈሳዊውም፡ የዳዊት ልጅ የሆነውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነው። ይሄኛል ስጋዊ የሆነ፡ የወሲብ ህይወት ነው። ይሄኛው ግን መንፈሳዊ፡ የተፈጠረ፡ ስለዚህ፡ የተፈጠረ ነው። አያችሁ? መጀመሪያ ላይ እንደዚያ ነበር፡ አሁን እኛ በምንኖርበት በዚህ ህይወት ግን አይደለም።

205 አስተውሉ፡ ይህን ሳትረዱት አትለፉ፡ በልባችሁ ውስጥ አስገቡት። ነገር ግን ከእነዚያ ሴቶች መካከል አንዳቸውም ቢሆኑ ተጨማሪ ባል ማግባት አይችሉም። ኦሪጂናል ፍጥረት እሱ እንጂ፡ እሷ አይደለችም። ከእነዚያ ሴቶች መካከል ማናቸውም ቢሆኑ አንድ ተጨማሪ ባል ማግባት አይችሉም፡ ያንኑ አንዱ ባል ግን አንድ ሺ ሚስት ማግባት ይችላል። **የሰራዊት ጌታ**

**እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ነው። አሁን፡ ወደ ኋላ ተመልሼ፡ ጊዜ ወሰጄ ያኔ በመጀመሪያ ኢየሱስ እንደተናገረው፡ የተፈጸመውን ነገር አሳይቻችኋለሁ። አሁን በግልጽ ይታያችኋል አይደል? የቻሉትን ያህል ማግባት...

206 "ኦህ፡" እናንተም "ያ ለእስታኤል ነበረ፡" ብላችኋል። እንደዚያ ነውን?

207 አብርሃም ሣራን ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር ባወረዳት ጊዜ፡ አቤሜሌክ የሚባል ንጉሥ ነበረ። ሣራም፡ ድፍን የመቶ ዓመት ልጅ ነበረች፡ ነገር ግን ወደ ቈንጆ ወጣት ሴት ስለተለወጠች ውብ ሆናለች። ያን ታውቁታላችሁ አይደል? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እሺ። አቤሜሌክም ሚሰት ትሆነው ዘንድ ፈልጎ ነበር። በዚህ ላይ መልእክቴ ታሰታውሳላችሁ? አቢሜሌክ ሣራን ለትዳር ሊወሰድ ፈለገ። ምናልባት ሌላ መንጋ ያህል ይኖረው ይሆናል፡ ለአብራሃም የተጋባች ከሆነች ግን ሊወሰዳት አይችልም። ስለዚህ አብራሃም ሳራን "አንቺን ለመውሰድ እኔን እንዳይገድለኝ፡ 'ወንድሜ ነው፡' በይ፡" አላት። አብርሃምን ከሀገር አሳድዶ፡ ሚሰቱን ይዞ ለምን አልሄደም? ሕግ በአማኞች ዘንድ ብቻ ሳይሆን፡ በፍጥረት ውስጥ ላሉ ሰዎች ሁሉ ነበር። ሰው ሆይ፡ ኃጢአተኛም ይሁን ቅዱስ፡ ስለ እነዚህ ድርጊቶች፡ ተጠያቂ ነህ። አረማዊ ንጉሥ ነበረ። ያ ታሪክ እውነት መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ? ["ኣሜን።"] መጽሐፍ ቅዱስ፡ ከዘፍጥረት፡ 16ኛው ምዕራፍ፡ ይመሰለኛል።

208 እንዳያችሁት፡ አቢሜሌክ ሚሰት አድርጎ ሊወሰዳት ይችል ነበር። ይህችን አዲስ ዕብራዊት ሴት ለማግባት ተዘጋጀ። እንዲህ አለ፡ "እሷ እህቴ... " እንዲህ አለች፡ "ይህ ወንድሜ ነው።"

እሱም "እህቴ ነች፡" አለ።

209 አቢሜሌክም እንግዲያውሰ "ሚሰት እንድትሆነኝ እወሰዳታለሁ፡" አለ። አንድ ሰው እንዲህ ያለ ነገር ሲያደርግ መገመት ትችላላችሁን? እሱ ግን አደረገ።

210 በዚያችም ሌሊት፡ ተኝቶ ሳለ፡ ጌታ በሕልም ተገለጠለት፡ እንዲህም አለው፡ "አቢሜሌክ፡ እንደ ሙት ሰው ነህ።" እያችሁ፡ ያንን የአይሁድ የደም ሐረግ፡ እየከለከለ ነበር። "የሌላ ሰው ሚሰት ለማግባት እየተዘጋጀህ ነህና። አንተ እንደ ሞተ ሰው ነህ፡" አለው።

211 እርሱም፡ "ጌታ ሆይ አንተ የልቤን ቅንነት ታውቃለህ፡" አለው። "እሷ ራሷ 'ወንድሜ ነው' አላለችኝምን? እሱ ራሱሰ 'እህቴ ናት' አላለኝምን? " አለው፡

212 እንዲህ አለው፡ "የልብህን ቅንነት አውቃለሁ፡ ስለዚህም በፊቴ ኃጢአት እንድትሠራ ያልፈቀድኩልህ ለዚህ ነው።" ልክ ነው? አለውም፡ "ሚሰቱን መልሰለት፡ ያ ሰው የኔ ነቢይ ነውና። ሚሰቱን ካልመለሰክለት በሰተቀር... ቁሰህ ሳይሆን፡ እርሱ ካልጸለየልህ በቀር። እሱ ካልጸለየልህ በቀር፡ ህዝብህ በሙሉ ይጠፋል።" አሜን። ይኸው ግሩም ጸጋው። በእውነት። "ህዝብህ በሙሉ ይጠፋል። የሰውዬው ሚሰት ናት፡ እርሱም የራሴ ነብይ ነው።" አሜን። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል**። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው። በእውነት።

213 አሁን ሞት፡ መከሰቱን አውቀናል። ሞት የሴቲቱ የኃጢአት ጠንቅ ነው፡ በሴት በኩል እንጂ በወንድ አይደለም። በአኗኗሯ፡ እና በእሷ፡ ሞት ሁሉ መጣ።

ሕይወት የምትሰጥበት መንገዷ ሞት ነው። ስንቶች ታውቃላችሁ? ቃሉን መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ኢዮብ 14 ላይ ነው።

214 ጥያቄ ከፈጠረባችሁ፡ ለእያንዳንዷ ነገር መጽሀፍ ቅዱሳዊ መልስ አለኝ፡ አዘጋጅቻለሁ።

215 ኢዮብ 14 ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ እንዲህ ይላል፡ “ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ቀን ነው፡ መከራም ይበዛዋል።” ልክ ነው? “እንደ አበባ ይወጣል፡ ይረግፋልም፡ ተቆርጦም ይጣላል፡” ወዘተረፈ። አያችሁ? ከሴት የተወለደ ወንድ ሁሉ፡ እንደመጣ በሞት ይወለዳል።

216 ወደ እግዚአብሔር ፍጥረት ሲወለድ ግን፡ ሊሞት አይችልም፥ እርሱ በኤደን ገነት ከነበረው ከሌላኛው ዛፍ፡ ከክርስቶስ ነው። የዘላለም ሕይወት ከዚያ ዛፍ ነውና።

217 “ኦህ፡” “ዛፍ ነበረች፡” ብላችኋልን? አዎን። “እንደው፡ ‘ከዚህ ዛፍ አትብላ፡’ ይላሉ። እግዚአብሔር በዘፍጥረት፡ እንዲህ አለ፡ ‘ከዚህ ዛፍ እንዳትበላ።’”

218 እንግዲህ፡ ሴቲቱ ዛፍ ነበረች። የምታፈራ ዛፍ ናት። እናንተ የእናታችሁ ፍሬ ናችሁ። የማሕጸን ፍሬ እናንተ ናችሁ። በትክክል። ሌላ ደግሞ በኤደን ገነት የነበረው፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ፡ ክርስቶስ ነው። ሞት በሴቲቱ በኩል መጣ፡ በመጀመሪያ ፍጥረት፡ በሰውዬው በኩል፡ ሕይወት መጣ። ከሴት መወለድ ሞት ነውና፥ ከክርስቶስ መወለድ ሕይወት ነው። ሃሳቡን ገባችሁ? ከዚያ ነው። አሁን አማልክቶቹ ወዴት እንደሄዱ፡ አሁን አይታችኋል?

219 ፊተኛው አዳም እና ሔዋን የሁለተኛው አዳም እና ሔዋን ጥላዎች ናቸው፡ መራባት፡ እዩት። አሁን ምድርን ለመሙላት የአዳምና የሔዋን መራባት ግን፡ በወሲብ ሆነ፡ በመጀመሪያ ግን እንዲህ አልነበረም። እግዚአብሔር ልክ እንደ ሌሎች ፍጥረታቱ፡ ወንድና ሴትን ብቻ አደረገ፡ አያችሁ፡ ሕግ፡ ልክ እንደ ቤተ ክርስቲያን።

220 አሁን በተገለጠው በእግዚአብሔር እውነት ፊት፡ እንዲህ እናድርግ፡ ከፈለጋችሁ፡ ዘልቃችሁ ተመራመሩ። [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] እሺ። አሁን ወደ ታች እስክንደርስ ድረስ ይህ ትንሽ ሊጎዳችሁ ይችላል፡ እኔ ግን እውነታውን ብቻ አሳያችኋለሁ።

221 መበለት የሚያገባ አገልጋይ የለም። ይህን ታውቃላችሁ? ማንበብ ትፈልጋላችሁ? እሺ፡ ሌዋውያን፡ ዘሌዋውያን 21፡7 እና ሕዝቅኤል 44፡22 አውጡ፡ እና ስለ ክህነት በወንድ የተነካች ሴት ማግባት እንደማይገባቸው ያሳያል። ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ድንግል የሙሽራው ጥላ ነው፡ ምክንያቱም ክሃናት፡ የአሮን ልጆች፡ የእግዚአብሔር እሳት የሚያቀርቡ እነሱ ናቸውና። እኩለ ቀን ላይ ለመውጣት፡ ሁሉንም ለማንበብ ጊዜ አናገኝም፡ ገና ሃያ ደቂቃ አለን። የእግዚአብሔር እሳት—የሚያቀርቡት—የአሮን ልጆች ነበሩ፡ ሌላ ወንድ የነካትን ሴት ማግባት አይችሉም ነበር። የማይለወጥ አምላክ ብሏልና። ማየት ከፈለጋችሁ፡ በጥላ እንደሚታየው፡ ሌላ ሴት አያገቡም፡ በሌላ ወንድ የተነካኝ ሴት አያገቡም፡ ይህም የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ንጹህ፡ ያልተበረዘች፡ የእግዚአብሔር ቃል መሆኗ፡ እና በሰው የምትመራ የሐይማኖት ተቋም አለመሆኗ የሚያሳይ ነው።

222 ማስታወሻ፡ እዚህ ጋር እናንብብ። ይህን ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ። ማቴዎስ 5፡ ኢየሱስ እዚህ ላይ ስለ አንድ ጠቃሚ ነገር ተናግሯል። እስኪ እንየው፡ ማቴዎስ 5 ላይ። እዚህ ላይ ጽፌያለሁ...

223 ለወንዱ መናገር የምፈልገውን ነገር ጽፌ ይዣለሁ፡ ስለዚህ በእህቶቻችን ፊት ለመናገር ትንሽ ጊዜ አለኝ። ይሁን እንጂ—ይህ ነገር ከመሆኑ መውጣት እፈልጋለሁ...

224 አሁን፡ እህቴ ሆይ፡ እግዚአብሔር ቃል በገባልሽ ሰፍራ እንዳስቀምጥሽ እፈልጋለሁ፡ ስለዚህ አንቺም፡ ሰፍራሽን ጠብቂ።

225 ማቴዎስ 5፡32። "አንድ" እና "ብዙ" የሚለውን አሳብ ለማጠናከር፡ እዚህ ላይ እንድታሰተውሉ እፈልጋለሁ። ማቴዎስ፡ ሠላሳ-... ለመጀመር ማቴዎስ 5:32፣ 31 ይመስለኛል።

**ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ፡ የፍችዋን ጽሕፈት ይሰጣት፡ ተባለ፥**

226 ይህ ማለት ኢየሱስ፡ "ከመጀመሪያው፡" ብሎ ከተናገረው ነው። አሁን ተከታተሉ።

> **እኔ ግን እላችኋለሁ፡ ያለ...** ዝሙት **ምክንያት፡ ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ፡ አመንዝራ** ያደርጋታል፥ ... (ተመልከቱ) **ያለ... ዝሙት** ምክንያት፡ **ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ፡ አመንዝራ ያደርጋታል፥** (ለምን? እንደገና ታገባለችና።) **እና የተፈታችውን** የሚያገባ **ሁሉ** ያመ**ነዝራል።**

227 አያችሁ፡ በሕይወት ያለ ባል አላት፡ ስለዚህም ማንም ሊያገባት አይችልም። ማን ናት ስራዋ ምንድነው አይገደኝም፡ ባልዋ በሕይወት ካለ፡ ምንም ምክንያት አይኖራትም። ለእሱ፡ ግን፡ እንዲህ አይደለም። "ጫናው በእሷ ላይ፡" እንጂ በሱ ላይ አሰራም። ገባችሁ? ቃሉ እንዲቀጥል ማድረግ አለባችሁ። አያችሁ፡ እሷ አትችልም እንጂ፡ እሱ አይችልም የሚል ነገር የለም። አያችሁ፡ "ጫናው በእሷ ላይ፡" እንጂ በሱ ላይ አሰራም። መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው ይህ ነው፡ "ጫናው በእሷ ላይ።" እንደገና እንዳያገባ ክልከላ በሱ ላይ አልተደረገም፡ "በሷ" እንጂ። ለምን? ክርስቶስን በጥላ።

228 ልብበሉ፡ ድንግል ብቻ እንጂ፡ ሌላ ማግባት እንደማይችል ተነግሯል። እንደገና ማግባት ይችላል። ይችላል-... ድንግል ከሆነ እንደገና ማግባት ይችላል፡ የሌላ ሰው ሚስት ማግባት ግን አይችልም። በእርግጥም አይችልም። እና የተፈታች ሴት ቢያገባ፡ በዝሙት እየኖረ ነው፡ ማን መሆኑ ግድ የለኝም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፡ "የተፈታችውን የሚያገባ ሁሉ፡ ያመነዝራል።" ይኸውላችሁ እንግዲህ፡ የተፈታችሁቱ አይቻልም።

229 ኦሪጂናሉን መለስ በሉና እዩት፡ "ከመጀመሪያው፡" አሁን? እንደገና ማግባት፡ ልብ በሉ፡ እሱ ይችላል፡ እሷ ግን አትችልም። እንደ ዳዊት፡ እንደ ሰሎሞን፡ እንደ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ይቀጥላል፡ ማለት፡ ልክ እንደ ዳዊትና እንደ ሌሎቹ።

230 አሁን 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡10 ላይ፡ አስተውሉ፡ ጳውሎስ ባሏን ስለምትፈታ ሚስት፡ ትእዛዝ አስተላልፏል፡ ከባልዋ ጋር ትታረቅ ወይም ሳታገባ ትቅር እንጂ፡ ዳግም መጋባት አትችልም ብሏል። ሳታገባ መቆየት፡ ወይም ከባልዋ ጋር መታረቅ

አለባት። እንደገና ማግባት አትችልም። አስተውሉ፡ ስለ ወንዱ አልተናገረም፡ ስለሷ ግን፡ ሳታገባ ትኑር አለ። አያችሁ፡ ቃሉን ውሸተኛ ማድረግ አትችሉም። “ከመጀመሪያው፡” ከአንድ ሚስት በላይ በማግባት በሆነ የጾታዊ ፍትወት ሕግ ነው። አሁን፡ የእግዚአብሔር ቃል ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ጋር በእኩል ይጓዛል፡ ቀጣይነቱን ያስቀጥላል።

231 አንደኛው እሳቤ ወደ ምስራቅ፡ ሌላኛውም ወደ ምዕራብ እንዴት እንደሄደ፡ አያችሁ? ምን እንደሆነ ለማወቅ፡ ወደ እውነት መመለስ አለባችሁ።

232 ሁልጊዜም እንደዚያ ነበር፡ ያ ከመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው መደበኛ ቃል ኪዳን ነው። **በመጀመሪያ፡** ከመጀመሪያው በፊት፡ ሲጀመር አንድ ለአንድ ብቻ ነበር። **በኋላ** ኃጢአት ገባ፡ አንድ ወንድ ለብዙ ሴቶች ሆነ፥ ይህን ከተፈጥሮ ለመረዳት ሞክሩ፡ እንስሶች ሁሉ፡ እና ሰዎች ተፈጥሮአዊ ሥጋ ለባሽ የሆነ ሁሉ እንስሳ ነውና። ሁላችንም፡ አጥቢዎች ነን፡ እናውቀዋለን፡ ይህም፡ ቀጣይነት ያለው የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ነው።

233 አሁን ግን ማኅተሞቹ ስለተከፈቱ፡ የእውነት መንፈስ ወደ ቃሉ ይመራናል። ይህ ማለት ማህተሞቹ አለመከፈታቸው፡ በዘመናት ሁሉ ላይ የነበረኡ ስሕተቶች ለምን እንደሆኑ ያብራራዋል፡ አልተገለጠም ነበርና። በትክክል።

234 ይኸውላችሁ፡ ጥላውን፡ ውሸት ማድረግ አይቻላችሁም። ትናንት ማታ ወለል ላይ ስለሚታየው ጥላ እንደሰበኳችሁ፡ በትክክል መውጣት አለበት። ወለሉ ላይ የሚታየው የዝሆን ጥላ ሆኖ ሳለ፡ በዝሆኑ ፈንታ፡ እንዴት አነስተኛና ሚጢጢ ሰው ይሆናል፡ ወይስ ዝሆኑ፡ ሚጢጢ ሰው እንዴት ሊሆን ይችላል?

235 አሁን ከቻላችሁ በትክክለኛው ጥላ ተመልከቱት።

236 አሁን፡ ባሏን አግብታ፡ በሕይወት የምትኖር፡ እውነተኛ ሴት፡ እውነተኛና፡ ድንግል ሴት፡ ለባልዋ በረከት ናት። እግዚአብሔር ለልጁ ከሚስት የተሻለ የሚሰጠው ነገር ቢኖሮ፡ ይሰጠው ነበር።

237 እሷ ግን የጾታዊ ፍትወት ሰራ ሆና የተነደፈች ንድፍ ናት፡ በሌሎች እንስሶች ዘንድ በዚህ መልኩ የተነደፈ ፍጡር የለም። በምድር ላይ እንደዚህ ያለ ሌላ ንድፍ ያለው ፍጥረት የለም። ከአንድ ሚስት በላይ የሚያገቡትን የምታዩአቸው፡ በዚህ ምክንያት ነው። ያ ነው ያመጣው።

238 እንግዲህ ተመልከቱ፡ በዚህ በመጨረሻው ትንታኔ ላይ፡ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ (ልክ ነው? )፡ አንድ ሰው፡ አምላክ፡ አማኑኤል እንዳለ ተመልከቱ። ይህን ታምናላችሁ? በሚስቱ አካል ውስጥ ያሉ አባላት ግን ብዙ ናቸው፡ አያችሁ፡ ሺህ ሲባዛ ሺህ ጊዜ ሺህ ናቸው (ልክ ነው? )፡ ሚስቱ፡ ማለት ሙሽራይቱ፡ ቤተ ክርስቲያን። አሁን ገባችሁ?

239 ለዛም ነው ለአዳም፡ ገና የፆታ ግንኙነት ከመፈጠሩ ወይም ከመተዋወቁ በፊት፡ “ተባዙ፡ ምድርንም ሙሏት፡” በማለት ገና በመጀመሪያ፡ ገና በራሱ ወንድና ሴት ሳለ ተናገረው። ያኔ ገና፡ ሙሽራይቱ ከቃሉ መምጣት እንዳለባት ያሳያል፡ ይህም፡ በመንፈሳዊ መባዛት፡ ተራብተው፡ ምድር በሞሙላት ነው።

240 አሁን፡ በዚህ የጾታዊ ፍትወት ሰራ ላይ፡ ሁለቱ እሳቤዎቹ እነዚህን ሁለት ነገሮች ይቀላቅሏቸዋል። ስለዚህ ይህን ማድረግ ስለማይቻላችሁ፡ ወደ እውነቱ መመለስ አለባችሁ፡ ወደ “መጀመሪያው።”

241 እና በመጨረሻ አንድ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ይኖራል፡ ሙሽራይቱም፡ ብዙ የሆነች አንድ ትሆናለች። ገባችሁ? በአንድ ዙፋን ላይ አንድ ዳዊት፡ አንድ ንጉሥ ነበረ (እንደ እግዚአብሔር ልብ) ለእርሱም አምስት መቶ ሚስቶች ነበሩት። ኢየሱስ በሺው ዓመት መንግስት፡ (ሃሌሉያ!) ከሚስት ጋር ሲቀመጥም፡ እንደ መጀመሪያው፡ በልዑል እግዚአብሔር እጅ፡ ከምድር እንደ ተፈጠረው፡ በትንሣኤ፡ በብዙ አባላት ይኖሩታል። ይኸው።

242 ይህን ለመሆን የምትታገሉ፡ ሴቶች ሆይ፡ ወደ ክርስቶስ ቅረቡና፡ ከእንግዲህ ወዲያ በዚያ እርኩሰት ውስጥ አትገኙም። ነገር ግን በሥነ ምግባር እና በመልካምነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ አባል ሆኜ እኖራለሁ፡ የምትሉ ከሆናችሁ አትገቧትም። ወንዶችም ብትሆኑ አለ ክርስቶስ አትገቡም። ጳውሎስም እንዲህ እንዳለ፡ "በዚያ፡ በክርስቶስ ግን፡ ወንድም ሴትም የለም።" ሁሉም አንድ ናቸው።

243 ነገር ግን ይህ **ጋብቻ እና ፍቺ** ነገሩን ለማቃናት፡ እናንተም የትኛው ትክክለኛ የትኛው ስህተት እንደሆነ እንድታውቁ፡ አሁን በነዚህ ጥላዎች በግልጽ አሳያችሁ። አንድ ክርስቶስ አለ፡ በሚስቱም ብዙ አባላት አሉ። ልብ በሉ፡ ስለመንፈሳዊ ዝሙት እና ስለ ሐሰተኛ ትምህርት፡ በፈለገው ጊዜ ሊያርቀን ይችላል፥ እናንተስ እሱን ፈትታችሁ፡ እንዴት ትወጡታላችሁ? ሰውየው ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት ይችላል፥ ሴቲቱ ግን ባሏን ፈትታ ሌላ አታገባም። ጥላዎቹ እና ተምሳሌቶቹ ሁሉ በፍጹም ሚዛናዊነት አይታዩአችሁምን? ኦሪጂናሉን ፍጥረት እንጂ፥ ተረፈ-አካሉ የትም አይታይም። ቤተ ክርስቲያኒቱ ሳትሆን፡ በቃሉ በኩል የሆነችው ሙሽራ። ሴቲቱ ሳትሆን፥ ሁሌም፡ ሰውዬው ነው። ለዚህም ነው ሰውዬውን ያንን ስለማድረግ በፍጹም ነቅፎት አያቅም፥ ሁሌም ሴቲቱን ነው። በትክክል።

244 እንዲህ በመሆን… የክርስቶስ ሙሽራ ልትሆን ትችላለች፡ አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የወንዱ አካል በመሆን፡ እንደምትችል ተናግሯል-… "ነገር ግን ሴት ዝም እንድትል እንጂ፡ እንድታስተምር ወይም ማንኛውንም ሥልጣን እንዲኖራት፡ አልፈቅድም። አዳም አስቀድሞ ተፈጠረ፡ በኋላም ሔዋን። አዳምም አልተታለለም፡ ተረፈ-አካሉ ግን ተታለለ። ነገር ግን በቅድስና እና በጭምትነት፡ እና በመውለድ፡ እና በመሳሰሉት ሁሉ **ከ**ቀጠለች ትድናለች።" ምክንያቱም ከዚያ በኋላ የሰውየው አካል ትሆናለች። ይህ ይቋጨዋል…

245 ለምን እግዚአብሔር አብራሃምን… ማለቴ ሣራን እዚያ ተቀምጣ፡ በፊቱ ስትዋሽ፡ እግዚአብሔር ለምን አልገደላትም? እንደ ሚች ሰው ተቀምጦ፡ ሥጋ በላ፡ እንጀራ በላ፡ ወተት ጠጣ፡ እሷም ከኋላው፡ በድንኳኑ ውስጥ ነበረች፡ ፈጽሞ ሳያያት፡ እንዲህ አለ፡ "ሳራ በዚያ ውስጥ ሆና ለምን ሳቀች፡" "'ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?' ብላ ነበርና፡"

246 እሷ ግን "አላልኩም፡" አለች! ኦህ፡ ወይኔ፡ አቤት! እግዚአብሔርን ፊት ለፊቱ ውሸታም ነህ ትለዋለችን? ይሁን እንጂ ሊገድላት አልቻለም። ለምን? የአብራሃም አካል ናትና። አሜን። አብራሃምን ሳይጎዳ አልፎ አይጎዳትም።

247 አሁን እናንተ ሴቶች ሰፍራችሁ የት እንደሆነ ተመልከቱ። መጽሐፍም አለ፡ "እናንተ ሴቶች ሆይ፡ ሣራ ደግሞ በልክ እራሷን እንዳጌጠች፡ ለባሏ በእውነት እና

በታምኝነት እንደኖረች፡ እርሱን ‘ጌታዬ’ ብላ እስከመጥራት… እንደወደደችው እናንተም እንደሷ ሁኑ፡” ገዥ፡ ባለቤት።

248 እናንተም፡ አንዳንዶቻችሁ ሴቶች፡ እራሳችሁን በወንዶች ፊት ለማራከስ እነዚህን የከረፉትን ልብሶች ትለብሳላችሁ። ኢየሱስም “ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፡” አለ። ታዲያ ጥፋተኛው ማን ነው፡ ሰውዬው ወይስ እናንተ? እሱ ይህን ድርጊት እንዲፈጽም የተሰራ፡ ወንድ ነው፡ አያችሁ፥ እምቢ ማለት ያለባችሁ፡ እናንተ ሴቶች ናችሁ።

249 እራሳችሁ እንደዚያ ማሳየት ለምን አስፈለጋችሁ? አጫጭር ልብሶች ለብሳችሁ ግማሽ አካላችሁ እስኪሞት ድረስ እየበረዳችሁ፡ ይህ ሊሆናችሁ እንደማይችል፡ ለምቾት እንደማይሆናችሁ ታውቃላችሁ። አያችሁ፡ ለምቾት ሊሆን አይችልም። ታዲያ ምንድን ነው? ለእርኩሰት ነው! ማመን አትፈልጉም፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ያለው ነው። እውነት ነው። በውስጣችሁ የገባ እርኩስ መንፈስ ነው። እርኩስ መሆን አትፈልጉም፥ መንፈሳዊ እርክሰና ውስጥ መሆናችሁ ግን፡ አትገነዘቡም፡ እራሳችሁን እርኩሰት አድርጋችሁ ታቀርባላችሁና።

250 አሁን፡ አንድ ወንድ፡ ያረጀ፡ የቆሸሸ፡ የተሸበሸበ ጉልበቱ፡ እየታየ እርቃኑን ቢወጣ፡ ምንም ለውጥ እያመጣም፡ ሰውነቱ የሚፈትን አይደለም። ለምን? በኦሪጂናል ፍጥረት ስለነበረ፡ በባህርይ፡ ሊሆን ይገባል፡ አያችሁ። እናንተ ግን፡ መፈተኛ፡ የምርት-ውጤት ናችሁ።

251 እግዚአብሔር ሆይ፡ ከኃጢአተኛው ዓለም! ኦህ፡ ማይ፡ አቤቱ ማረን! ይህ ሲያበቃ እደሰታለሁና።

252 አስተውሉ፡ ሚስቱን በፈለገ ጊዜ ሊፈታት ይችላል፡ እሷ ግን ልትፈታው አትችልም፥ ሊሰራኝ ይችላል፡ በፈለገ ጊዜም ወደ አፈር ሊመልሰኝ ይችላል፡ እኔ ግን፡ ወንድሜ ሆይ፡ እሱን ለመጣል፡ አለመሞከር ይሻለኛል፡ ያበቃልኛልና።

253 ሰሎሞን ያላገባችውን ማንኛውንም ሴት ማግባት ይችላል፡ የፈለጋትን ሴት ማግባት ይችላል። ካህን ማግባት የሚችለው ድንግል የሆነችውን ሴት ብቻ ነው። ሰለሞን…

254 ዳዊት፡ ያገባት (ሰሟ ማን ነበር? ) አቢግያ። መልካም ሚስት የነበረችው፡ “ምናምንቴ፡” የሆነ አንድ ሰው ነበረ፡ እርሱም ሞተ። አቢግያም ለዳዊት ተዳረች፥ ንጉሥ እንጂ ካህን አልነበረምና፡ ካህን አልነበረም፡ አያችሁ፡ ሰ—ሰለዚህም አገባት።

255 ካህን ግን ያን ማድረግ አይችልም፡ ምክንያቱም ቀድሞውንም የሰው ሚስት የነበረችውን ሴት ነክቷል ወይም ሚስቱ ትሆነው ዘንድ ወሰዷልና ይህ አይቻልም። ይህም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ድንግልና ያሳያል፡ ሙሽራይቱ፡ ቃሉ፡ ያልተበረዘች መሆን አለባት፡ በምንም መልኩ አንዲት ቃል መጉደል የለባትም። በትክክል። አሰቡት እስኪ ትክክለኛ ሙሽራ ሆና፡ አንድ ጡቷ የተቆረጠባት፡ ሁለተኛውም፡ በሆነ መንገድ፡ ችግር የገጠመው፡ እስኪ አሰቡት? የክርስቶስ ሙሽራ እንዲህ አትሆንም። እሷ ፍጹም ነች። እሷ የቃሉ ሙላት ናት፡ አንዲት ቃል በምንም አትጎድላትም። በጭራሽ።

256 አስተውሉ፡ እሱ ሊፈታት ይችላል፡ እሷ ግን ልትፈታው አትችልም። በሉተር፡ ዌስሊ፡ እና በጴንጤቆስጤ በነበሩበት ዘመናት፡ ይህን አድርጓል፡ አረጋግጧል፡ በመነፍሳዊ የፍቅር ጨዋታ ቃሉ ላይ በመቀጠል አናረግዝም ከእንግዲህ ወዲህ አካልህ አንሆንም ባሉት ጊዜ አረጋገጧል። ገባችሁ? እምቢ አለችው። የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ከእርሷ ጋር ምንም ፍላጎት እንዲኖረው አልፈለገችም፥ ሉተር እምቢ አለ። በተጨማሪም፡ መሰደቤ ላይቀር እንዲህ ልበላችሁ፡ ሌሎቹም ሁሉም እንዲሁ ናቸው፡ ቃሉን አንቀበልም ብለዋል፡ ክርስቶስን እምቢ ብለዋል።

257 ባልዋን ልጆች አልወልድልህም የምትለዋ የትኛዋ አይነት ሴት፡ ሚስቱ የመሆን መብት የላትም። አሜን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ንጉሡ አስቴርን ሲያገባ፡ ታስታውሳላችሁ? ንግስቲቱ እምቢ በማለቷ ምክንያት፡ ሌላ አመጡለት። እምቢ ባለች ጊዜም... ወደ ንጉሡ ዘንድ አልወጣም ብላ ባልታዘዘች ጊዜ ምን ሆነ? ለባሏ ሚስት ለመሆን ፈቃደኛ በማትሆን ሴትም እንደዚሁ ነው።

258 አሁን ባለንበት ዘመን የዘመኑ ልጆች ለመውለድ እምቢ አልጸንሰም የምትል፡ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ናት። እኛ ሉተራኖች አይደለንም፡ ዌስሊያውያን አይደለንም፡ ጴንጤዎችም አይደለንም! በእግዚአብሔር ቃል እርግዝና፡ የዘመኑ ልጆች ማለት የዘር ልጅ፡ መውለድ እንድንችል፡ የዚ ዘመን ልጆች መሆን አለብን። አሜን። እንደምትረዱት ተሰፋ አደርጋለሁ። ማስጸነስ ካልቻለ፡ ካልሆነለት፡ ምን ያደርጋታል? በፍች፡ ይሸኛታል። በትክክል። እሷ እሱን መሸኘት ግን አትደፍርም። እሱ ይሸኛታል እንጂ።

259 ለአካሉ ቃሉ እየገለጠላት፡ እና በተመሳሳይ መልኩ፡ እራሱን፡ በምስክር እያሳያት ቀጠለ። ልጆቹም እሱን መምሰል ጀመሩ፡ ምክንያቱ ሙሉ በሙሉ የሚያበስል ነውና፡ ወይም፡ የቃሉ ልጆች ያደርጋቸዋል፡ የቸርች ልጆች አይደሉም። የቃሉ ልጆች እንጂ! ሙሽራይቱም የተዋበች በየትኛውም የሰው ድርጅትና፡ በሰው-ሰራሽ ጽንሰ ሀሳብ ያልተነካካች፡ ያልተበረዘች የቃሉ እመቤት ትሆናለች። ሙሉ በሙሉ፡ ያልተበረዘች የቃሉ ሙሽራ ትሆናለች! አሜን አሜን! በስልክ መስመር ያላችሁ፡ ይህን እንደተረዳችሁት ተሰፋ አአርጋለሁ። የፀነሰች የእግዚአብሔር ልጅ ትሆናለችና።

260 እንግዲያውስ ሴት ምን የከበረች መሆን እንደምትችል ታያላችሁን? ቤተ ክርስቲያን ምን ያክል ታላቅ መሆን እንደምትችል፡ ይሁን እንጂ እርኩሰት እንደገባባት አያችሁን? ስለዚህ ያን ቤተ ክርስቲያን እዚህ ካለችው ቤተክርስቲያን ጋር ለማነጻጸር በመሞከር፡ ይህን ማድረግ አትችሉም። የጎዳና ላይ ጋለሞታ ከሕያው ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ጋር፥ ወይም እመቤት፡ ትክክለኛዋ እመቤትን፡ ከጋለሞታ ጋር ማነጻጸር ትችላላችሁን?

261 እንደዚህ ያሉ ነገሮች ለምን ኖሩ? የንጽጽር ሕግ፡ የእግዚአብሔር ህግ ነው። ሌሊት ከሌለ በቀን ብርሃን መደሰት እንዴት እናውቃለን? ዝናብ ከሌለ በደረቁ አየር መደሰት እንዴት እናውቃለን? የቆሸሸች ሴት ከሌለች፡ በእውነተኛ ሴት መደሰት እና ማክበር እንዴት እናውቃለን?

262 ስለዚህ እየገለጠው፡ ቃሉ እየገለጠው ቀጠለ፡ ነገር ግን ማናችንም ብንሆን እሱን ለመተው እና ሌላ ለማግባት እንሞክር።

263 አሁን ሁለቱም እሳቤዎች ለምን እንደተሳሳቱ ግልጽ ነው። **በዚህ** መንገድ ማስኬድ አይቻላችሁም፡ የለምና፥ **በዚያ** መንገድ ብትሞክሩም፡ ተስፋ ቃሉን አልፎ ይሄዳል። **እነሆ** የተሰፋው ቃል ይህ ነው፡ ነገሩ እዚህ አለ። ቃሉ አይቃረንም። ከማቴዎስ 28፡19 በላይ ከሐዋርያት ሥራ 2፡38 አይቃረንም፡ በዚህ መቀጠል አለበት።

264 አሁን፡ እንዳንዶቻችሁ ሴቶች፡ አንዳንዶቻችሁ ወንዶች፡ ይህን እ—እየተቃወማችሁ እንደሆነ አ—አውቃለሁ። ምክንያት፡ አሁን፡ መደበቅ እንደማትችሉ ታውቃላችሁ። አትችሉም።

265 ግን አንድ ነገር ላሳያችሁ። የማቴዎስ ወንጌል 28፡19 ላይ፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፡ በልጅና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ አስተምሯቸው፡" ብሏቸው ሳለ እርሱን ወደ ጎን ብለው፡ እነርሱ ሲያጠምቁ የተጠመቀ ሰው ሁሉ በተቃራኒው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቀው ከሆኑ፡ እንግዲያውስ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሁሉ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን በኋላ፡ ለሦስት መቶ ዓመታት እስከ ኒቂያ ጉባኤ ድረስ እንዲህ ነበር። እንግዲያውስ የራሳቸው ዶግማ መሰርተዋላ። ካልተገለጠ ግን፡ ልዩነቱ ምንድነው?

266 መላው መጽሐፍ፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስ፡ መገለጥ መሆኑን ታውቃላችሁን? በዚህ እና በሌላኛው መካከል ያለውን እውነት ማወቅ የሚቻላችሁ በዚህ መንገድ ነው፡ ምክንያቱም ይህ መገለጥ ነው። መገለጡም በትክክል ከቃሉ ጋር የሚስማማ እንጂ፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረን መሆን የለበትም። "ይኸው፡ ለእኔ፡ ተገልጦልኛል፡" ብላችሁ ከሆነ። ቃሉን የሚጻረር ከሆነ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም። በትክክል።

267 አሁን መጸፍ ከፈለጋችሁ ማቴ-... ማቴዎስ 16፡18 ላይ ነው። ኢየሱስ ራሱ፡ መላው ቤተ ክርስቲያን፡ ቤተክርስቲያኒቱ፡ በራሱ መንፈሳዊ መገለጥ፡ እርሱም በቃሉ ላይ እንደምትገነባ ተናግሯል። "እልሃለሁ፡ አንተ ጴጥሮስ ነህ... በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም ይህን ከቶ አልገለጠልህም። በዚህች ዓለት ላይም... "

268 አሁን፡ ማዶ ላይ ያሉ፡ የካቶሊክ ወዳጆቻችን፡ የምትሉትን አውቃለሁ፡ "በጴጥሮስ ላይ፡ ሐዋርያዊው ጴጥሮስ ላይ፡ ስለዚህ፡ በሐዋርያዊ እውቅና፡ የሚተካካኩ፡ **እከሌ-እና-እከሌ** ነው።"

ፕሮቴስታንቶች "የገነባት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው፡" ይላሉ።

269 የተለየ ለመሆን ፈልጌ አይደለም፡ ነገር ግን የተናገረውን ውሰዱ! እንዲህ ብሏልና፡ "በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም። በዚህች ዓለት ላይም" (ቃሉ ምን እንደሆነ በሚያስረዳ መንፈሳዊ መገለጥ) "ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ፥ የገሀነም ደጆችም አይችሏትም።" ሚስቱ ከሌሎች ወንዶች ጋር አትፈተንም። "ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ፡ የገሃነም ደጆችም በጭራሽ ሊያናውጧት አይችሉም።"

270 እንደገና አቤልና ቃየን፡ በኤደን ገነት ውስጥ። ቃየን የራሱን ፅንሰ ሀሳብ አወጣ፡ እንዲህም አለ፡ "እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ መልካም አምላክ ነው። እሱ በተፈጥሮ ሁሉ ላይ አለ፡ ስለዚህ ባቄላውን እና ድንቹን አመጣለሁ፡ አበቦችም—አመጣለሁ፡ ቆንጆና የሚያምር መሠዊያ አደርግለታለሁ።" ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ነው። ተንበረከከ። እግዚአብሔርን አመነ። እግዚአብሔርን

አመለከ፡ እጁንም ከፍ አደረገና፡ ይህን መሥዋዕት አቀረበ። አቤል ያደረጋቸውን ሃይማኖታዊ ነገሮች ሁሉ አድርጓል።

271 አቤልም ተመሳሳይ መሠዊያ ሠራ። አቤል የራሱን ባመጣ ጊዜ ግን፡ ጠቦት አመጣ። አሁን፡ ቃየን አባቱ እና እናቱ የበሉት ነገር ይህ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ሰላሰበ፡ የኃጢአት መድኃኒት፡ ይህ መሰለው፡ በዚያ በአትክልት ስፍራ ተምረዋልና። አቤል ግን፡ በመለኮታዊ መገለጥ፡ የዚህ ነገር ጠንቅ ደም መሆኑን አውቀዋል። በመለኮታዊ መገለጥ! መጽሐፍም በዕብራውያን፡ ምዕራፍ 12 ላይ፡ ምዕራፍ 11 ላይ እንዲህ ይላል፡ እንዲህ በማለት፡ "አቤል፡ በእምነት፡" (መገለጥ) "ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረበ፡ በዚህም እግዚአብሔር ጻድቅ እንደ ሆነ መሰከረ።" ልክ ነው? አሜን! ወንድም፡ እህቶቼ ሆይ፡ ለእኔ ሊሆን ከሚችለው በላይ ያህል፡ ግልጽ ነው። ነገሩ ሁሉ ይህ ነው።

272 አሁን ወደ **ጋብቻ እና ፍቺ** ስንመጣም፡ እያችሁ፡ ሊገለጥ ይገባዋል። እስኪገለጥ ድረስ፡ አታውቁትም። ነገር ግን በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ በዚህ ዘመን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደበቀ ምስጢር ሁሉ እንደሚገለጥ ቃል ገብቶልናል። ስንቶች ይህን ታውቁታላችሁ? ራዕይ፡ ምዕራፍ 10 ላይ! ኢየሱስ እነዚህ ሁሉ የተደበቁ ምስጢሮች ስ—ስለ **ጋብቻ እና ፍቺ፡** ስለ ሌሎቹም፡ ስለተደበቁ ምስጢሮችም ሁሉ፡ በዘመን ፍጻሜ እንደሚገለጡ ቃል ገብቷል። አሁን ድምጹ፡ "ወደ ቱሰን ሂድ፡" የሚል እንደነበረ አስታውሱ። በሰማያት የታየውን ምስጢራዊ ብርሃን ታስታውሳላችሁ? ሰባተኛው መልአክም በዚያ ቆሞ ነበር? በተመለስሁ ጊዜ፡ የሰባቱም ማኅተሞች መከፈት ነበር። ምን እንደተከናወነ ተመለከቱ። ይህ እውነት ነው።

273 አሁን ትንሽ ገፋ እናድርገው። አሁን ግን፡ በደንብ ስሙኝ! ሄዳችሁ ምግብ የምትበሉበት ሰዓት እየተቃረበ እንደሆነ አውቄአለሁ፡ እኔ ግን በደንብ እየበላሁ ነው።

274 ልብ በሉ፡ አሁን፡ ሴቲቱ የራሷ ስፍራ አላት፡ ደግሞም እሷ ጌጥ ነች። ይህ አሥር ሺህ ሚስቶች የነበሩት... ማለቴ፡ አንድ ሺህ ሚስቶች የነበሩት፡ ይህ ሰለሞን፡ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡ "ሚስትን ያገኘ፡ መልካም ነገር ያገኛል።" አለም፡ "መልካም ሴት በዘውዱ ላይ ጌጥ ናት፡" ይህም ክብር ነው። "ዓመፀኛ ሴት ግን በደሙ ውስጥ እንዳለ ውሃ ናት።" ይህም ህይወቱ ነው። እንዲህም አለ፡ "በሺህ መካከል አንድ ጻድቅ ወንድ ሊገኝ ይችላል፡" ብሏል ሰሎሞን፡ "ነገር ግን፡" አለ፡ "በሺህ መካከል ግን አንዲት ጻዲቅ ሴት አትገኝም።" ይህን ያለው ሰለሞን ነው፡ እያችሁ። አሁን ይህ እንዴት እንደሆነ፡ አስተውሉ።

275 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ሴቶች ሆይ፡ ጌ—ጌጥ መሆን ከፈለጋችሁ መሆን ትችላልችሁ፡ ፍላጎቱ ግን ከእናንተ መሆን አለበት። ስለዚህ ኢየሱስ ያኔ ብሎ ያመላከተበት፡ ያንን **ጋብቻ እና ፍቺ** ለምን እንደሆነ እዩት፡ ምክንያቱ የዚህ ሁሉ ጠንቅ ከእናንተ ወገን አንዷ ናት። ፖሊጋሚ እና ፍቺ፡ ሌሎች ነገሮችም፡ መተዋወቅ የቻሉት ምክንያቱ ይህ ነው። በመጀመሪያ ላይ በፍጹም እንደዚያ አልነበረም፡ በሚመጣው ዓለምም ፈጽሞ እንደዚህ አይሆንም።

276 ከእርሱ ዘንድ አባቶች የወጡት፡ ያዕቆብን ተመልከቱት። ቢያንስ ደርዘን ሚስቶች ነበሩት። ሁለት እህትማማቾችን አገባ፡ ከእነርሱ ሌላም ቁባቶች ነበሩት፡

አብረውት የሚኖሩ ሴቶች ጋር መሆን፡ የሁሉም-ሕግ ነበር። እነዚያም አባቶች የተወለዱት ከቁባት ሴቶች ነበር። ልክ ነው? አያችሁ፡ ቃሉ በትክክል መጥቀስ አለባችሁ።

277 ኦህ፡ ስለነዚህ ነገሮች አንድ ገጽ ሙሉ ይዣለሁና፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሐይማኖት ሰዎች ከጠየቃችሁኝ፡ አብረንም ከሆንን፡ ማውራት እንችላለን። ስለ እውነት ግን፡ ትንሽ መንፈሳዊነት ያለው ቢሆን፡ እውነቱን እዚሁ እንዳለ ማየት ይችላል። ምን አያጠያይቅም።

278 መልካም ሴት መልካም ነው። ይሄን አውቀዋለሁ። ከትክክለኛ ሴት አውቀዋለሁ። ልክ እንደማንኛውም ሰው እውነተኛ የሆኑ፡ እውነተኛ ሴቶች ያጋጥሙኛልና።

279 እሷ ተረፈ-አካል እና አካሉ ናት፡ በውድቀት ጊዜ እሷን ሰማ። እ... አካሉ ናትና። ነገር ግን፡ የሷ ምርጫ ነው፡ መርከስ የምትችል ተደርጋ ተሰርታለችና፡ እሺም እምቢም የማለት መብትም ተሰጥቷታል። ያ ግን በመጀመሪያ ከነበረው ኦሪጂናል ተፈጥሮ ተቃራኒ ነው፡ አያችሁ፡ ይሁን እንጂ ይኸው ነው።

280 አሁን አስራ ሁለት ሰአት ሆኗል፡ ስለዚህ ለጥቂት ደቂቃዎች እዚህ የሆነ ነገር ልተወውና። አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ።

281 አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህንን የምለው የራሴ ለሆኑት ብቻ ነው። እናንተ በሰልክ መሰመር ላይ ላላችሁ፡ ተከታዮቼ ለሆኑት ብቻ ይህን እላለሁ። ይህ መልእክት እና እዚህ የምናገረው ነገር ሁሉ፡ ለእነሱ ብቻ ነው።

282 ማንኛውም አገልጋይ፡ የእርሱ፡ በሆነው፡ እርሱ፡ የመንጋው እረኛ ነውና፡ የፈለገውን ያድርግ። ያ በእርሱ እና በእግዚአብሔር ላይ ነው። የትኛውም ቄስ፡ የትኛውም ሰባኪ፡ ወንድሜ፡ ያንተው ጉዳይ ነው።

283 እየተናገርኩት ያለሁት እዚህ በጄፈርሰንቪል ውስጥ ብቻ ነው፡ ይህ ቦታም መንጋዬ ያለበት ስለሆነ፡ የምናገርበት ብቸኛው ቦታ ነው። የበላይ ተመልካች እንድሆናቸው እንድረዳላቸው መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝ መንጋ ነው፡ ኃላፊነቱም እሸከማለሁ። እናም እነዚህ የእኔ የሆኑ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የመራኋቸው፡ ከአገሪቱ ሁሉ ዘንድ የተለወጡ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ፡ እናንተ ታናናሽ ልጆቼ ሆይ፡ እናንተን ለመርዳት መጥቻለሁና፡ ወዳጃችሁ ነኝ። እናንተን ተቃውሜ የምናገር ሊመስላችሁ ይችላል፡ አያችሁ፡ እኔ ይህን የምናገረው፡ ስለእናንተ ጥቅም ነው። እወዳችኋለሁ። ይህን እውነት ካልሆነ፡ እግዚአብሔር ዳኛዬ ነው። እንደምወዳችሁም እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ።

284 ይህ እጅግ ከባድና ኃይለኛ ነገር ነው፡ እንዴት እንደምናገረው አላውቅም ነበር። በጉባኤዬ ውስጥ አንዳንዶቹ ሁለቴ እና ሶስቴ ያገቡ፡ ወንዶች እና ሴቶች ተቀምጠው እያየሁ፡ ምን ላድርግ? መልካም ወንዶች እና ሴቶች፡ ከሁሉም! ይህን ምን አመጣው? ሐሰተኛ ትምህርት፡ ጌታን አለመጠበቅ፡ በትክክል።

285 “እግዚአብሔር ያጣመረውን፡ ማንም አይለየው።” ሰው ያጣመረውን አይደለም፡ ነገር ግን “እግዚአብሔር” አንድ ያደረገው! ቀሪ ዘመናችሁ፡ ሚስትህ እንደሆነች፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቀጥተኛ መገለጥ ተቀበል፡ አንቺም በተመሳሳይ መልኩ፡ የአንቺ እንደሆነ ተቀበይ። አያችሁ? ሰው ያጣመረው ግን፡ ማንም ሊለየው ይችላል። እግዚአብሔር ያጣመረውን ግን፡ ማንም ሊነካው

አይደፍርም። “እግዚአብሔር የሚያጣምረውን ሁሉ፡” “ማንም አይለየው፡” አለ። በሰካር ሞቅ-ያለው ዳኛ ያጣመረው አይደለም፡ ወይም በዓለም ባለው ነገር ሁሉ እንደፈለጉ እንዲሆኑ የሚፈቅድላቸው፡ ከእምነቱ የወደቀ በምጽሐፋ ውስጥ ብዙ የሐይማኖት መግለጫ የሞላ ሰባኪም አይደለም፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን በፊቱ አለ። አያችሁ? እኔ የምናገረው እግዚአብሔር ስላጣመረው ነው።

286 አሁን ይህን እላችኋለሁ። ስለምነግራችሁ ነገር እጅግ እጠነቀቃለሁ። እናንተ ሰዎች ሆይ በእናንተ ላይ ለመክበድ ፈልጌ አይደለም። ፓስተር የሆናችሁ ወንድሞቼ ሆይ፡ በእናንተ ላይ ለመክበድ ስለፈለግኩ አይደለም። ለእንደዛ አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ በእጄ ስለመሰጠቱ፡ ኃላፊነት እንዳለብኝ አውቃለሁ፡ ይህም… ማፈን አልችልም፡ እንዴት መናገር እንደነበረብኝ አላውቅም፡ ይህ ቅጂ ግን እንደሚያደርሰው አውቃለሁ… ኦህ፡ ማይ፡ ቢሮው ይከፈታል፡ እኔም እዘጋጅበታለሁ፡ ምክንያቱ ነገሩ ተነግሯልና። አያችሁ?

287 ልክ **በእባቡ ዘር** ላይ እንደሆነው ሁሉ፡ እውነት ስለመሆኑ ግን የተረጋገጠ ነው። እዚህ ጋር አንድ ጋዜጣ ይዣለሁ፡ ጋዜጣው ላይ፡ አሁን እንዳሉ ሴቶች… እና በ—በታላቁ… ዋናው ሥዕል በአንዳንድ ታላላቅ ሀገረ ሰብከቶች ዘንድ ይገኛል፡ እባቡ ሴትዋ እግር ላይ እየተሳበ ሲሄድ፡ እና በዙሪያዋ ሲራመድ ይታያል፡ ወንድ በጭራሽ ሊነካት እስከማይችል ድረስ ነገር፡ ግዙፍ እባብ ዙርያዋ ላይ ተጠምጥሞባት፡ ወዘተረፈ፡ ሁሉም ዓይነት ስሜቶች እና ነገሮች የተደራረቡባት ሴት ናት። ትክክልና እውነት ነው። እና እየባሰ ይሄዳል፡ እየባሰም ይቀጥላል። እባብ፡ እንደ እባብ ሆኖ ከእሷ ጋር… ጾታዊ ግንኙነት ሊያደርግ አይቻለውም፡ ነገር ግን ይህን አስታውሱ…

288 በቀደም ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ክርክር ገጥመን ነበር በ… በርግጥ ክርክር ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር ባርያዎች እና ረዳቶቻቸው ስብሰባ ላይ፡ “በዚህ ነገር ላይ፡ ተሳስተሃል፡” አሉኝ።

እኔም “እሺ፡ ሊሆን ይችላል። እናንተ እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ፡” አልኳቸው።

289 ከዚያም ቀጠለና፡ ስለ ጉዳዩ ማውራት ጀመረ። ገና ከጅምሩ፡ እሱ ራሱ ጠፋበት። እና አንድ የተናገረው ነገር ግን፡ እንዲህ ጠየቀኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ያ ዝርያ የት አለ? እግዚአብሔር ‘ሁሉም እንደየወገኑ’ ብሏልና። አሁን ያ በሰውና በአውሬ መካከል ነው ያልከው፡ ሳይንስ አሁን ሊያገኘው ያልቻለው የት አለ? የት ነው ያለው? ” እንዲህም አለ፡ “በምድር ላይ ነው ያለው? ቺምፓንዚ ነበር ወይ? ”

290 “አልነበረም፡ ምክንያቱም የቺምፓንዚ ደም ከሴት ጋር አይዋሃድም፡ ሌላ እንስሳ ከእሷ ጋር አይዋሃድምና። በጭራሽ፡ አይዋሃድም፡ ወይም ደግሞ የወንድ ዘርም—ከእንስት ጋር መዋሃድ አይችልም። በጭራሽ አይችልም።”

291 “ታዲያ እንስሳው የት አለ? እንግዲህ እግዚአብሔር፡ ‘ሁሉም እንደየወገኑ ያብቅል፡’ ብሏልና።”

292 አንድ ደቂቃ ብቻ ጠበቅኩት። መልካሙ መንፈስ ቅዱስም “‘እዚህ ነው፡’ ብለህ ንገረው፡” አለኝ።

አሁን፡ በመጀመሪያ እንዲህ ብዬው ነበር፦ "እንግዲህ፡ ምናልባት ጠፍቶ ሊሆን ይችላል።"

"ወንድም ብራንሃም፡ ግን'ኮ፡ እያወራን ያለነው፡ ስለ እግዚ አብሔር ቃል ነው፡ አይደለም'ዴ፡" ብሎ ጠየቀኝ?

293 እኔም "አዎን፡ ጌታዬ፡" አልኩት። እኔም አልኩት፡ "በርግጥ'ኮ፡ እንደ ዳይኖሰር እ—እና ሌሎች ግዙፍ ፍጥረታት፡ እና ሌሎቹ ሁሉ፡ እነሱ፡ እንደሚሉት፡ አጥቢ እንስሶች፡ ማለቴ፡ ግዙፍ ፍጥረታት፡ ጠፍተዋል፡ ወዘተረፈ ይላሉ።" "እንደዚያም ሊሆን ይችላል፡" አልኩት።

294 እሱም አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ የምንናገረው'ኮ ስለ ቃሉ ማረጋገጫ ነው። ኃጢአት ካለ፡ ማለት፡ ዋናው ኃጢአት አለ ካልነው፡ እሱም እዚህ መኖር አለበት።"

295 እኔም ጸለይኩ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ 'በሰው ፊት ስትቀርቡ፡ በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና፡ ምን እንናገራለን ብላችሁ አትጨነቁ ብለሃል።' ጌታ ሆይ፥ ምን ልበል? " ልክ እዚህ መድረክ ላይ፡ እንደማያቸው ራእዮች ነበር። "እዚህ ነው፡ ብለህ ንገረው፡'" አለኝ።

296 እኔም የት እንደሆነ ሳላውቅ፡ "እዚህ ነው፡" አልኩት።

እሱም "የት፡" አለኝ?

ገና ምንም ሳላስብ፡ "እባቡ ነው፡" አለ።

297 ከእንግዲህ ወዲህ እንስሳ አይደለምና፡ በትክክል እንደዚያው ነበር። ዘመኑ በሙሉ በሆዱ እንዲሄድ ተረግሟል። እዚህ ነው። ልክ ነው? አሁንም እሱ ባደረገው ተግባር ላይ፡ ልክ እንደ ወንድ ፆታ፡ በሴት ዙሪያ የሚሰራው ተመሳሳይ ኃጢአት አለ። ማንም ሰው ሊያደርግ ከሚችለው በላይ ሰሜ ሲኖራት፡ አይኖቿን የምታስለመልምበት ይህ ሁኔታዋ አለ።

298 በተደባለቀ ህዝብ ውስጥ ስለሆንን እዚህ ላይ አቆመዋለሁ። ከአንዳንድ ሰዎች ጋር፡ በበለጠ... እንነጋገርበታለን። ጋዜጦች እና ሌሎች ነገሮች በሙሉ፡ አሁን በእጄ ላይ እዚሁ ይዣቸዋለሁ፡ እና ዛሬ ጠዋት አቀርብላችኋለሁ ብዬ አሰብኩ። በዚህ ውስጥ ሙሉ ቀን እውልበታለሁ ብዬ አሰቤ ነበር፦ ግን ይህን በመናገር አሁን እዘጋለሁ።

299 ይህ ለቤተክርስቲያኔ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያኔ ሳይሆን... እኔን የሚያምኑኝ እና የሚከተሉኝ ታናሽ መንጋ፡ ይህ ለነሱ ነው።

300 በቀደም፡ የምነግራችሁ ነገር ሁሉ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ሆኖ መምጣት እንዳለበት ስለማውቅ፡ ከዚያም እርሱ በሚገልጥልኝ መጠን ቅዱሳት መጻሕፍት መያዝ እንዳለብኝ አውቃለሁና። ግን፡ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ጉባኤ ምን እለዋለሁ? መለያየት ይገጥመናል። ወንዱ በግቢው በረንዳ ላይ ተቀምጦ፡ ሌሎቹም በሌላ ቦታ ሆነው፡ 'ትቻት ልሂድን? ' ሴቶቹም ይላሉና፡ 'ባሌን ትቼው ልውጣን? ' 'ምን ባደርግ ይሻለኛል? '" "ጌታ ሆይ፡ ምን ላድርግ፡" አልኩት?

301 የሆነ ነገር እንዲህ አለኝ፡ "ወደ ተራራው ወደዚያ ውጣና፡ በዚያ ከአንተ ጋር እነጋገራለሁ።"

302 እና በተራራው ላይ ሳለሁ፡ በቱክሰን ዘንድ እያዩት እንደሆነ አላውቅም ነበር። ነገር ግን አስተማሪዎች ሳይቀር ልጆቹን፡ ሴትዋ ልጄን እና ሌሎቹን… ከክፍሎቻቸው ጠርተው፡ እንዲህ ይሏቸው ነበር፡ "በዚያ ወደ ተራራው ተመልከቱ! አሳታማ-መሳይ አምበር ደመና በአየር ላይ ይወጣል ይወርዳል፡ ወደ አየር ይወጣል ወደ ታች ይመለሳል።"

303 ወይዘሮ ኢቫንስ፡ እዚህ ነሽ? ሮኒ፡ እዚህ ነህ? በማደያው በኩል፡ በኢቫንስ ነዳጅ ማደያ ወደ ታች ወረድኩና፡ ይህ ወጣቱ ልጅ ነዳጅ ማደያው አጠገብ አገኘሁት። እና ወጣቱ ምን ሊለኝ እንደፈለገ ሳላውቅ፡ በእግር ወሰደኝና፡ እንዲህ ጠየቀኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ አንተ በዚያ ተራራ ላይ ነበርክ፡ አይደል? "

304 እኔም ምን ሊያደርግ እንደፈለገ ለማየት፡ "ምን ማለት ነው፡ ሮኒ? አልነበርኩም፡" አልኩት፡ አያችሁ። ብዙ ጊዜ ለሰዎች እንዳች ሳልናገር፡ ሳትነግሯቸው፡ የሆነ ነገር ይሆናል። ነገሩ… በተደጋጋሚ ሲሆን ስለምታዩት፡ እንዲህ ይሆንባችኋል፡ ማለት ተራ ይሆንባችኋል። አያችሁ? ለሰዎች አልነገርኳቸውም። እንዲህ አልኩት፡ "ሮኒ፡ ምን ነበር ያልከው… "

305 "የነበርክባትን ቦታ በትክክል ልነግርህ እችላለሁ፡" አለኝ። "እማዬን ጠራኋትና፡ እዚህ ጋር ሆነን፡ ደመናው ሲንቀሳቀስ፡ እና ወደ ላይ ወደታች ሲል አየነው። ከዚያም እንዲህ አልኳት፡ 'ወንድም ብራንሃም በአንድ ቦታ ተቀምጦ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እየተነጋገረ ነው።'"

306 እና የከተማዋ ሰዎች፡ ሁሉ፡ አይተውታል። ደመና በሌለበት ብሩህ ቀን፡ ይህ ትልቅ አምበር ደመና በዚያ ተንጠልጥሎ፥ እንደ ማጣሪያ እየወረደ፡ እና እየተመላለሰ በዙርያውም ሁሉ እየተሰፋፋ ነበር።

307 ወዳጆች ሆይ፡ እንግዲያውስ እኔ እዚህ ላይ እዘጋለሁ፡ እናንተ ግን ከዚህ ቀጥሉ። ይህ አሁን ለእናንተ ልነግራችሁ ያለ ነገር፡ ለእኔ የተገለጠው ያን ጊዜ ነበረ፡ ስለዚህ እንዳያልፋችሁ።

308 አሁን እኔ የምናገራቸው ከውጭ ላሉት ሳይሆን፡ እኔን እና መልእክቱን ለሚከተሉ፡ ለተከታዮቻችን ብቻ እናገራለሁ። በእግዚአብሔር ፊት ይህ ምስክርነቴን ታገሱ። ለዚህ መንጋ ብቻ ነው!

309 አሁን በዚህ ምስቅልቅል ውስጥ የተገኘነው በተሳሳተ መንገድ በተተረጎመ ቲኦሎጂ ምክንያት ነው። ልክ ነው? ለዚያም ነው እናንተ ሴቶች ሁለተኛ ጊዜ ያገባችሁት፡ እናንተም ወንዶች፡ በተሳሳተ የቲኦሎጂ ትርጉም ምክንያት ነው። አሁን እሱ የነገረኝን አንድ ነገር ላሳያችሁ እፈልጋለሁ።

310 እና ፈጣሪያችን፡ እግዚአብሔር፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እዚህ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ጥያቄው ተጠየቀ፥ ይህም ሙሴ የተባለው፡ ነጻ አውጪ የሆነው የራሱ ነብይ፡ ልጆቹን ከግብጽ ለማውጣት፡ እና በተስፋይቱ ምድር ላይ ለማስፈር፡ ወደ ግብጽ በወረደ—ጊዜ ነበር፡ ኢየሱስም ስለዚህ ሲናገር ሙሴ ህዝቡን በዚህ ሁኔታ ሰላያቸው፡ የፍች ጽሕፈት ፈቀደላቸው አለ፡ ምክንያቱም ሁኔታው እንደነበረ ነበር። ሙሴም፡ እንዲሁ፡ "ለመታገስ… " እግዚአብሔር፡ ወደ ሕዝቡ የላከው ነብይ ሙሴን፡ የፍቺ ጽሕፈት እንዲሰጣቸው ፈቀደላቸው።

311 እና በአንደኛ ቆሮንቶስ፡ ስ—ስ 7ኛው ምዕራፍ፡ 12ኛው እና 15ኛው ቁጥር ላይም፡ የአዲስ ኪዳኑ ነቢይ፡ ጳውሎስ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተመሳሳይ

ነገር ገጠመው፡ እና እንዲህ ተናገረ፡ "ይህ እኔ እንጂ፡ ጌታም አይደለም።" ልክ ነው? በፍቺ ሁኔታዎች ምክንያት ነው።

312 "ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም።" ሙሴ ግን ፈቀደ፡ እግዚአብሔርም ጽድቅ አድርጎ አጸደቀው። እና ጳውሎስም ቤተክርስቲያኑን በዚህ ሁኔታ ሲያገኛት፡ መብት ነበረው።

313 አሁን ይህ እውነት እንደሆነ እመኑት፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ እመኑ! እንግዲያውስ እዚህ ድረስ ባደረሰኝ በመልእክቱ እና ለምስክር በመጣው ደመናው፡ እግዚአብሔር በተራራው ላይ ያንኑ ነገር አደርግ ዘንድ እናንተንም፡ ባላችሁበት ሁኔታ እንድትቀጥሉ፡ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትደግሙት እታገሳችሁ ዘንድ አልፈቀደለኝምን! ከሚስቶቻችሁ ጋር በሰላም ኑሩ፡ ጊዜው በደጅ ነውና። የጌታ መምጣት በደጅ ነው። እነዚህን ነገሮች ለመተንተን ጊዜ አላገኘንም። እንደገና ያን ለመድገም እንዳትዳፈሩ! የምናገረው ለጉባኤዬ ብቻ ነው። ባለ ትዳር ከሆናችሁ… ይህንም እንድል፡ እግዚአብሔር፡ በተራራው ላይ መሰክሮልኛል፡ በሰባቱ ማኅተሞች መከፈት ምክንያት፡ ይህም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለ ጥያቄ ነውና፡ በመለኮታዊ መገለጥ መሰከረልኝ። "ተዋቸው፡ ባሉበት ይቀጥሉ፡ ከእንግዲህ ደግመው ኃጢአት አይስሩ!"

314 "ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም።" ትክክል ነው፡ እንደዚያ አልነበረም፡ በመጨረሻ ላይም እንዲህ አይሆንም። በዘመናዊነት ሁኔታዎች ግን፡ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ… ራሴን የሱ ነቢይ ነኝ ለማለት አልደፍርምና፥ ምናልባትም ለዚያ ነገር ተልኬ ይሆናል፡ ብዬ አምናለሁ፡ እርሱ ሲመጣ መሰረት እያነጠፍኩለት ነውና። ስለዚህ በዚህ በዘመናዊነት ሁኔታዎች ውስጥ፡ ሚስቶቻችሁን ይዛችሁ፡ ወደ ቤታችሁ እንድትሄዱ አዛችኋለሁ። በእሷ ደስተኛ ከሆናችሁ፡ ከእርሷ ጋር ኑሩ፡ ልጆቻችሁን በእግዚአብሔር ምክር አሳድጉ። እንደገና ይህን ካደረጋችሁ ግን እግዚአብሔር ይማራችሁ! ልጆቻችሁን እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ እንዳያደርጉ አስተምሯቸዋል፡ በእግዚአብሔር ምክር አሳድጓቸው። አሁንም ባላችሁበት ሁኔታ ሆናችሁ፡ አሁን በምንኖርበት የፍጻሜ ሰዓት ላይ፡ እንቀጥል፡ እና "በክርስቶስ ወዳለው ከፍተኛው ጥሪ ለመድረስ እንትጋ፡" በዚያም ሁሉም ነገር ይቻላልና።

315 ዛሬ ማታ እስካያችሁ ድረስ፡ ጌታ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ እንጸልይ።

316 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ እናመሰግንሃለን። ምስጋናን እናቀርባለን። አንተ ሙሴን የታገስከው ታላቅ እግዚአብሔር ነህ። ያ አገልጋይ፡ ሙሴ፡ ለህዝቡ ምንስ ይላቸዋል? እና፡ አምላክ ሆይ፡ የፍች ጽሕፈትን እንዲሰጣቸው ፈቀድክለት። እንዲሁም ሙሴ ብሉይ ኪዳን እንደጻፈ፡ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ የሆነው ታላቁ ሐዋርያም፡ ጳውሎስ ነበረ። ሙሴ ሕጎችንና የሕጎችን የዘመን ሙላቶች ጻፈ። ብዙዎቹ ነቢያት፡ ቃላቶቻቸው ከሱ ጋር የተያያዙ ናቸው፡ ሕጎቹን የጻፋቸው ግን ሙሴ ነው። ከልባቸውም ጥንካሬ የተነሣም፡ የፍቺን ጽሕፈት ይጽፍላቸው ዘንድ፡ ፈቀድህለት።

317 ታላቁ ቅዱስ ጳውሎስም፡ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ እንደመሆኑ መጠን፡ እንዲህ ያለውን ማረጋገጫ ሊሰጥ ችሏል፡ "በእነዚህ ነገሮች ላይ እኔ እናገራለሁ፥ እኔ፡ ጌታም አይደለም፡" በማለት።

318 ዛሬም እንዲሁ ነው፡ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ በዓለም ፍጻሜ ላይ፡ በእግዚአብሔር ምሕረት ሥር ሆነናል፡ በቅርብ በፊቱ መልስ እንደምንሰጥ አውቀናልና። አንተም በህዝቡ ፊት፡ ይህን ሁሉ በማድረግህ፡ ጌታ ሆይ፡ ከአንተ ዘንድ እንደመጣ አድርገው፡ አጥብቀው እንደሚይዙት እተማመናለሁ። ዛሬም በአውሎ ነፋስ የእግዚአብሔር መላእክት የመጡበት፡ ሰባት መላእክት ሆነው የተገለጡበት፡ የሰባቱ ምስጢራት መገለጥ የተከፈተበት፡ በተራራው የታየውን ምልክት ማየታቸውን ምስክር ለመሆን፡ ብዙ ሰዎች እዚህ ተቀምጠዋል፥ በተራራው ላይም፡ ይህ ነገር በተገለጠበት ቀን፡ በተመሳሳይ አቅጣጫ፡ ይህ ራሱ መልአክ ነበረ!

319 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህን ጸጋ ከእግዚ አብሔር ዘንድ ሰለ ተሰጣቸው ሕዝቡ እያመሰገኑ ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ በማስፈቀድ ብቻ፡ ተናገርኩ። እኔም ጌታ ሆይ፡ በፈቃድ ብቻ ነው እላለሁ። ህዝቡም በድጋሚ ያንን ኃጢአት ለመሰራት ሰለማይሞክር እጅግ ያመሰግንህ! በሙሉ ልባቸው ይውደዱህ እንጂ፡ ከእንግዲህ ምንም አይነት ኃጢአት ለመሰራት እንዳይሞክሩ። ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ቤተሰቦች ደስታ ሰጣቸው፡ ልጆቻቸውንም በእግዚአብሔር ምክር ማሳደግ እና ማነጽ ይሁንላቸው።

320 ጌታ ሆይ፡ በልቤ የነበረው መልእክቴ፡ ደርሷልና። እንዴት ማድረግ እንዳለብኝ በማውቀው ሁሉ አድርጌያለሁ። ሰይጣንም ለሳምንታት እና ለብዙ ሰዓታት፡ እንቅልፍ በማሳጣት ተዋግቶኛ ነበር። አሁን ግን፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህ ሰዎች እንዲያጠኑት፡ ሄደውም፡ ሰለ አንተ እንዲኖሩ አዝዣለሁ። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። አሁን ከትከሻዬ ተራግፏል። በእጅህ ውስጥ ናቸው። እንድትባርካቸው እጸልያለሁ።

321 ጌታ ሆይ፡ ለታመሙ እና ለተቸገሩት፡ አሁን የቀረቡትን፡ እነዚህን መሃረብ ባርካቸው። ይህች ሌሊት ሰዎች ሁሉ የሚፈወሱባት፡ ከታላላቅ ኃያላን ምሽቶች፡ አንዷ ይሁን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ሁላችንም ባርከን።

322 "ከመጀመሪያው ጀምሮ" የነበረውን ነገር፡ የፍጥረት ሁሉ አምላክ ይህን ሰላሳየን በሰላም፡ በደስታ፡ በኃሴት እንሄዳለን፡ እና በዚህ ባለንበት፡ በመጨረሻው ዘመን ላይ፡ ጸጋውን እንደገና፡ ለእኛ ዘረጋ። ታላቅ እና ዘላለማዊ አምላክ ሆይ፡ አቤት እጅግ እናመሰግንሃለን! እና ልባችን በጣም ደስተኛ ይሁን፡ በአንተ ላይ ለመበደል ሌላ ፍላጎት እንዳይኖረን ያደርጋልና። በኢየሱስ ሰም። ኣሜን።

እወደዋለሁ፡ (እሱን መውደድ አይገባችሁምን? )
  እወደዋለሁ
ቀድሞ ሰለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ላይ...

323 አገልጋዮች የሆኑ ይህ እንዲረዱት እንዲህ እላለሁ። ይህ መእልእክቱን ለሚከተሉ ሰዎች ብቻ ነው!

324 ኦህ፡ ደስተኞች ናችሁን? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እንዳች ሳላሰቀር፡ እውነትን ነግሬአችኋለሁ፡ **ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር**! ["አሜን!"]

325 አሁን ቆመን እጆቻችንን አንስተን ደግመን፡ “እወደዋለሁ፡” እንዘምር። ስለ ጸጋው እወደዋለሁ። ስለ ምህረቱ እወደዋለሁ። ስለ ቃሉ እወደዋለሁ። “የጌታም ቃል ወደ ነቢያት ይመጣልና!”

እኔ...

326 ና፡ ወንድሜ፡ ቀጥል።

65-0221M ጋብቻ እና ፍቺ
ፓርክቪው ጁኒየር ሀይ ስኩል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org